
በተሾለይ ለመጣቸች

በተለይ ለወጣቶች

ቢትሪስ ኮልመን

የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በካናዳ

ማውጫ

ገፅ

ክፍል 1 መግቢያ

ምዕራፍ 1. ዕድገት 1

ክፍል 2 አካላዊ ዕድገት

ምዕራፍ 2. በወንዶች ልጆች ላይ የሚታይ አካላዊ ለውጥ 5

ምዕራፍ 3. በሴቶች ልጆች ላይ የሚታይ አካላዊ ለውጥ 8

ምዕራፍ 4. ከመወለድ በፊት 11

ክፍል 3 ራስን መቀበል

ምዕራፍ 5. ራስህን እንደ አንተነትህ መቀበልን መማር 15

ምዕራፍ 6. በወጣትነት ጊዜ መጀመሪያ የሚከሰቱ ችግሮች 19

ክፍል 4 በጉርምስና ጊዜ ያሉ ግንኙነቶች

ምዕራፍ 7. ከቤተሰብህ ጋር መግባባት 23

ምዕራፍ 8. ትምህርት ቤትስ እንዴት ነው? 26

ምዕራፍ 9. ቤተክርስቲያን ምንድን ነው? 29

ክፍል 5 ለአዋቂነት መዘጋጀት

ምዕራፍ 10. እራስን መቆጣጠር 33

ምዕራፍ 11. የሕይወትህ ሥራ 39

ምዕራፍ 12. የመቀራረብ፤ የመግባባት ጊዜና ጋብቻ 44

ምዕራፍ 13. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕይወትህ ማወቅ 48

ኤይድስ እና ክርስቲያን 55

መቅድም

«በተለይ ለወጣቶች» የተባለው መጽሐፍ የተጻፈው ለእናንተ ነው። የዕድገትን ሂደት ለማወቅ ትፈልጋላችሁን? ሙሉ ሰው ለመሆን ትጓጓላችሁን? በአሁኑ ጊዜ በሰውነታችሁ ላይ በምታዩት ለውጥ ትደነቃላችሁን? እነዚህን ነገሮች በአሁኑ ጊዜ ለማወቅ የምትፈልጉ ከሆነ እንግዲያውስ ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ለእናንተ ነው።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ወደ ሙሉ ሰውነት ስለምትሸጋገሩበት የሕይወት ደረጃ አሁን እንነጋገር። ምንአልባት ስለወጣትነት ጊዜ አንዳንድ ነገሮች ብታውቁም ዝርዝር ሁኔታው ይበልጥ ግልጽ ሲሆንላችሁ ትወዱት ይሆናል። ምናልባት ይህን አስፈላጊ የሕይወት ዘመን ገና ማወቅ የጀመራችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ።

ብዙ ወጣቶች ስለ ዕድገት ሂደትና ችግሮች በግልፅ የሚያናግሯቸው ወላጆች አሏቸው። ይህን መጽሐፍ እንዳነበባችሁ ስለተለያዩት የእድገት ደረጃዎች ከእነርሱ ጋር መወያየት ያስደስታችሁ ይሆናል። ሌሎቻችሁም እንዲህ ዓይነት ነገር ከወላጆቻችሁ ጋር መነጋገር የማትችሉ ትኖራላችሁ፤ ምክንያቱም የግል ጉዳዮችን አንስተው ለመወያየት ወላጆቻችሁ የተቆጠቡና ደስ ላይላቸውም ይችላል። ይህን መጽሐፍ በማንበብ እነርሱም ደግሞ ይጠቀሙ ይሆናል።

ዕድገት በጣም የተወሳሰበና አንዳንዴም ደግሞ ስቃይ ያለበት ነው። በመሆኑም «በተለይ ለወጣቶች» የተባለው መጽሐፍ የተዘጋጀው እናንተን ለመርዳት ነው። ለጥያቄአችሁ ሁሉ መልስ ባይሰጥም እንኳ አንዳንድ ጥያቄአችሁንና ስለ አንዳንድ ሌሎች ነገሮች መልስ ለማግኘት ሊረዳችሁ ይችላል።

ክፍል 1
መግቢያ

ምዕራፍ 1 ዕድገት

ዓላማ፡- ወጣትነት ምን እንደሆነ ለመግለፅና ወጣቶችም ወደ ጎልማሳነት የሚመራቸውን የራሳቸውን ዕድገት እንዲገመግሙ አጋጣሚውን ለማመቻቸት ነው።

መታወስ የሚኖርበት ጥቅስ፡- በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ። 2ኛጴጥ. 3፡18

መግቢያ

ብዙ ጊዜ «እንደምን ነህ?» ተብለህ ስትጠየቅ ብዙ ሳትጨነቅ መልስህ «እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ» ትላለህ።

እንደ እውነቱ ግን ምን ይሰማሃል? ስለ ራስህ፣ ስለሌላ ሰው፣ ስለ ቤተሰብህ፣ ስለጎረቤተህና ስለቅርብ ጓደኞችህ ምን ይሰማሃል?

አሁን ባለህበት የወጣትነት እድሜ ስለብዙ ነገሮች ያለህ ስሜት በፊት ከነበረህ አስተያየት እጅግ በጣም ተለውጧል። የዚህ ምክንያት ሕፃንነትህ አብቅቶ ትልቅ ሰው የመሆን እድገትህ በፍጥነት ስለተቃረበ ነው። አካልህ፣ አስተሳሰብህና ስሜትህም እየተለወጠ ነው።

እስከ አሁን ድረስ ተቃራኒ ፆታህን ማራቅ አለብኝ ብለህ ታስብ ነበር። አሁን ድንገት ደስ የሚሉና የሚስቡ ሆነው አግኝተሃቸዋል። እንዲሁም ትምህርትህን ስትጨርስ ምን እንደምትሆን ታስባለህ። ማንን እንደምታገባ ታስባለህ የት እንደምትኖርና ምን ዓይነት ሥራም እንደምትይዝ ታሰላስላለህ።

በእርግጥ ወላጆችህን ትወዳለህ፣ ነገር ግን ስለ ራስህ ለማሰብ ደግሞ አጋጣሚ እንዲኖርህ ትፈልጋለህ። እንዲያውም አንዳንዴ ወላጆችህ ጓላ ቀርና ዕውቀት የሚያንሳቸው መስለው ቢታዩህም፣ አንተ የሚገባውን ክብር ትሰጣቸዋለህ። ሆኖም ሁልጊዜ ልትረዳቸው ስለማትችል ግራ የገባህና የተምታታብህ ይመስልሃል።

ትምህርት፡-

እንደ እነዚህ ዓይነት አንዳንድ ስሜቶች ካሉህ እንግዲያውስ አንተ ጤናማ የሆንክ ጎረምሳ ነህ! ይህንን ታውቅ ኖሯልን? ይህ በወጣትነት ዕድሜ ውስጥ ባለ በአንድ ጎረምሳ ላይ የሚከሰት የተለመደ ለውጥ ነው።

ይህ የጉርምስና ዘመን ከአስራ ሁለት ወይም ከአስራ ሦስት ዓመት ጀምሮ በግምት እስከ ሃያና ሃያ አንድ ዓመት እስኪሞላህ ድረስ የሚቀጥል ነው። የራስህን ውሳኔ እስከምትወስን ራስህን እስከምትችል ድረስ ልጅነትህንና ወላጆችህ የሚያደርጉልህን ጥበቃና እንክብካቤ ሁሉ የምትተውበት የዕድገት ዘመን ነው።

ይህ የጉርምስና ዘመን ከአስራ ሁለት ወይም ከአስራ ሦስት ዓመት ጀምሮ በግምት እስከ ሃያና ሃያ አንድ ዓመት እስኪሞላህ ድረስ የሚቀጥል ነው። የራስህን ውሳኔ እስከምትወስን ራስህን እስከምትችል ድረስ ልጅነትህንና ወላጆችህ የሚያደርጉልህን ጥበቃና እንክብካቤ ሁሉ የምትተውበት የዕድገት ዘመን ነው።

አንተን በአንተነትህ ሙሉ ሰው እንድትሆን ብዙ ነገሮች ረድተውሃል። አንዱ የሕይወት ረቂቅ ነገር የዘር ውርስ የሚፈጠርበት መንገድ ነው። ይኸውም የወላጆችህ ባህርይ ወደ አንተ እንዴት እንደሚተላለፍ ነው። የሰው ሕይወት ሁሉ የሚጀመረው የአባት አንድ ህዋስ (ሴል) ከእናትየው አንድ ህዋስ ጋር ሲዋሃድ ነው። ይህ የመጀመሪያው ህዋስ (ሴል) ልክ አንድ ቅንጣት ዝልግልግ ጠብታ ያህል ነው። በአዲሱ ህዋስ (ሴል) ውስጥ በራሂዎች (ጂንስ) የሚባሉ አካላዊ ቅርፁን ወይም ሰው የሚያድግበትን የሰውነቱን ይዘትና ባሕሪይ የሚለዩ ነገሮች ይገኛሉ። እነዚህ በራሂዎች (ጂንሶች) ያ ሰው ወንድ ወይም ሴት፥ ረጅም ወይም አጭር፥ ጠጉረ ለስላሳ ወይም ከርዳዳ፥ በጣም ጎበዝ ወይም መካከለኛና የመሳሰሉትን ነገሮች የሚወስኑ ናቸው። እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚወሰኑት በዚያው በመጀመሪያው ህዋስ (ሴል) ውህደት ሲሆን እነዚህ የሰውነት ይዘትና ባሕሪይ የሚተላለፉት ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ ነው።

ሰው እንደመሆንህ መጠን አካባቢህ ደግሞ አንተ ላይ ተፅዕኖ አለው። አካባቢህም የተመሠረተው በዙሪያው በሚገኙት ሰዎችና ቁሳቁሶች ውጤት ነው። ይህ የሚያካትተው በማደግ ላይ የምታካብተውን ልምምድ፥ ወላጆችህ እንደ ህፃን የሚያደርጉልህን አያያዝ፥ በትምህርት ቤት የሚያጋጥሙህን ነገሮች ከጓደኞችህ ጋር ያለህን የዕለት ተዕለት ግንኙነት ጭምር ነው። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች በአንተ ላይ ተፅዕኖ አላቸው እንደውም የአንተው ተፈጥሮ ሆነዋል። ሰብዕናህ ማለት አሁን እንደሆንከው ዓይነት ባህርይ እንዲኖርህ ያደረገህ በዘር የወረስከውና አካባቢህ ተጽዎረው ነው። አንተ ተግባቢ ጓደኛ ማፍራት የምትችል ወይም ደግሞ ዓይነ ዓፋርና ዝምተኛ ልትሆን ትችላለህ። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሰብዕና ናቸው። ሰብዕናህና አመለካከትህን አካላዊና አዕምሮአዊ ብስለትህን ልምድህንና በዓለም ከሚገኘው ከማንኛውም ዓይነት ሰው ልዩ የሚያደርግህን አንተነትህን ሁሉ ያጠቃልላል።

በእድገትህ ወቅት ቢያንስ በአራት የተለያዩ መንገዶች ትዳብራለህ፡ - ከእነዚህም የመጀመሪያው አካላዊ ዕድገትህ ነው። ያም ሰው ሁሉ በግልጽ የሚያየው ነው። ቁመትና ክብደት ትጨምራለህ፤ የአዋቂ ቅርፅም ትይዛለህ። ሁለተኛውም ዕድገትህ የአዕምሮ (እድገት) ብስለት ነው። የአዕምሮ ችሎታ እግዚአብሔር ከሰጠህ ዕውቀትና ከልምምድ ጋር ተዋህዶ ብዙ ዓይነት የመማሪያ ዓይነቶችን የሚያጠቃልል ነው። በሴቶችና በወንዶች ልጆች መካከል ጎላ ብሎ የሚታይ የአዕምሮ ችሎታ ልዩነት የለም። ሆኖም ከልምምድ የተነሳ የተለያየ ችሎታ ይዘው ይሰለጥናሉ። ለምሳሌ ሴቶች ልጆች የቤት ውስጥ ሙያ ሲማሩ ወንዶች ልጆች ደግሞ የአናጢነትን፥ የእጅ ሙያ፥ የእርሻ ወይም የቢሮ ሥራ ይማሩ ይሆናል።

እያደግህ ስትሄድ ስሜትህን ተቋቁመህ መኖር የምትችልበትን ከፍተኛ ችሎታ ታዳብራለህ። ይህ ሦስተኛው የዕድገት ዓይነት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ልጆች ከወንዶች ልጆች ይልቅ ስሜታቸውን በይፋ ይገልፃሉ። ይህ በውስጣቸው ከሚኖረው ውጥረት የተነሳ ስሜታቸውን እንዲገልፁና ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይልቁንም ወንዶች ልጆች ስሜታቸውን ይደብቃሉ፤ ምክንያቱም በጎብረተሰቡ ውስጥ «ወንድ» የሚለው ስም ተጽዕኖ ስላሳደረባቸው ነው።

በመጨረሻም ማህበራዊ እድገት የሚባል አለ። እያደግህ ስትመጣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስትሆን እንዴት እራስህን እንደምትቆጣጠር ትማራለህ።

እነዚህን የተለያዩ የዕድገት ዓይነቶች እየገፋን በሔድን ቁጥር በመፅሐፋችን ውስጥ በስፋት እንወያይባቸዋለን። ማደግህንና መብሰልህን ለማወቅ ከፈለግህ ራስህን መፈተን ትችላለህ። ብዙ ሰዎች ከሚከተሉት ሦስት መንገዶች በአንዱ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል ይሞክራሉ፡-

1. ከችግሩ በመሸሽ ችግሩን ማስወገድ ትችላለህ። ይህም የሽሽት ተቃውሞ ተብሎ ይጠራል። ይህ ማለት ከሁኔታው ለመውጣት ሰበብ ትፈጥራለህ ይልቁንም ውሸት ትናገራለህ። ችግሩም እንደሌለ ታስመስላለህ።

2. ትጨቃጨቃለህ፣ መከራከርም ትችላለህ። ስትናደድ ወላጆችህ ወይም ባልንጀሮችህ ከአንተ ፊት ዘወር እንዲሉ ልትናገር ትችላለህ። ከችግሮችህ ጋርም መጋፈጥ ትችላለህ።

3. ሰውዬውንና ሁኔታውን በቅን መንፈስ ተረድተህ ለችግሩ መፍትሄ የሚሆነውን ነገር ለመፈለግ መሞከር ትችላለህ። ችግር ሲገጥምህ እንዴት መቋቋም ትችላለህ? የሚከተሉትን ምሳሌዎች በመጠቀም በቀኝ በኩል የተሰጡትን መልሶች በግራ በኩል ከተሰጡት ከእያንዳንዱ ሁኔታዎች ጋር ይዛመዳሉ ብለህ የምታስበውን እያገናዘብክ አራስህን ፈትን።

ሀ. አዲስ ትምህርት ቤት ገብተህ መማር ስትጀምር ተማሪዎቹ የማያቀርቡህ ሲሆን፣	ምንም እንዳልተሰማው መሰለህና ጓደኛቸው ለመሆን መሞከር፡- ከእነርሱ ወይስ መራቅ
ለ. በሌላ ከተማ ያለችውን እህትሽን ለመጠየቅ ትፈልጊያለሽ ነገር ግን ደህና ወይም አዲስ ልብስ የለሽም።	ማኩረፍ ለምቦጭን መጣል ወይም ማልቀስ አባትሽን አዲስ ልብስ እንዲገዛ ማስገደድ ያለሽ ልብስ ቆንጆ መስሎ እንዲታይ ማጠብና ማስተካከል (መስፋት)።
ሐ. አንተ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኘው ከቡድን ጋር የእግር ኳስ ቦታ በምትጫወትበት ቀን [ሴት ከሆንሽም መረብ ኳስ ሊሆን ይችላል] አባትህ ደግሞ እቤት ውስጥ እንድትረዳው ሲጠይቅህ።	በጣም ተናደህ አባትህን መዝለፍ ወደ ጨዋታው ያለፈቃድ መሄድ። ከአባትህ ጋር ተነጋግረህ ቢቻል ሥራው ሌላ ጊዜ እንዲሠራ ዕቅድ ማውጣት።
መ. ከአንተ ይልቅ ሌሎቹ ተማሪዎች በቂ የመዝናኛ ገንዘብ ሲኖራቸው።	በእነርሱ መቅናት ያለማቋረጥ ወላጆችህ ገንዘብ እንዲሰጡህ መለመን በትርፍ ጊዜ በቤትም ሆነ በእርሻ ቦታ እየሠራህ በግል ጥረትህ ገንዘብ ለማግኘት መሞከር።
ሠ. ትምህርት ቤት በሚሰጠው ትምህርት በአንዱ ጥሩ ባትሠራ።	አስተማሪውን ትወቅሳለህ ትምህርቱን ፈፅሞ ትተዋለህ አስተማሪውን እርዳታ ትጠይቃለህ።
ረ. ሁሉ ሰው ወንድምህን ቢወድ ስለሚሠራው መልካም ነገርም ቢያደንቁት።	እርሱ የሠራውን ነገር ለመከረጅ መሞከር መቅናት፣ እርሱንም መተቸት የራስህን ችሎታ ማሳደግ።

አሁን አንተ ከእውነተኛ ልብ በሐቅ ለሁኔታው ምላሽ የሚመስልህን ሰጥተሃል። እንደገናም መለስ ብለህ የተሻለ መንገድ ነው ብለህ የምታምንበትን ምረጥ። ይህ የራስህን ሰብዕና የምታሻሽልበት አንድ መንገድ ነው። የሕፃንነት ዝንባሌህን፥ ስሜትህን ተቋቁመህ በጣም በበሰለ መንገድ መግለፅ በምትችልበት ሁኔታ ትመራለህ። እንዲሁም ወደፊት ችግርን እንድትጋፈጥ ይረዳሃል። አንድ ነገር ከመሥራትህ በፊት ሁልጊዜ ቆም ብሎ ማሰቡ መልካም ነው።

ችግር ሲገጥምህ እንዴት እንደምትቋቋመው እግዚአብሔር ማወቅ እንደሚወድ መረዳት የሚያበረታታ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ብዙ ችግር እንዲገጥመን የሚፈቅደው ራሱ ሲሆን በችግሮቹም ውስጥ እየበሰልን እንድንሄድ ፈቃዱ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። እግዚአብሔር ልጁን ጌታ ኢየሱስን እንድንመስለው ይፈልጋል። ይህንን ይበልጥ መማር የምንችለው በሁኔታዎች ውስጥ ሆነን የራሳችን ምርጫ ሲኖረን ነው። ለችግርህ መፍትሄ እንዴት እንደምታገኝ ጥቂት አስብና እግዚአብሔር ትክክለኛውን አቋም እንዲሰጥህ ጠይቀው። እግዚአብሔር ያቀደልህን ዓይነት ሰው እስከምትሆን እርሱ በዚህ በወጣትነት ዕድሜህ እንድታድግ ይረዳሃል።

ለአስተማሪዎች

የሚጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያዕ. 1፡2-4 ዮናስ 4፡1-11 ሉቃ. 2፡40፥ ሉቃ. 2፡52 ሰዎች ለችግራቸው መፍትሄ የሚፈልጉባቸው ሦስቱን መንገዶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፋቸውና ተወያዩባቸው። ስድስቱን ችግሮች ጻፋቸውና ተማሪዎቹ የመጀመሪያው ምላሻቸውን ከውስጥ የሚሰማቸውን ስሜት ሳይደብቁ በግልጽ እንዲጽፉ አድርግ። መልሳቸውን ከላይ ከተሰጡት ከሦስቱ መንገዶች ጋር አመሳስሉት። ከዚያም ስድስቱን ችግሮች እንደገና እንዲያዩት አጥጋቢ የሆነ መልስም እንዲሰጡ አድርጋቸው።

ክፍል 2
አካላዊ ዕድገት

ምዕራፍ 2
በወንዶች ልጆች ላይ የሚታይ አካላዊ ለውጥ

ዓላማ፡ ወንዶች ልጆችን በወጣትነት መጀመሪያ ዕድሜአቸው ለሚከሰተው አካላዊ ለውጥ ለማዘጋጀት።

መታወስ የሚናርበት ጥቅስ፡- ኢየሱስ ክርስቶስም በዕውቀትና በማስተዋል በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ያድግ ነበር። ሉቃ 2፡52

መግቢያ

«ማርቆስ ስታድግ ምን ለመሆን ትፈልጋለህ?» ብሎ አንቱ ጥላሁን ጠየቀው። የአምስት ዓመት ልጅ የሆነው ማርቆስም ትንሽ ሸምቀቅ ቢልም ነገር ግን በግልጽ እንዲህ አለ «ሳድግ ትልቅ ሰው መሆን እፈልጋለሁ!» ይህ የሁሉም ወንዶች ልጆች መልስ ነው።

ትምህርት፡-

በልጅነት ወቅት ወንድ ልጅ ትልቅ ሰው ለመሆን በጣም ረጅም ጊዜ የሚወስድበት ሆኖ ይሰማዋል፤ ነገር ግን ጊዜው ወዲያውኑ ይደርስና አብዛኛውን እድገቱ በጉርምስናው ጊዜ ይፈጥናል።

በዚህ አስደናቂ የሕይወት ወቅት በጣም ጉልህ ሆኖ የሚታየው ቅጽበታዊው የቁመትህ መጨመር ነው። ምናልባት ተደጋግሞ የሚሰማው አባባል «ወይ ጉድ! ረዥም ሆነህ የለ እንዴ!» የሚል ነው። ጓደኞቻችሁም የትከሻችሁን መስፋት ይመለከታሉ። ይህ የሚያመለክተው የጡንቻቻችሁን መዳበርና የአጥንታችሁን መስፋት ነው።

እግርህንና እጅህን ተመልከት። እንዲያውም ለውጥህን ላታጤነው ትችላለህ። ነገር ግን አባትህ ይህንን ያውቃል። ምክንያቱም አሮጌው ጫማችሁ ሳያልቅ ሌላ አዲስና ሰፋ ያለ ጫማ እንደሚያስፈልግህ ትናገራልህ! በዚህ ዕድሜ ሰውነትህ በቶሎ ስለሚያድግ መደናቀፍም ሆነ ዕንቅፋት በቀላሉ ያጋጥምሃል። በምትራመዱበት ጊዜ ዕንቅፋት ይመታህና እንዲያውም ትወድቅ ይሆናል። ቅልጥፍና የጎደለውና የገልጃጅነት ስሜት ቢሰማህ አትጨነቅ። ምክንያቱም ይህ የሆነው በፍጥነት ስላደግህ ነው። እግር ኳስ ወይም ሌላ ደስ የሚልህን ማናቸውንም ነገር ከመጫወት አትቦዝን። ልምምዱ ነገሮችን ያለችግር በቀላሉ ለማከናወን ይረዳሃል፤ በተጨማሪም ሰውነትህ በቅልጥፍና ይታዘዝልሃል። ትዕግሥት ይኑርህ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ መርዘም እስከምትችልበት ደረጃ ድረስ ቁመት ትጨምራለህ። ስለዚህ እጅህ ምን ያህል መዘርጋት እንደሚችልና እንዴትስ ጠንካራ እንደሆነ ለማወቅ ትችላለህ።

ገጽህም ይቀየራል። ፊትህ ይረዝማል፤ አፍንጫህና አገጭህም ከበፊቱ የበለጠ ሾል ያለ ይሆናል። ፊትህስ ላይ ያለው ለስላሳ ጠጉርስ? አሁን ትንሽ ጢም ብቅ ብቅ እያለ ነው! ጢምህን አንዳንዴ በመላጨት ምንአልባትም በሳምንት አንዴ ሙከራ ለማድረግ ትፈልግ ይሆናል።

በፈትህም ላይ ብጉር ይታይ ይሆናል። ይኸውም በፈትህ ቆዳ ውስጥ የሚገኙት ትንንሽ (ዕጢዎች) ግላንድስ ለአዲሱ የሰውነትህ ፍላጎቶች ለማሟላት ሥራቸውን በጣም ስለሚሠሩ ነው። እነዚህ ዕጢዎች (ግላንድስ) ቆዳህን ለማለስለስ ቅባት የመሰለ ንጥረ ነገር ይፈጥራሉ። አንዳንዱ ትንሹ ከረጢት መሳይ ነገር ይሞላና መንገዱን ይዘጋል። በዚህ ጊዜ ወደ ውጪ ሲተፋ ብጉር የሚባለው ይወጣል። ፈትህን በየቀኑ በሳሙናና ለብ ባለ ውኃ ታጠብ፤ ነገር ግን ብጉሩ እየባሰ ከመጣ ለሐኪም ማሳየቱ ይበጃል።

ጢምህ እያደገ በመጣ ቁጥር እግርህና ክንድህ በፍጥነት በፀጉር መሸፈን ይጀምራል። እንዲሁም በብብትህና በሰዋራ ቦታዎች ላይ ጠጉር ማደግ ይጀምራል።

ሙሉ ሰው የመሆን ደረጃ መድረስህን የሚያመለክተው ሌላው እውነት በጉሮሮህ ላይ የሚታይ የዕድገት ሂደት ነው። ስለዚህም የአዳም ፍሬ ተብሎ የሚታወቀው ማንቁርትህ ስለሚያድግ ድምፅህ ጎርናና ይሆናል። ሆኖም ቮይስ ቦክስ ወይም አዳም አፕል (ድምፀ ከረጢትህ) በአንድ ሌሊት አያድግም። ስለዚህ ድምፅህ ለጥቂት ጊዜ እንደዚሁ ይቆያል። አንዳንዱ ስትናገር ድምፅህ ቆንጆና ወፈር ያለ ይሆናል ሌላ ጊዜ እንደበፊቱ የሕፃንነት ድምፅህ ቀጭንና ቃጠሎ ይሆናል። ይህ ለውጥ በቃላት መካከል እንኳ ሊደመጥ ስለሚችል አትጨነቅ። ይህ አንተ ጎረምሳ በመሆን ላይ እንዳለህ የሚያረጋገጥ ሌላው ማስረጃ ነው።

በሰውነትህ ውስጥ ይህ ሁሉ ለውጥ እንዲፈጠር ያደረገው ምንድን ነው? ይህን ለውጥ ያመጣው ሆነ የሚቆጣጠረው የዘር ፍሬ ነው። በወንድ አባለ ዘር ብልት ጎን የሚገኘው ስክወተም [በቆዳ የተሸፈነ ብልት] ውስጥ የሚገኝ ሁለት ዕጢዎች ቴስትክልስ [ብልት] ቆለጥ የሚባለው ነው። ይህ የዘር የፍሬ ሽፋን [ቆለጥ] ለስላሳና ላላ ባለ ቆዳ የተሠራ ከረጢት መሳይ በወንዶች ልጆች እግር መጋጠምያ መካከል ከሰውነቱ ጋር ተያይዞ የሚገኝ የተንጠለጠለ ነገር ነው። በሕፃንነት ዘመን እስከል (በጭንቅላታችን) ውስጥ ከሚገኘው የሰውነት ዕድገት ከሚቆጣጠረው ዕጢ [ፒቱታሪ] መልዕክት በመቀበል ድምፅህ በወፈረ ወቅት ይህም [የዘር ፍሬ] ቴስትስ እያደገ ይሄዳል። ከዚህ በኋላ [የዘር ፍሬ] ቴስትስ 2 ዓይነት ሥራዎች ይኖሩታል።

በመጀመሪያ [የዘር ፍሬው] ቴስተስ በሰውነት ውስጥ ሁሉ የሚተላለፍና በዚህ ምዕራፍ የተገለጡትን ለውጦች የሚያመጣውን ውሑድ ያሰናዳል። የሰውነት የተፈጥሮ ቅመም (ሆርሞን) ተብለው የሚጠሩትን ንጥረ ነገሮች ለቀሪው የሕይወትህ ዘመን ሁሉ ያዘጋጃል። እንዲሁም የወንድ ባሕሪይ እንዲኖር ያደርጋሉ።

የዘር ፍሬ ሌላው ተግባርም የወንዴ አባለዘር [ስፐርማቶዚ] በእጭሩ አባለዛር የወንዴ ዘር (ስፐርም) ተብሎ የሚታወቀውን ማዘጋጀት ነው። የወንዴው ዘር እንቁራሪት እጭ የመሠለ ቅርፅና ትንሽ ጭራ ያለው ነው። ወደፊት ስለወንዴው ዘር (ስፐርም) በሰፊው እንማራለን። በጣም የሚያስገርመው ይህ ዘር (ስፐርም) በጣም ሞቃት በሆነ ሥፍራ መኖር ስለማይችል፤ የፍሬ ዘር [ማህደረ ቴስተስ ወይም ቆለጥ] ከሰውነት ውጪ ተንጠልጥሎ ይገኛል።

ከ ቆለጥ ፊት ለፊት የሚገኘው የእጅ ጣት የመሰለ የወንድ አባለ ዘር ፔኒስ (ቁላ) ይባላል። በቁላ ጫፍ ውስጥ ባለው የቀዳዳ ጫፍ ሽንት ይወጣል። ሕፃን ልጅ ሲወለድ የቁላው ጫፍ በትንሽ ቆዳ በመሰለ ሽለፈት ይሸፈናል። ብዙ ጊዜ ወላጆች ይህ ሽለፈት ቢወገድ (ቢገረዝ) ይመርጣሉ። ይህ ግርዘት የሚባለው ቀላል ቀዶ ጥገና በሐኪም ቤት ወይም ንፅሕና በተሞላው መንገድ መፈፀም አለበት። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ስምንት ቀን የሞላው አይሁዳዊ ወንድ ልጅ ሁሉ እንዲገረዝ ይፈልግ ነበር። ይህ ድርጊት አይሁዳዊ ወንዶች ልጆች ሁሉ በእግዚአብሔር

የተመረጡ ሰዎች መሆናቸውን የሚያሳይ ምልክት ሆኖ የሚያገለግል ነበር። ዛሬ ሳይንሳዊ በሆነ አመለካከት በቀላሉ የሰውነት ንፅሕና ለመጠበቅ የሚጠቅም ዘዴ ነው።

በቁላ ውስጥ የሚገኝ (ስስ የሆኑ አካላት) ስፖንጅ መሳይ ናቸው አንዳንዴ ደም በብልቱ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ይገተራል [ቀጥና ግትር ያለ ይሆናል] ይህ የሚሆነው በጣም ጠባብ የሆነ ልብስ ሲለበስ ፊኛ ሲሞላ ወይም የፍትወት ፍላጎት ሲቀሰቀስ ነው። ሆኖም ብልቱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደቀድሞው ቅርፁና ቦታው ይመለሳል።

በአንድ ጤናማ ወጣት ብልት ውስጥ በቀን በርካታ ስፐርም ይፈጠራል እስከ ሃምሳ ሚሊዮን የሚደርስ [የወንዴው ዘር] ይሰናዳል። የወንዴው ዘር [ስፐርም] ከፍሬ ዘሩ ተነሥቶ (በማስተላለፊያው) በሁለት ነገር በኩል (ውስጥ) አድርጎ ወደ አንዱ ሴሚናል ቬስትክልስ [ተጨማሪ ፈሳሽ የሚያመነጩ ዕጢዎች] ወደሚባለው ከረጢት መሳይ ነገር ውስጥ ይገባል። ይህ ከረጢት መሳይ ነገር በወንዴው ዘር ፈሳሽ ነገር (ስፐርም) ከተሞላ በሕልም የፈሳሽ ነገር መውጣት ማየቱ የተለመደ ነው። ይህ የተጠራቀመው ፈሳሽ በወንዴው የሽንት መሽንያው አድርጎ ወደ ውጪ ይወጣል። ይህ የሚፈፀመው ሌሊት በዕንቅልፍ ልብ ነው።

በሕልም ስለማፍሰስ ሁኔታ [መርጠብ] ብዙ መጥፎና እውነት ያለሆኑ አስተሳሰቦች አሉ። አንዳንድ ወጣቶች በዚህ ጊዜ የሕሊና ፀፀት ያድርባቸዋል። አንድ መጥፎ ነገር ወይም ኃጢአት እንደሠሩ ይሰማቸዋል። ሌሎች ደግሞ በሕልሙ አማካኝነት በሚመጣው ስሜት በመደሰት ሰውሰራሽ በሆነ መንገድ ብልታቸውም በመጠቀም ድርጊቱን እንደገና ለመፈፀም ይሞክራሉ ይህ የሞኝ ልማድ ስለሆነ ድርጊቱን መቀጠል አይገባቸውም። አንዳንዶች ደግሞ ይህ ሰውነትንም ሆነ ዕውቀት የሚያዳክም ጎጂ ድርጊት ነው ይላሉ። ሆኖም ከእነዚህ አስተሳሰቦች አንዱ እንኳ እውነት አይደለም።

በዚህ የዕድገት ደረጃ ወቅት የጡቶችህ ጫፎች ሊሰፉ ይችላሉ። እንዲሁም ደግሞ ለጥቂት ሳምንታት ያህል በዚህ የጡትህ ጫፍ አካባቢ ትንሽ እብጠትና የመቆጣት ስሜት ሊሰማህ ይችላል።

በዚህ ምዕራፍ ያየነው የአካል ለውጥ በሙሉ በወጣቶች ሁሉ ላይ የሚታይ ነው። ነገር ግን እነዚህ ለውጦች ሁሉ መታየት የሚጀምሩት ለተለያዩ ሰዎች በተለያዩ የዕድሜ ደረጃዎች ነው። ስለዚህ ባልንጀራህ ከአንተ ቀድሞ በቁመት ቢረዝምና ቢጎረምስ አትጨነቅ። እግዚአብሔር አንተን በፈለገበት መንገድ ሠርቶሃል። እንዲሁም አንተን ትክክለኛ በሆነ ጊዜ እንደሚያሳድግህ አትዘንጋ። ይህ የተወያየንባቸው የዕድገት ደረጃዎች ለመከናወን ብዙ ጊዜ ስለሚወስድ በሰውነትህ ሥራና አሠራር ለውጥ በሚታይበት ጊዜ ትዕግሥተኛ መሆን አለብህ። እግዚአብሔር ሙሉ ሰው ለመሆን የሚያበቃህን [የሚያስፈልግህን] ሁሉ ነገር እንደሰጠህ አካልህንም እንደፈጠረ ማወቅ ድንቅ አይደለምን? ዳዊት በመዝሙሩ 139 ቁጥር 13ና 14 ላይ «አቤቱ አንተ ኩላሊቴን ፈጥረሃልና፤ በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛልና ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች»።

ለአስተማሪዎች የሚጠቅም

- ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠና፡- ሉቃ 2፡40-51፥ መዝ. 119፡13-15
- ሥዕላዊ መግለጫውን አጥንታችሁ ልጆቹ ለሚያቀርቡት ማንኛውም ጥያቄ መልስ ለመስጠት ዝግጁ ሁኑ። አንድ ወንድ አስተማሪ ወንዶች ልጆችን ሰብስቦ ክፍል ሁለትን

ቢያስተምርና ሌላ ሴት አስተማሪ ደግሞ ሴቶቹን ሰብስባ ክፍል ሦስትን ብታስተምር መልካም ነው። ሆኖም ሁለቱንም ምዕራፎች በተጨማሪ 4ኛውን ምዕራፍ በግል ማንበብና መረዳት ለወጣቶች ጠቃሚ ነው።

ምዕራፍ 3
በሴቶች ልጆች ላይ የሚታይ አካላዊ ለውጥ።

ዓላማ፡- በወጣትነታቸው ጊዜ ልጃገረዶች በአካላቸው ላይ የሚካሄደውን ለውጥ እንዲያውቁት ለመርዳት።

የሚጠና ጥቅስ፡- «ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል።» መጽሐፈ ምሳሌ 31፡10

መግቢያ

ሂሩት ስለራሷ ልዩ ነገር እንደገጠማት ተገንዝባለች። ብዙ ጊዜ ይርባታል። እድገቷም ፈጠነባት ጡቶችዋ እያደጉና ቅርፅ እየያዙ ስለሆኑ ብቻዋን ስትሆን ባላት አዲስ ቅርፅ ትደሰታለች። ሆኖም ሌላ ሰው ይህንን ለውጥ ቢያይ በጣም ያሳፍራታል። ልብሶችዋ በጣም ጠቧታል፤ የነበራት ነገር ሁሉ በአንድ ጊዜ በጣም ያነሳት ይመስላል። አንድ ቀን በጣም የሚያስደነግጥ ነገር ገጠማት፤ ከብልቷ ውስጥ ደም መፍሰስ ጀመራት። በጣም ስለ ደነገጠች ምን ማድረግ እንደሚገባትም ግወቅ ተሳናት። አንደምትሞትም እርግጠኛ ሆነች፤ ሆኖም ለማንም ሰው ለመንገር ፈራች።

ትምህርት፡-

አንቺስ እንደ ሂሩት ነሽን? ምናልባት አንቺ ጨርሶ ያልተረዳሻቸው ሁኔታዎች በሰውነትሽ እየተፈፀሙ ነው። ምናልባትም ደግሞ በጣም ደንግጠሽ ስለሁኔታው ለማን መንገር እንዳለብሽ እንኳ አታውቂም ይሆናል። አንድ ነገር ልንገርሽ በመጀመሪያ አንቺ እንከን የሌለሽ ልጃገረድ መሆንሽን እነዚህ በአንቺ ላይ የሚፈፀሙት ለውጦችም ትክክለኛና የጤናማ ሰው ምልክት መሆናቸውን ተረጂ። አትፍሪ ይህንን ምዕራፍ በማስተዋል አንብቢው። ደረጃ በደረጃ የሚፈፀሙትን ነገሮች እንድትረጂው ለማድረግ እንጥራለን።

ትልቅ ሰው ለመሆን የሚያበቃሽን የሕይወት አስደናቂ ደረጃ ጀምረሻል። የመጀመሪያው ምልክት ቁመትሽ በአንድ ጊዜ መጨመሩ ነው። ቅርፅሽም ይለወጣል። ዳሌሽ ይሰፋል። ሰውነትሽም ጥሩ ቅርፅ ይይዛል። ቆዳሽ ይለሰልሳል የበለጠ ቆንጆም ይሆናል። ይህ በአንቺ ዕድሜ ከሚገኙት ወንዶች ልጆች የበለጠ የምትረዝሚበትና የምትወፍሪበት ጊዜ ነው። እነርሱም የራሳቸው የሆነ የዕድገት ደረጃ አላቸው ነገር ግን ከአንቺ በኋላ ይሆናል።

በዚህ ጊዜ ጡቶችሽ እያደጉና ቅርፅ እየያዙ ቀለማቸውም ከቀይነት ወደ ጥቁር ቡናማ እየተለወጡ ይመጣሉ። ጡቶችሽ እስከመጨረሻው ካደጉ በኋላ ጡት ማስያዣ ትፈልጊ ይሆናል። ለአንቺ የሚበቃሽን ተስማሚና ነድጎድ ያለ ጡት ማስያዣ መርጠሽ ግዢ። ስትሰቂ ስታንነበሺ እንዲሁም ስትተነፍሺ ሊይዝሽ አይገባም። አዲሱ ጡት ማስያዣም ሆነ በውስጥ የምትለብሺው ሁሉ በየጊዜው ታጥቦና ንፁሕ ሆነው መቀመጥ አለባቸው። አሁን አካልሽ በማደግ ላይ ሳለ የሰውነት ጠረን ስለሚኖር በየቀኑ ሰውነትሽን በሙቅ ውሃና በሳሙና መታጠብ ያስፈልግሻል። ሥራም

ስትሠሪ ሆነ ስትንቀሳቀሺ ንፁሕና ቆንጆ ጠረን እንዲኖርሽ መልካም ሽታ ያለው ቅባት ብብትሽን መቀባት ያስፈልግሽ ይሆናል።

ጠጉርም በብብትሽና (ፐልቪክ ሪጅን) በብልትሽ አካባቢ ላይ ማደጉን ታያለሽ። አንዳንድ ልጃገረዶች በፊታቸው ላይ ብጉርና ብጉር መሰል ሽፍታ ያስቸግራቸዋል። በቆዳ ውስጥ ያለው ቅባት የሚያሰናዳው (ዕጢ) ብዙ ቅባት ይፈጥርና በዚህ ጠቆርና አበጥ ባለ ሽፍታ ውስጥ ይጠራቀማል። ይህንን ሽፍታ ዘወትር ፊትንና አንገትን ለብ ባለ ውሃና በሳሙና በመታጠብ ማስወገድ ይቻላል። ብጉር የሚመጣው በውስጡ መግል ከያዘው (አባጣ) ፓርስ ወይም ቁስል መሳይ ነገር ቀዳዳ በሚዘጋበት ጊዜ ነው። ለዚህ ዋናው መድኃኒት ከላይ እንደተገለፀው ለሽፍታ ጊዜ እንደሚደረገው በጥንቃቄ ፊትን በየቀኑ መታጠብ ነው።

በልጃገረዶች የዕድገት ወቅት አስደናቂው ለውጥ የሚታየው የዕድገታቸውም የመጨረሻው ምልክት የወር አበባቸውን ማየት መጀመራቸው ነው። (የወር አበባ) በየወሩ የሚታይ ከሴቶች የሴት ብልት (ቫጃይና) የሚፈስ ደም ሲሆን ይህም ጤናማ ምልክት ነው። ከ11 እስከ 17 ባሉ ዕድሚዎች መካከል በየወሩ መታየት ይጀምራል። ከሁለት እስከ 5 ቀናት ይቆያል። አንድ ሴት የ40 ዓመት መጨረሻ እስከሚሆናት ድረስ በግምት በወር አንድ ጊዜ የወር አበባ ይታያታል።

የዚህ ነገር መነሾው ምን እንደሆነና እኛም የጤንነት ምልክት ነው ልንል የቻልንበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ትፈልጊ ይሆናል። በሴት ልጅ ውስጠኛው ሆድ ውስጥ ሁለት ትንንሽ የእንቁላል ዕጢ ማኩረቻ [እቫሪ] ግላንድስ አሉ። እነዚህ ከአውራ ጣታችን ጥፍር በመጠኑ ከፍ ያሉ የሰውነት ክፍሎች ሁለት ሥራ አላቸው።

የመጀመሪያው ሥራም በዚህ ምዕራፍ የተነጋገርንባቸውን የሴትነት ባሕሪይ በአንዲት ልጃገረድ እንዲጀመርና እንዲቀጥልም የሚያደርገውን ንጥረ ነገር (ሆርሞን) የሰውነት የተፈጥሮ ቅመም ማዘጋጀት ነው።

ሁለተኛውም ሥራ የእንቁላሉን ሴሎችን (አቫሪስ) በወር አንድ ጊዜ ማዘጋጀት ነው። ይህ የእንቁላሉ ሴል አቮም [አቮዩም] ከእስፒል ጫፍ የማይበልጥ ትንሽ ነገር ነው። ይህም ዝልግልግ ያለ ፈሳሽ መሳይ ነገር አንድ ጠብታ ያህል ነው። እርሱም ከዚህ ዕጢ ይወጣና በቱቦ መሳይ ሥር [ፍሎፒያን ቲዩብ] የማህፀን ቧንቧ አድርጎ ወደ ማህፀን ዩተረስ ይገባል። ማህፀን የኮረንቲ አምፖል የሚመስል ቅርፅ ያለው የእጅሽን ጭብጥ የሚያህል ብልት ነው። የሚገኘውም በታችኛው አካል ውስጥ ሲሆን ተለቅ ያለው ጫፉ በላይኛው፥ እነሰ ብሎ አንገት የመሰለው ጫፍ (ሰርቪክስ) ማለት የማኅፀን በር ደግሞ በታችኛው በኩል ነው። ማህፀን እንቁላሉ ከወንዴው የዘር ሴል ጋር ከተገናኘ በኋላ ልጅ የሚያድግበት ጠንካራ የአካል ክፍል ነው። በሚቀጥለው ምዕራፍ ስለልጅ አወላለድ ከዛም በኋላ ስለሚቀጥለው የሰው ዘር የሕይወት ዘመንና አስደናቂ ስለሆነው የእግዚአብሔር ሥራ እንነጋገራለን።

የተዘጋጀው የእንቁላል ሴል ከእንቁላል ዕጢ የመውጫ ጊዜው ሲደርስ ማህፀን የውስጠኛውን ቆዳ በደም በመሸፈን እንቁላሉን ለመቀበል ይሰናዳል። የእንቁላሉ ሴል ከወንዴው የዘር ሴል ጋር ካልተገናኘ እንቁላሉ ይሞትና ማሕፀን ለእንቁላሉ ያሰናዳውን ደምና የላይኛውን ለስላሳ ሽፋን ወደ ውጪ ያስወጣዋል። ይህም የአንገት ቅርጽ ባለው አካል [ሰርቪክስ (የማህፀን በር)] ወደ ታችኛው የአባለ ዘር ብልት ይገባና ከሰውነት ውጪ ይወጣል። በዚህ ዓይነትም የወር ሂደት ይቀጥላል።

እነዚህ ሁለቱ ተግባሮች በየወሩ ይፈፀማሉ። እሽም (የእንቁላሉ ሴል) እሻሪ (ከእንቁላሉ ዕጢ) [ማመንጫ] ከወጣ ሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የወር አበባ መታየት ይጀምራል። የወር አበባ ያታየበት የመጀመሪያው ቀን ከተቆጠረ ከ28 ቀን በኋላ እንደገና ሊታይ ይችላል ሆኖም የአካል ክፍሎች ሁሉ በደንብ መሥራት እስኪጀምር ልጅቱም አካለ መጠን እስከምትደርስ የወር አበባቸው በጀማሪ ልጃገረዶች ጊዜውን ባይጠብቅና አንድ ወር ወይም ሁለት ወር አከታትሎ ቢቀር አዲስ ነገር አይደለም።

የወር አበባ ጊዜውን ጠብቆ እንዳይመጣ የሚያደርጉት ብዙ ነገሮች አሉ ጉንፋን፣ በብርድ መንዘፍዘፍና የመንፈስ ጭንቀት እነዚህ ጊዜውን ሊያፈጥኑ ወይም ሊያዘገዩ ይችላሉ።

ደምና ንፍጥ የሚመስል ነገር (ሚዩከስ) የሚፈሰው ደምና ብዛት እንደ ልጃገረዶቹ ይለያያል። አንዳንድ ልጃገረዶች የወር አበባቸው በጥቂቱ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ሲቆይ ሌሎች ደግሞ በብዛት ከአራት እስከ አምስት ቀናት ያህል ሊፈስ ይችላል። በመጀመሪያ ጊዜም ቀላ ያለ በኋላ ጠቆር በሚል ደም ይጀምርና ከጥቂት ቀናት በኋላ እየቀነሰ ይሄድና በመጨረሻም ይጠፋል። ይህ ፈሳሽ ደስ የማይል ሽታ ስለሚኖረው በየቀኑ መታጠብ ያስፈልግሻል። በዚህ ጊዜ መልበስ የሚገባሽ ልብስ ምን ዓይነት እንደሆነ እናትሽን ጠይቂ። ከተጠቀምሽበት በኋላ መታጠል የሚችል ሞዴስ [ለዚሁ የተዘጋጀ ከጥጥ የተሠራ በጨርቅ የተሸፈነ] ከገበያ መግዛት ትችያለሽ። ይህ ሞዴስ በደም ስለሚነከር ከአንድ ቀን በላይ አትጠቀሚበት። በቀን ውስጥም ከተበላሸ ሌላ መቀየር ያስፈልግሻል።

ስለወር አበባ ብዙ ዓይነት ከእውነት የራቁ አባባሎች አሉ፣ ምን አልባትም አንዳንዶቹ ያስደነግጡሽ ይሆናል። ነገር ግን የወር አበባ ትክክለኛና የጤናማነት ምልክት ነው። እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ሴት አድርጎ ሠርቶሻል ለዚህም ደግሞ ምክንያት አለው። እውነተኛ ያልሆነውን ነገር አትመኚ። በሌላ ጊዜ እንደምታደርጊው በወር አበባ ጊዜ መጫወት ሆነ ሥራ መሥራት ትችያለሽ። አንዳንድ ጊዜ የወር አበባሽ ከመምጣቱ ከአንድ ቀን በፊት በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ቀን ሕመም ወይም ወገብሽን የመቁረጥ ስሜት ሊሰማሽ ይችላል። በዚህ ጊዜ ሰውነትሽ የማያስፈልገውን የዕንቁላል ሴል ለማስወጣት እራሱን እያዘጋጀ ነው። ሕመሙም ጀርባሽን ቢሰማሽ ለጥቂት ጊዜ ያህል አረፍ በይ እንጂ ቀኑን ሙሉ መተኛት አያስፈልግም። ስታርች ያልበዛበት ቀላል ምግብ፣ ፍራፍሬዎችና ብዙ ፈሳሽ ነገር እንደ ውሃና ወተት የመሰሉትን መውሰድ የተሻለ ነው። በአንቺ ላይ እየተፈፀመ ያለው ነገር ትክክለኛና ለሁሉም ሴት ልጆች የሚሆን ነገር መሆኑን ስታውቂ ነገሩን ለመቀበል አይከብድሽም።

ዕድገት የሚያስደስትና አስደናቂ ነው! ማንኛውም ልጃገረድ አድጋና ተውባ ማስተዋል ያላት ሙሉ ሴት ለመሆን ትፈልጋለች። አሁን ባለሽበት የዕድገት ደረጃ ደስ ተሰኚ ለወደፊትም እግዚአብሔር ያቀደለሽን ዓይነት ሴት ለመሆን ተስፋ አድርጊ። ብዙ ነገር የሚያሳውቅሽን የሚቀጥለውን ገፅ ለማንበብ አትርሺ።

ለአስተማሪዎች የሚረዳ

የሚነበብ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡- ምሳ. 31

ልጃገረዶች በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያሉትን ስሞች የሰውነታቸውን የተለያየ ክፍል የሚያወሱትን በስማቸው እንዲያውቁ እርዷቸው ጥያቄዎቻቸውንም መልሱ። ሐኪም ወይም ነርስ አጠገባችሁ ቢኖር ወደ ክፍሎቹ እንዲመጡና ትምህርቱን በሰፊው ለልጆቹ እንዲያስረዱ

ጥያቄዎቻቸውንም እንዲመልሱ አድርጉ ወደ ክፍል ከመምጣታቸው በፊት ልጃገረዶቹ ምዕራፉን እንዳነበቡም አረጋግጡ።

ምዕራፍ አራት
ከመወለድ በፊት

ዓላማ፡- በሰው ልጆች አፈጣጠርና አኗኗር እግዚአብሔር ያለውን አስደናቂ ዕቅድ ወጣቶች እንዲረዱና የተፈጥሮን አጀማመር ግልፅና አጠር ባለ መንገድ ለማወቅ ነው።

የሚጠና ጥቅስ «ከማህፀን የሠራህ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሁሉን የፈጠርሁ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ከእኔ ጋር ማን ነበር?» ኢሳ. 44፡24

መግቢያ

ዮሐንስ ቁመቱ ስለጨመረ ሱሪዎቹ እንዳጠሩት ተመልከቶ እራሱን በመነቅነቅ እንዲህ አለ። «ሱሪዎቼ እንዴት እንዳጠሩኝ ተመልከት! በዚህ ዓመት እንዳደኩኝ በሕይወቴ ሙሉ እንዲህ አድጌ አላውቅም።

አቶ ጥላሁን ዶክተር ለመሆን በሥልጠና ላይ ይገኛል። የልጁም አጎት በመሆኑ ልጁን አየና «አቤት! እንዴት ነው ያደከው» አለው።

«አዎን ከዚህ በፊት ልብሶቹ ሁሉ እንዲህ አጥረውኝ አያውቁም» አለ ዮሐንስ አጎቱ በሰጠው መልስ ግራ እየተጋባ።

አቶ ጥላሁን እንዲህ ሲል መለሰለት፥ «ያ እውነት ሊሆን ይችላል ነገር ግን በጣም ያደግህበት የሕይወት ደረጃህ አሁን ሳይሆን ከመወለድህ በፊት ባለው ዘጠኝ ወር ውስጥ ነበር። በዚያ ልክ እያደክ ብትመጣ ኖሮ አሁን 250 ሜትር የሚሆን ቁመት ይኖርህ ነበር»

ያ እውነት ነው። እስቲ አሁን አንድ ፅንስ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሳለ የሚካሄደውን አስደናቂ ዕድገት እንንገራችሁ።

ትምህርት፡-

ፅንስ ዕድገት የሚጀምረው በማኅፀን መነፅር ካልሆነ በዓይን ከማይታይ ከትንሽ ሕዋስ ሴል በመጀመር ነው። እነዚህ ሕዋሳት (ሴሎች) ትንንሽ ቢሆኑም እንኳ በተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸው ላይ የራሳቸው የሆነ መለያ ቅርፅ አላቸው። ለምሳሌ ያህል የነርቭ ህዋሳት (የነርቭ ሴሎች) ረዘር ያለና ቀጠን ያለ ቅርንጫፍ ያላቸው ሲሆኑ፤ የደም ሴሎች ደግሞ ክብ ናቸው» እንዲህ እያለም ይቀጥላል።

ሰውነታችን የተለያዩ ቅርፅና ይዘት ባላቸው ስፍር ቁጥር በሌላቸው ሴሎች ቢሠራም እንኳ የሰው ሕይወት የሚጀምረው ሁለት ትንንሽ ልዩ ሴሎች ሲገናኙ ነው። አንደኛው ሴል ከእናትየው የመጣው የዕንቁላል ሴል ሲሆን፤ ሌላኛውም ከአባትየው የመጣ ያወንዱ አባለ ዘር (የስፐርም ሴል) ነው።

በምዕራፍ 3 እንደተማርነው በየ ሀያ ስምንት ቀን ዕንቁላል በሴቶች የዕንቁላል ማኩረቻ (እቫሪ) ክፍል ይሰናዳል። ከዛም ወደ ቱቦ መሳይ ማስተላለፊያ [ፍሎፒያን ትዩብ] ይጋዛል። በዚህ ጊዜ ማህፀን በውስጠኛው ቆዳ ውስጥ በዛ ያለ ደም በማጠራቀም ዕንቁላሉን ለመቀበል ይሰናዳል። ይህ ደም ዕንቁላሉ ልጅ ሆኖ የሚያድግ ከሆነ ለሕፃኑ የሚሆን ምግብና አየር ይዟል። ልጅ ለመሆን የሚችለው ከወንዴው የዘር ሴል [ስፐርም] ጋር የተዋሐደው ዕንቁላል ብቻ ነው። እንቁላሉ ከእንቁላል ዕጢ ማመንጫ ልክ እንደወጣ በእናትና በአባት መካከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢከናወንና ከብዙ ሚሊዮን የወንድ የአባለ ዘር ብልት የተጠራቀሙት የዘር ሴሎች [ስፐርም] በሴትየዋ የአባለ ዘር ብልት ውስጥ አድርጎ ወደ ማህፀን ማስተላለፊያው ቱቦ መሳይ ያልፋል። [ፍሎፒያን ቲዩብ] ሁለት የተለያዩ ሴሎች ሲገናኙ በመዋሓድ ፅንስ ይጀምራል። ይህም ፈርትላይዜሽን ተፈፀመ ማለት ነው።

የዕንቁላሉ ሴል ለፅንስ (ለፍሬ) ዝግጁ ሆኖ የሚቆየው የማመንጫ ቦታውን ትቶ ከመጣ ለሁለት ቀን ጊዜ ያህል ብቻ ነው። በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለፍሬ የሚያበቃ ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ካልተደረገ በቱቦው አድርጎ ወደ ማህፀን ይደርስና ከዚያ በኋላ በምዕራፍ 3 እንደተነጋገርነው ወደ ውጪ ይወጣል። በማህፀን ውስጠኛው ክፍል የተጠራቀመው ደም እንቁላሉ ከእንቁላል ማኩረቻ (እቫሪስ) ከወጣ በኋላ ከአሥር እስከ አሥራ አራት ቀን ድረስ ይቆያል።

(የዕንቁላሉ ሴል) ኦቮም ፅንስ መሆን እንዲችል ከዕንቁላል ዕጢ ማመንጫው ወደ ማህፀኑ በሚወስደው ማስተላለፊያ ቱቦ [ፍሎፒያን ቲዩብ] ውስጥ ያለፈና ገና ሕይወት እያለው የወንዴው የዘር ሴል እንዲደርስ ያስፈልጋል። የወንዴው የዘር ሴል (ስፐርም) በማህፀኑ ታችኛው አንገት በመሰለው ጫፍ [ሰርቪክስ] አድርጎ በማህፀን ውስጥ አልፎ ወደ እዚህ ማስተላለፊያ ቱቦ (ፍሎፒያን ቲዩብ) እንዲደርስና እንቁላሉዋን እንዲገናኛት የሚረዳው ረጅሙ ጭራ ነው። እነዚህ ሴሎች ከተዋሃዱ በኋላ ዕንቁላሉ ወደ ማህፀን ይገባና ጉዞውን ቀጥሎ በተሰናዳላት ለበላሳ ውስጠኛ ሽፋን ላይ በመጣበቅ ማደግ ይጀምራል። የዕንቁላሉ ሴል ከማህፀኑ ጋር የተጣበቀበት እንጨት መሰል ዕትብት (አምብሊካል ኮርድ) ወደተባለው ጅማት መሰል ነገር ያድጋል። እርሱም የሚገናኘው የእንግዴ ልጅ (ፕላሴንታ) ከተባለው ሥር መሰል ጋር ነው።

የእናትየው ደም ከእንግዴ ልጁ ጋር የተገናኘ ስለሆነ በማህፀን ውስጥ የሚያድገው ሕፃን ምግብና አየር ከእናትየው ደም ያገኛል።

ማህፀን በማደግ ላይ ያለውን ዕንቁላል ወይም ፅንሱን ኢምብርዩ ይንከባከባል። ፅንሱ ባደገ ቁጥር ማህፀኑ አየተለጠጠ ይመጣል። ለተሻለ ጥበቃም ፅንሱ (ፈሳሽ ነገር በተሞላበት ከረጢት አምኒዮቲክ ፍሉይድ መሳይ ነገር ውስጥ ማደግ ይጀምራል። ይከበባል። ይህም እናትየው ከቦታ ቦታ በምትንቀሳቀስበት ጊዜ ህፃኑን ጉዳት እንዳያደርስበት ይጠብቀዋል።

የዕንቁላሉ ሴል ከወንዴው የዘር ሴል ጋር ከተገናኘ 3 ሳምንት በኋላ የሕፃኑ ልብ መምታት አንጎሉም መሥራት ይጀምራል። በስምንተኛው ሳምንት ሁለት ተኩል ሴንቲ ሜትር ያህል ርዝመት ብቻ ይኖረዋል። ሆኖም በዚሁ ጊዜ ከመጀመሪያ ርዝመቱ በ175 ጊዜ አድጎአል። በአሥራ ሁለት ሳምንቱም ከንዱ ጭኑ እጁና እግሩ እንዲሁም ጥፍሮቹ ይፈጠራሉ።

በአሥራ ስድስት ሳምንቱ ሕፃኑ የአሥራ አምስት ሴንቲ ሜትር ርዝመት ይኖረዋል በዚሁም ደረጃ ለእናትየው እስከሚሰማት ድረስ መንቀሳቀስ ይጀምራል። በሃያ ስምንት ሣምንቱ ሕፃኑ ሠላሳ አንድ ሴንቲ ሜትር ያህል ይረዝምና ዓይኑ ይከፈታል ጠጉሩም መብቀል ይጀምራል።

በ256 ቀናት ወይም በዘጠኝ ወር በግምት 50 ሴንቲ ሜትር ያህል ይረዝማል 3 ኪሎ ግራም ያህል ይመዝናል። አሁን ለመወለድ ዝግጁ ነው።

በብዙ ሁኔታዎች የእናትየው የማህፀንና የብልት ጡንቻዎች ስለሚዘረጉና የዳሌም አጥንቶች ስለሚሰፉ ሕፃኑን በተለመደው መንገድ እንዲወለድ ያስችሉታል። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ እናትየው በጣም ትንሽ ወይም አመቺ ያልሆነ ቅርፅ ካላት ልጅዋን ካለ እርዳታ ለመውለድ በጣም አስቸጋሪ ይሆንባታል። ስለዚህም በእርግዝናዋ ወራት ሁሉን ነገር ደህና መሆኑን ለማረጋገጥ ሐኪም ማማከር ጠቃሚ ነው። ቢቻል ሁሉ ነገር በንፅሕና በሚጠበቅበትና ቢያስፈልግም ተጨማሪ እርዳታ በሚሰጥበት ሐኪም ቤት መውለድ መልካም ነው።

እርጉዝ ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ይታወቃታል። ምክንያቱም የማህፀኗ ጡንቻዎች ሲወጣጠሩና ሲኮማተሩ እንደገናም ለቀቅ ሲያደርጋት ስለሚሰማት ነው። በዚህ ጊዜ እናትየው ምጥ (ሌበር) ይሏታል ይባላል። ጡንቻዎችዋ ሕፃኑን ወደ (መውለጃው ቦይ ወይም ብልት) ይገፉታል። በመጀመሪያ ይህ መኮማተርና መላላት ከ 15 እስከ 20 ደቂቃ ይቆይና ከዛም በመካከሉ ፋታ ይሰጣል።

የምጡ ሕመም በየሁለቱ ደቂቃ ፍጥነቱ ይጨምርና ሕፃኑን የሚጠብቀው (ፈሳሽ የተሞላው አሞኒናቲክ ሳክ ከረጢት) መሳይ ነገር ተቀዶ የሕፃኑ ጭንቅላት ይወጣል። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ሰውነቱ ይከተላል። አንድ ጊዜ ከእናትየው ማህፀን ውስጥ ሕፃኑ ከወጣ መተንፈስ ይኖርበታል። አየር ወደ ሳንባው ሲገባና ለመጀመሪያ ጊዜ ለመተንፈስ ሲል አብዛኛውን ጊዜ በኃይል ይጮኻል። በዚህን ጊዜ ሕይወት ያለው ጤንማ ልጅ እንደወለደች ስለምታውቅ ጩኸቱ እናትየውን የሚያስደስት ድምፅ ነው።

ሕፃኑ እንደተወለደ ዶክተሩ ወዲያውኑ ለዘጠኝ ወር ለሕፃኑ ምግብና አየር ይሰጠው የነበረውን እትብት (አምፕሊካል ኮርድ) ይቆርጠዋል። በሁለቱም ጫፍ ያለውን በሚገባ አስሮ ያስወግድና ለመድረቅ በሚያመች መንገድ ትንሽ ጫፍ ከልጁ ጋር ያስቀራል። እምብርቱም (ኔቮል) እትብቱ ደርቆ ከወደቀ በኋላ የሚቀር ምልክት ነው።

ይህ እግዚአብሔር የደነገገው የሰው ዘር አፈጣጠርና አኗኗር አስደናቂ ሥራ ነው። እነዚያ በዓይን እንኳ መታየት የማይችሉ ትንንሽ ሴሎች በዘጠኝ ወር ውስጥ አድገው እንዴት ቆንጆ ልጅ እንደሚሆኑ የሚያስደንቅ ነገር አይደለምን!

ልጁ እንደተወለደ የእንግዴ ልጁ (ፕላሴንታ) በእናትየው (ብልት አድርጎ ወደ ውጪ ይወጣል)። የእንግዴ ልጁ በሙሉ መውጣት ስላለበት ይህንን ለማወቅ ከሁሉ የተሻለው ሐኪም ነው። ከዚህ በኋላ ለሁለት ሳምንት ያህል እናትየው የደም ፈሳሽ ይኖራታል። ተነሥታ ልጁን መንከባከብ ብትጀምር በቶሎ እንደ ድሮዋ ልትሆን ትችላለች ነገር ግን ጠንካራ እስከምትሆን ድረስ ከባድ ሥራ መሥራት አይኖርባትም።

ስለዚህ ሁኔታ አንዳንድ ጥያቄዎች እንደሚኖራችሁ አያጠራጥርም። ምን አልባት አንዳንድ ጊዜ ወንድ ልጅ ሌላም ጊዜ ሴት ልጅ እንዴት እንደሚወለድ ትደነቁ ይሆናል። ስለዚህ ነገር ልንገራችሁ። የልጁ ፆታ የሚለየው ወዲያው የዕንቁላሉ ሴልና የወንዱው የዘር ሴል (እስፐርምና አቨም) እንደተገናኙ ነው። በእነዚህ ሴሎች ውስጥ ሀብለ በራሂ (ክሮሞዞምስ) የሚባሉ ረቂቅ ነገሮች አሉ። የዕንቁላሉ ሴል አንድ ዓይነት ክሮሞዞምስ ሲኖሩት የወንዱ የዘር ሴል (ስፐርም) ግን ሁለት ዓይነት ክሮሞዞምስ አሉት። ሰ የሴቷ ሲሆን ሱ ደግሞ የወንዱ ነው እንበል። የወንዱ

የዘር ሴል (ስፐርም) ሰ ክሮሞዞምስ ከያዘ ጽንሱ ሴት ይሆናል። የወንዱው የዘር ሴል (ስፐርም) ሱ ክሮሞዞምስ ከያዘ ጽንሱ ወንድ ይሆናል። በሆድ ውስጥ ያለው ሕፃን ወንድ ወይም ሴት ለመሆኑ ማወቂያ መንገድ የለም። ይህ የሚታወቀው በሚወለድበት ጊዜ ብቻ ነው። ሰውም ይህንን መቆጣጠርና መቀየር የሚችልበት መንገድ የለም።

ስለመንትያዎችስ አስባችሁ ታውቃላችሁ? አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ (አይደንቲካል) መንትያ ልጆች ይወለዳሉ። እነርሱም ሁለቱም ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆች ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ዓይነት መልክ አላቸው። ይህ የሚሆነው ከአንድ እንቁላል ስለተፈጠሩ ነው እንቁላልዋ ከወንዱ የዘር ሴል (ስፐርም) ጋር ከተገናኘች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለሁለት ይከፈላል። ከዛ በኋላም ሁለቱም እያንዳንዳቸው ለየብቻ ልጅ እየሆኑ ያድጋሉ። ሁለቱም ከአንድ የዕንቁላል ሴል ስለተፈጠሩ አንድ ዓይነት ባሕሪይ ይኖራቸዋል። አንድ ዓይነት የሆኑትም በዚሁ ምክንያት ነው።

ከሁለት የተለያየ የዕንቁላል ሴሎች ስለተፈጠሩ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሴትዮዋ ሁለት የዕንቁላል ሴሎች ይኖራትና ሁለቱም ዕንቁላሎች ከተለያየ የወነዱ የዘር ሴል (ስፐርም) ጋር ሲገናኙ ሁለት ልጆች ይፈጠራሉ ታዲያ እነዚህ መንትዮች ከተለያዩ እንቁላሎችና የወንድ የዘር ሴሎች (ስፐርም) ስለተፈጠሩ በአንድ ጊዜ የተወለዱ ሁለት (የተለያዩ ሕፃናት) ይሆናሉ። እነርሱም ሁለቱም ሴቶች ወይም ወንዶች ወይም ደግሞ አንድ ወንድና ሴት ሊሆኑ ይችላሉ።

የልጅ አወላለድ ተአምርና እውነት በምንመለከትበት ጊዜ አሁን እናንተ ለምን በፍጥነት ማደግና በመለወጥ ላይ እንደምትገኙ ለመገንዘብ እንደሚረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሔር እናት ወይም አባት በምትሆኑበት ጊዜ እያዘጋጃችሁ እንደሆነ ታያላችሁ። ጋብቻ በምትመሠርቱበት ወቅት ጤነኛ ወላጅ ለመሆን እንድትችሉ ሰውነታችሁን እያዘጋጀ ነው። አንዳንድ ጊዜ ለተቀራኒ ፆታ ፍቅር ይኖራችሁና ምናልባት በግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመሞከከር ትፈልጉ ይሆናል። እስከመጨረሻ በምታድጉበትና በምትረዝሙበት ጊዜ በአካል ለወላጅነት ዝግጁ መሆናችሁ ዕውነት ነው። ሆኖም በዕድገት ውስጥ የሚጠቃለሉ ብዙ ነገሮች አሉ። እግዚአብሔር በአእምሮአችሁ በስሜታችሁ ከሕብረተሰቡ ጋር ባላችሁ ግንኙነትም በተጨማሪ እንድታድጉ ይፈልጋል። አግብታችሁ ትልቅ ሰው ከመሆናችሁ በፊት በቅድሚያ ብዙ ነገር መማር ያስፈልጋችኋል። በሚቀጥሉት ምዕራፎች እነዚህን የተለያዩ የዕድገት ዓይነቶች እንወያይባቸዋልን።

ለመምህራን የሚረዳ፤

የሚጠና ጥቅስ፡- ዘፍጥ. 1፡26-31፥ 2፡18-25፥ 4፡1፥ 25 ይህንን ክፍል ስታስተምሩ ስለ ሰው ዘር አፈጣጠር ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድና ውበት ለመመልከት ምክሩና ለተማሪዎቹ የእግዚአብሔርን ታላቅ ጥበብ ከምሥጋና ጋር ግለጹላቸው። አካላችንን በድንቅ ሁኔታ ስለፈጠረ ይህንን የትምህርት ክፍለ ጊዜ እግዚአብሔርን በማመስገን ልትጨርሱት ትችላላችሁ።

ክፍል 3
ራስን መቀበል

ምዕራፍ 5
እራስህን እንደ አንተነትህ መቀበልን ማወቅ

ዓላማ፡ - እግዚአብሔር ወጣቶችን በዚህ ዓይነት መንገድ የፈጠራቸው እርሱ እንዲህ እንዲሆኑ ስለፈለገ መሆኑን እንዲረዱ ለማድረግነው። ክርስቶስን በግል እንዲያውቁት ለማድረግና እርሱንም ለማስደሰት በእርሱም ታይል መደገፍ እንዳለባቸው ለማድረግ

የሚጠና ጥቅስ፡ - እግዚአብሔር ለሙሴ አለው የሰውን አፍ የፈጠረ ማን ነው? ዲዳስ ደንቆሮስ የሚያይስ ዕውርስ ያደረገ ማን ነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ዘዳ. 4፡11

መግቢያ

ግርታ ተጨንቃለች በከፍል ውስጥ የሒሳብ አስተማሪ ጥያቄ ሲጠይቃት መመለስ አልቻለችም። ከጎኗ የምትቀመጠው ኤልሳቤጥም ቀስ ብላ ደደብ ብላ ሰድባታለች። እንዲሁም ትላንትና ከትምህርት ቤት ስትመለስ ጨው መግዛት ስለረሳች እናትዋ ደግሞ ተቆጥታ አህያ ብላ አዋረደቻት።

ያ ብቻ አይደለም። ሕፃን ልጅ ሳለች እሳት ስላቃጠላት ግንባሯ ላይ ጠባሳ አለ። ስለዚህም እንደሌሎቹ ልጃገረዶች ቆንጆ አይደለሁም ብላ ትጨነቃለች። ሁሉም ሰው የሚያየው ቦታ ላይ ጠባሳ ስላላት በጣም ትጠላዋለች! ልክ እንደ መኪና መብራት የሚያበራ ወይም የሚታይ ሆኖ ይሰማታል። አንዳንድ ጊዜ ሰው ሁሉ የጠላት ይመስላታል። አገር ጥላ ብትጠፋ ደስ ይላታል። ግርታን እንዲህ እንዲሰማት ያደረጋት ምንድን ነው?

ትምህርት፡ -

ምን አልባት እናንተም በአሁኑ ጊዜ እንደ ግርታ ታስቡ ይሆናል? በመስተዋት ራሳችሁን አይታችሁ አፍንጫዬ ቀጠን ቢል ጸጉሬ ለስለስ ቢል ብላችሁ ትመኙ ይሆን? ምን አልባትም እግሬ ተለቀ ቁመቴም ረዘመ ወይም አጠረ ትሉ ይሆናል) ምን አልባትም በጣም ወፈርኩ ወይም በጣም ከሳሁ ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። ብዙ ገንዘብ ወይም የተሻለ ልብስ እንዲኖራችሁ ትመኛላችሁ? ይህ በእናንተ ዕድሜ ያለ ማንኛውም ወንድ ወይም ሴት የሚሰማው ነገር ነው።

ብዙ ወጣቶች በሌሎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያምኑበት 3 ጉዳዮች አሉ። የመጀመሪያው ውብት ነው። ወንድ ወይም ሴት ብትሆኑም መልከ መልካም መሆንን ትፈልጋላችሁ። በአእምሮአችሁ ምን መምሰል እንደምትፈልጉ ከቀረፃችሁት ሥዕል ጋር አትመሳሰሉ ይሆናል። 80/ከመቶ የሚያህሉ ወጣቶች ባላቸው መልክ የማይረኩ መሆኑ ይገመታል።

ሁለተኛም ማንኛውም ወጣት በትምህርት ቤቱ ጥሩ ለመሥራትና የተሻለ ውጤትም ለማምጣት ይፈልጋል። በትምህርቱ ነበዝ መሆንም ይመኛል፥ ከክፍሉም ደግሞ አንደኛ የመውጣት ሃሣብ አለው።

ሦስተኛ በጓደኞቹ ዘንድ ተቀባይነትን ለማትረፍ በጣም አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበት ነገር ቢኖር ገንዘብ ነው። ወጣቶች አለባበሳቸው የተለየ እንዲሆንና ሌሎች ያላቸውን ማንኛውም ነገር እነርሱም ደግሞ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ።

እነዚህ ሦስቱ ነገሮች ለወጣቶች በጣም አስፈላጊ ነገሮች ሊሆኑ ስለሚችሉ እነዚህ ካልተሟሉላቸው ተስፋ ቢስና ዘወትር ተጨናቂዎች ይሆናሉ።

አናንተም እራሳችሁ እግዚአብሔር በዚህ መንገድ እንደፈጠራችሁ መቀበል አቅቶአችሁ በዚህ ዓይነት ወጥመድ ውስጥ ከወደቃችሁ ብዙ ዓይነት ምልክቶች ይከተላሉ። እራሳችሁን ብቻ የምትመለከቱ አሳባችሁም በእናንተም ሁኔታ ላይ የሚያተኩር ብቻ ይሆናል። በእግዚአብሔር ከመታመን ፋንታ ሁሉን ነገር በራሳችሁ ኃይል ለመሥራት ትፈልጋላችሁ። ብዙ ጊዜም ለችግራችሁ መንሥዔው በዙሪያችሁ የሚገኙት ሰዎች ሁሉ እንደሆኑ ቆጥራችሁ ለመናገር ትፈልጋላችሁ። በወላጆቻችሁ ትማረራላችሁ፥ ደስተኛ ባለመሆናችሁም እነርሱን ትወቅሳላችሁ። የአስተማሪ፥ የትምህርት ቤት፥ ወይም የመንግሥት ስህተት መስሎ ይታያችኋል። ከጊዜ በኋላ ብትፀፀቱም እንኳ እነዚህን ሁሉ መውቀስና ስለ እነርሱም የማይገባና ደግ ያልሆነ ነገር መናገር ትጀምራላችሁ።

አንዳንድ ሁኔታዎች ካለፉ በኋላ ስላደረጋችሁት ነገር ሁሉ እራሳችሁን ትጠላላችሁ፥ ሳታስቡ አንድ ነገር ታደርጉና ወይም ትናገሩና ካለፈ በኋላ በነገሩ ታዝኑ ይሆናል። በጓደኞቻችሁም አንድ ነገር ለማግኘት ትፈልጉና ካላገኛችሁት ግን ይቆጫችሁ ይሆናል። ይህም ከወላጆቻችሁ ከእህቶቻችሁ ወይም ከወንድሞቻችሁ እንዲሁም ከጓደኞቻችሁና ከማንኛውም ሰው ጋር ያላችሁን ግንኙነት ያበላሽባችኋል።

ከዚህ በኋላ እራሳችሁን በዕድሜ እኩያችሁ ከሆኑ ከሌሎች ልጆች ጋር ማወዳደር ትጀምራላችሁ። ያላቸውን ነገሮች ትመለከታላችሁ። በትምህርት ቤት ስላገኙትም ውጤት ትሰማላችሁ። መልከ መልካም መሆናቸው ዝናን እንዳተረፈላቸው ታያላችሁ። እነዚህ ሁሉ ነገሮች እንደነርሱ ለማድረግ እንድትሞክሩ ያደርጋችኋል። እንደ ሌላ ሰው ለመሆን ደካማ ጎናችሁን ለመደበቅ ትሞክራላችሁ። ይህ አጉልና እውነተኛ ያልሆነ ሰው እንድትሆኑ ያደርጋችኋል። በእነዚህ ሁሉ ድርጊት መካከል አንድ ነገር ይደሰትባችሁ ይሆናል። ይኸውም መልካም ጠባይና ጠንካራ ጎኖች ስላላችሁ ከጓደኞቻችሁ በላይ እንደሆናችሁ ይሰማችሁ ይሆናል። ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወዳድራችሁ ለማሸነፍና በታዋቂነት የመጀመሪያውን ደረጃ ለመያዝ የሚያበቃችሁን ይህን ጠንካራ ጎናችሁን ለማጎልበት ትጥሩ ይሆናል። በስፖርትም ሆነ በክፍል ውስጥ ያሉትን ተወዳዳሪዎቻችሁን ለመጣልና ለማሸነፍ እራሳችሁን ጠንካራ በሆነ የጠባይና የሥራ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ትጥሩ ይሆናል። በዚህ ሁሉ ሙከራችሁ በነገሩ ማንም ቢጎዳም እንኳ ዓላማችሁ ታዋቂነትንና ውጤታማነትን ለማትረፍ ነው።

በአሁኑ ጊዜ እንዲህ በመሰለ መጨረሻ በሌለው ውድድር ውስጥ አላችሁበትን? የብሽቀት ስሜት ተሰምቶአችሁ መውጫ መንገድ ትፈልጋላችሁን? እራሳችሁን ሳይሆን ሌላውን ሰው ለመምሰል የምታደርጉት ሙከራ ካለነፃነት እንድትኖሩ ስላደረጋችሁ ሰልችቶአችኋልን? ይህ እንዲህ ከሆነ

የሚከተሉት አንቀጾች በጥንቃቄ አንብቡና በእግዚአብሔር እርዳታ የተሰጡትን ምክሮች ለመጠቀም ሞክሩ።

በመጀመሪያ ኤር. 31፡3 ን አብረን እንመልከት «በዘላለም ፍቅር ወድጀሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ፍቅር ሳብሁሽ» እግዚአብሔር እናንተን እንደ እናንተነታችሁ እንደወደዳችሁ ታውቃላችሁ። ለእናንተ ያለው ፍቅር ዘላለማዊ ስለሆነ አይለዋወጥም። ለእናንተ ያለው ፍቅር በሠራችሁት ሥራ በምታደርጉት ነገር ወደፊትም በምታደርጉት እንዳልተወሰነ ታውቃላችሁ። «መለወጥ በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ» ይላል (ቢያዕ. 1፡17)። ፍቅሩ የማይለዋወጥና የማይቀዘቅዝ ነው። እግዚአብሔር እናንተን ለመውደድ መረጠ ፍቅሩንም ልጁን ጌታ ኢየሱስን ለኃጢአታችን እንዲሞትና ከሞትም እንዲነሣ ሕይወትም እንዲሰጣችሁ አሳልፎ በመስጠት ገለጠው። በክርስቶስ በማመን ኃጢአታችሁንም በመናዘዝ ይቅር ልትባሉና የእግዚአብሔር ልጆች ልትሆኑ ትችላላችሁ። በሕይወታችሁ እንዲናርና እርሱንም ደስ የሚያሰኝ ኑሮ ለመኖር ኃይልና ብርታት እንድታገኙ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣችኋል።

እናንት ወጣቶች የምመክራችሁ ምክር አለኝና ልብ ብላችሁ ተከታተሉኝ። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኛችሁ አድርጋችሁ ካልተቀበላችሁ አሁን ልትቀበሉት ትችላላችሁ። እራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ በጸሎት ለእግዚአብሔር ንገሩት። በዚህ ዓይነት ኑሮን መግፋት እንደደከማችሁ ግለፁለት። ስለሠራችኋቸው አያሌ መጥፎ ነገሮች ሁሉ ይቅርታን ጠይቁት ከዚያም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታችሁ አዳኝና ጌታ እንዲሆን ጋብዙት። ከዚህም በኋላ ይህንን ማድረጋችሁን ለአንዳንድ ሰዎች ንገሩና እነርሱንም የእምነታችሁን አቋም ይፋ የምታደርጉበትን መንገድ እንዲያሳዩአችሁ ድጋፋቸውን መጠየቅ ትችላላችሁ።

አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ልጁን ከተቀበላችሁት በኋላ ከባድ የሆነባችሁን ሁኔታዎች ሁሉ እንድታሸንፉ ሊረዳችሁ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነው። እንደገናም ብትወድቁ ወይም ብትሳሳቱ ይቅርታ ከጠየቃችሁት ይቅር ሊላችሁና ልባችሁንም አዲስ አድርጎ ሊያጠራው ዝግጁ ነው። (1ኛዮሐ. 1፡7-10)

ምናልባት ክርስቶስን ከዚህ በፊት ተቀብላችሁት ሊሆን ይችላል፥ ነገር ግን እራሳችሁን ከላይ በተጠቀሱት ልማዶች ውስጥ አጥላልታችሁ ይሆናል። እግዚአብሔርን ይቅር እንዲላችሁና እንደገናም የቀድሞውን ግንኙነት እንዲመልስላችሁ ጠይቁት። ስለችግራችሁና እንዴትም መውጣት እንደምትችሉ ጥበብ እንዲሰጣችሁ ለእርሱ በፀሎት መንገር ትችላላችሁ (ያዕ. 1፡2-4)

ከዚያም ሕይወታችሁን በቅንነት መርምሩ፥ ችግሮችህን በግልጽ መመልከት ይጠቅማል። ተቀመጥና ስለራስህ የማትወደውን ነገር ለመጻፍ ሞክር። የምትጽፈውን ዝርዝር ለሁለት ክፈለው። በአንደኛው ዝርዝር መለወጥ የሚችሉትን ነገሮች ጻፍ። በሁለተኛውም ዝርዝር መለወጥ የማይቻሉትን ነገሮች ጻፍ። ከዚህ በኋላ የጻፋችሁትን ዝርዝር በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አቅርቡት። ስለእያንዳንዱ ጉዳይ ንገሩት። መለወጥ የሚገባቸውን ነገሮች እንዲለወጡ ለማድረግ ኃይል እንዲሰጣችሁ ጠይቁት። እንዲህ ብላችሁ ጽፋችሁ ይሆናል። «አንድ ነገር እንድሠራ ሰው በሚያዘኝ ጊዜ እናደዳለሁ» ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ንዴት የሚናገር ክፍል ፈልጉና እግዚአብሔር ምን እንደሚል ተመልከቱ። ምን ጥቅስ አገኛችሁ? እኔ ኤፌሶን 4፡31-32 አስባለሁ። እግዚአብሔር ንዴትን አስወግደን እርስ በእርሳችን ደግ ሥራ እንድንሠራ ይነግረናል።

ጌታ መታዘዝ የምንችልበትን ኃይል ካልሰጠን በስተቀር አንድን ነገር እንድንሠራ አይነግረንም። ስለዚህም ሊያሠራችሁ ስለሚችለው ኃይል እርሱን መጠየቅ ትችላላችሁ።

መለወጥ ስለማትችሉትስ ዝርዝር ምን ታደርጋላችሁ? ምንአልባትም ልክ እንደ ማርታ በፈታችሁ ላይ የምትጠሉት ጠባሳ ይኖራችሁ ይሆናል። ያ ልትለውጡት የማትችሉት ነገር ነው። እግዚአብሔር ለእናንተ ልዩ ዕቅድ ስላለው እንዲህ እንድትሆኑ እንደፈቀደ በማስተዋል እናንተም ይህንን መቀበል እንድትችሉ ፀጋውን እንዲሰጣችሁ ጠይቁት። እግዚአብሔር ለእናንተ ያለውን ልዩ ዕቅድ ታውቃላችሁን? የእርሱ ትልቁ ዕቅድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድተመስሉ ማድረግ ነው (ሮሜ. 8:29) እግዚአብሔር በውስጣዊ ሕይወታችሁ መልካም ጠባይ እንዲኖራችሁ ይፈልጋል። እርሱ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግስት፥ በጎነት፥ ደግነት፥ ታማኝነት፥ ጨዋነት፥ እራስን መቆጣጠር እንዲኖራችሁ ይፈልጋል። (ገላ. 2:22) እነዚህ ነገሮች ከውጫዊ ውበት ሁሉ ለእርሱ የከበሩ ናቸው። «ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል።» (1ኛሳሙ. 16:7)

ለከብሩ ሲባል ንጹሕና ጠፈፍ ያልን ሆነን መታየትን እንፈልጋለን። ነገር ግን ለጥቃቅን ውጫዊ መልካችን መጨነቅ የለብንም። ስለውስጣዊ ሰብእናችንና እግዚአብሔርም እንዴት እንደሚያየን በበለጠ ማሰብ የሚገባን ስለዚህ ነው። በአንደኛ ጴጥ. 3:3-4 እንዲህ ይላል «ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና ወርቅንም በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ የውጪ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ»

እንዲህ ዓይነት ባሕሪይ ለማዳበር በአንድ ጊዜ የሚቻል እንዳልሆነ አስተውሉ። እንዲህ የሚል የድሮ አባባል አለ:- «ሮም በአንድ ቀን አልተገነባችም» ሮም አንዲት ታላቅ ከተማ ናት። ስለዚህ በአንድ ቀን የተገነባች ይመስላችኋልን? ስለዚህ በራሳችሁ ተስፋ አትቁረጡ። እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ ምን ያህል መለወጥ እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃል። አንዳንዴ ወደ ኋላ ታፈገፍጉ ይሆናል። በርቱ እግዚአብሔር በሕይወታችሁ እየሠራ ነው፥ ብትተባበሩት ሳያቋርጥ ሊረዳችሁ ይወዳል። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል «በእናንተ መልካም ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈፅመው ይህን ተረድቻለሁና» (ፊል. 1:6)። እግዚአብሔር ውስጣዊውን ጠባይ በእናንተ ለመሥራት ይፈልጋል። ትፈቅዱለታላችሁን?

ለመምህራን የሚረዳ:-

የሚጠና መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:- ኤር 31:3፥ ያዕ. 1:17፥ ዮሐ. 3:16 ኤፌ. 1:13-14፥ ሮሜ 10:9፥10፥ 1ኛዮሐ 1:7-10፥ ሮሜ 8:29፥ ገላ. 2:22፥ 1ኛጴጥ 3:3-4፥ ፊልጵ. 1:6

ተማሪዎቹ ስለራሳቸው የሚሏቸውን ነገሮች እንዲነጋገሩባቸውና እንዲፅፏቸውም ፍቀዱላቸው። በእነዚህ ጉዳዮች በግል ጸሎት እንዲያደርጉ ጊዜ ስጧቸው። በክፍሉ ካሉት ልጆች ክርስቶስን ጌታውና አዳኙ አድርጎ ያልተቀበለውን ለመርዳት ተዘጋጁ። የደህንነትን መንገድ የሚያመለክቱ ጥቅሶች እንደምታውቁ እርግጠኞች ሁኑ።

ምዕራፍ 6
በወጣትነት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮች

ዓላማ፡- በተለይ ከ12 እስከ 15 ዕድሜ ውስጥ ያሉትን ወጣቶች የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመጠቆምና ወደ መፍትሔው ለመምራት ነው።

የሚጠና ጥቅስ፡- «እግዚአብሔር ጽድቅንና ፍርድን ቅንነትንና መልካም መንገድን ሁሉ እንድታስተውል ያደርጋል። ጥበብ ወደ ልብህ ትገባለችና ዕውቀትም ነፍስህን ደስ ታሰኛለችና» ምሳሌ 2፡9-10።

መግቢያ

ሂሩት በጣም አዝናለች። በዚህ ሳምንት ምንም ነገር አልሆነላትም። ሰኞ ዕለት የወደቀችበት የሳይንስ ፈተና አለ። ያኔም ኤልሳቤጥ ደግሞ ቆንጆ ሹራብ ለብሳ ወደ ትምህርት ቤት መጥታ ነበርና ሂሩት እንዲህ ብላ አሰበች። «ልክ በጌጥ እንደተሽቀረቀረ ፈረስ ለብሳ መምጣቷ ምን ማለቷ ነው? አዮ! በከንቱ መውረግረግ! ለካ ፍቅሩ እርሷን መስደቡ! ደግ አድርጓል! ይገባታል!» በማለት ሂሩት የቅንዓት ስሜት አደረባት።

ዛሬ ደግሞ ሂሩት በክፍሏ ልጆች ፊት ወጥታ የሂሳብ ጥያቄ በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንድትፅፍ ከማድረግ የባሰ ነገር ይኖር ይሆን? በመቀጠልም ተአምራት እንዲህ ብሎ በሹክሹክታ ተናገረ፡- «አሁን ሴቶች ስለ ሂሳብ ምን ያውቁና ነው?» ከዛም በክፍሉ ያሉት ወንዶች ልጆች ሁሉ ሳቁባት። እርሷም በጣም አፈረች።

ትምህርት

ለውጥ ለውጥ! አሁን እናንተ ብዙ ለውጥ በሚካሄድበት ዘመን ላይ ናችሁ። ይህም ሊረብሻችሁ ይችላል። አሁን የሚያስጨንቋችሁ አንዳንድ ነገሮችስ ምንድን ናቸው?

በእናንተ ዕድሜ የሚገኙት አንዳንድ ወጣቶች በጣም ከማደጋቸው በላይ ከእንግዲህ ሰውነታቸው ስላደገባቸው ለእነርሱ አዲስ ነገር ይሆንባቸዋል። «ጤነኛ የሆንኩ አይመስለኝም» ብሎ ማርቆስ ያሰላስላል። «እግሬ ከራሴ የራቀ ይመስላል!» ምን አልባት አንተም እንደ ማርቆስ ታስብ ይሆናል። ቅርፅህና ቁመትህ አዲስ ነገር ስለሆነብህ በእራስህ እንድታተኩርና እፍረት እንዲሰማህ ያደርግሃል። በአንድ ጊዜም ስላደግህ አንዳንድ ጊዜ ይደክምህና ብዙ መኝታ ትፈልግ ይሆናል። ስለሰውነትህ እድገት ትእግሥት ይኑርህ። እየተፈፀሙ ያሉትን ዕድገቶች ለማሰብ በመሞከር በቂ እንቅልፍና ጥሩ ተስማሚ ምግብ በመብላት ሰውነትህን ተንከባከብ። ሰውንትህ ማደግ የሚገባውን ያህል እንዲያድግ ፍራፍሬ፣ ወተት፣ ሥጋ፣ ዕንቁላልና አትክልት መመገብ ያስፈግሃል። በአካባቢህ የሚገኙትን ምግቦች በተመጣጠነ ሁኔታ መመገብ ይጠቅማል።

ደማቅ ቀለማት ያላቸው ጥሩ ጥሩ ልብሶች ትወድ ይሆናል፣ የሚያምሩ አይደሉምን? ምን አልባትም ሞቅ ያለ ሙዚቃ ይማርክህ ይሆናል።

ካለፈው የሕይወት ዘመንህ አብዛኛውን እንዲሁ ነው ያሳለፍከው። አንተን የሚመለከቱ ነገሮችን የወሰኑልህ ወላጆችህ ነበሩ፣ ይህም ማለት፡- የምትለብሰውን የምትመገበውንና የምትሄድበትን ሥፍራ ሁሉ እንዲህ የመሳሰሉትን ነገሮች ይወስኑልህ ነበር። አሁን ግን የራስህን ውሳኔ ለማድረግ

ትፈልጋለህ። ምክንያቱም ዕድገትን አላደተሃል። በራስህ የእኗኗር ስልት መኖር ትፈልጋለህ። በእውነት ስለራስህ ማወቅ ትመኛለህ። አሁን አዲስ ሀሳቦችን፣ ዘዴዎችን፣ መንገዶችን፣ መመርመር ትጀምራለህ። ድሮ ከምንም የማትቆጥረውን ነገር አሁን ከጓደኞችህ ጋር ሆነህ ማሰብ ትጀምራለህ።

ጫጩት ከተፈጠረበትና ከአደጋም ከሚጠብቀው የዕንቁላል ቅርፊት እራሱን ነፃ ለማውጣት ሲታገል አደተሃል። አሁን የሚገባውን ያህል ስላደገ የዕንቁላሉ ቅርፊት አያስፈልገውም። ይህ እናንተን ይመስላል: እናንተም አሁን አድጋችሁ ትልቅ ሰው ለመሆን እራሳችሁን ከሕፃንነት ለማላቀቅ የምትታገሉበትና የምትፍጨረጨሩበት ጊዜ ነው። ጫጩቱ ወዲያው እራሱን ከቅርፊቱ ሊያላቅቅ ይችላል። ለእናንተ ግን ጊዜ ይወስድባችኋል። አንዳንድ ወጣት ልጆች በዚህ ጊዜ በእናትና በአባታቸው ያምፃሉ ይጣላሉ፣ ምክንያቱም አባትና እናታቸው «የዕንቁላሉ ቅርፊት» ስለሚመስሏቸው ነው፣ ነገር ግን ተገንዝባችሁ ከሆነ፣ ሕፃንነትን ለማስወገድ እየሞከራችሁ ነው።

ይህ ሊጎዳ ይችላል፣ የአካል ጉዳት ሳይሆን ነገር ግን ጥርጣሬን፣ ፍርሃትን ተደላድሎ አለመኖርን ሊያስከትል ይችላል። ይህም አኩራፊና ነጭናጫ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል። ብቸኛና ምስኪን እንደሆናችሁም ይሰማችሁ ይሆናል።

በዚህ አዲስ የመረበሽ ስሜት ሳቢያ ወላጆቻችሁን ትወቅሱ፣ ምን አልባትም ከእነርሱ ጋር ትከራከሩና ትዘልፏቸውም ይሆናል። በኋላም የሕሊና ወቀሳ ይሰማችሁና በድርጊታችሁ ታፍሩ ይሆናል። ይህ የማያቆምና የሚሸከረከር ነገር ነው። ጫጩቱንና የዕንቁላሉን ቅርፊት አስቡ። ወላጆችም የዕንቁላል ቅርፊት እንዳልሆኑ አስተውሉ። እግዚአብሔር እነርሱን ለእናንተ የሰጠው ለዚህ ጊዜ ነው። ሄዳችሁ የተሰማችሁን ሁሉ ንገሩአቸው። እነርሱም በዚህ የዕድገት ደረጃ ውስጥ እንዳለፉ አስቡ። እነርሱም በዚያን ጊዜ በወላጆቻቸው ለምን እንደተቆጡና እንዳመፁ ጠይቋቸው። ይህ መንገድ ስለወላጆቻችሁ የበለጠ እንድታውቁ ይረዳችኋል።

ራስን መቻል አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳ አስፈላጊ ነገር ነው። በዚህም ጊዜ ከሁለት ዓይነት ተፅዕኖዎች ጋር ትለማመዳላችሁ።

1. የመጀመሪያው ፍርሃት ይሆናል። ይህ ያለሙትን ነገር ከግብ አለማድረስ በትምህርት ቤት የምትፈልጉትን ያህል አለመሥራት ዓይነት ፍርሃት ነው። በዙሪያችሁ ያሉት ሰዎች እንዲያከብሯችሁ ሁሉንም ነገር በደንብ መሥራት ትፈልጋላችሁ። ባልንጀሮቻችሁ እናንተን መቀበላቸውና መውደዳቸው ለእናንተ በጣም አስፈላጊ ነው። መልከ መልካም ወይም ጎበዞች ወይም ሀብታሞች መሆን ብትችሉ ብዙ ጓደኞች ወደ እናንተ ለመሳብ የምትችሉ ይመስላችኋል። እነዚህ ነገሮች ግን ስለሌላችሁ ተስፋ ቢሶችና የማትረቡ ሆኖ ሊሰማችሁ ይችላል።

2. መጨነቅ ላልሆነ ነገር በሃሳብ መባከን ነው። አንድ መጥፎ ነገር ቢሆንስ ብላችሁ ለማይታወቅ ነገር በፍርሃት መኖር ነው። አንድ ሰው እንዲህ አለ:- በአዕምሮዬ በጣም ብዙ ችግሮች ነበሩብኝ። ብዙዎቹ ግን አልተፈፀሙም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «የነገው ጭንቀት ለነገው ይበቃል፣ ስለዚህ ለነገ በማሰብ አትጨነቁ ለእያንዳንዱ ቀን የገዛ እራሱ ጭንቀት ይበቃዋል» (ማቴ. 6:34)

ከተቃራኒ ፆታ ጋር ምንም ነገር ላለማድረግና ደደቦችም ናቸው ብላችሁ ያሰባችሁበት ጊዜ እሩቅ አይደለም። አሁን ግን በአንድ ጊዜ ከወንዶችም ሆነ ከሴቶችም ጋር መነጋገር ትወዳላችሁ፤

ሆኖም እነርሱ አካባቢ ስትደርሱ ፍርሃትና ሐፍረት ይሰማችኋል። አንዳንድ በእናንተ ዕድሜ የሚገኙ ወንዶች ልጆች በልጃገረዶች ላይ ይቀልዳሉ ያሾፋሉም። ይህ ካለሐፍረት ከልጃገረዶች ጋር የሚነጋገሩበት አንዱ መንገድ ነው። ከምዕራፍ ሁለት እስከ አራት ድረስ ባሉት ምዕራፎች ውስጥ በወጣት ልጆች ላይ የሚካሄደውን ለውጥ አውቃችኋል። ነገር ግን ይህ አካላዊ ለውጥ ብቻ እንዳልሆነ እወቁ። ስሜታዊ ለውጥም ጭምር ነው። አንድ ቀን ራሳችሁ የምታፈቅሩትና የምትንከባከቡት ባል ወይ ሚስት እስከሚኖራችሁ ጊዜ ድረስ እግዚአብሔር እያዘጋጃችሁ ነው። ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች አዲስ የግፍቀር ስሜት መሰማቱ መጥፎ አይደለም። ነገር ግን በተቃራኒ ፆታ አጠገብ እራስህን እንዴት እንደምትጠብቅ ለመማር ገና ብዙ ዓመት እንዳለህ አትዘንጋ። ከሁሉ የተሻለው ሕግም እራስህን መሆን ነው። አነጋግራቸውና ስለ እነርሱ በተቻለ መጠን ለማወቅ ሞክር። ከእነርሱ ብዙ ለመማር ትችላለህ።

እግዚአብሔር በየዕድሜአችን ደረጃ እንዴት መኖር እንደሚገባን በቃሉ ጽፎልናል። ግራ በሚያጋባው የዕድገት ወቅት ውስጥ ስታልፍ በዘጸአት 20:3-17 የሚገኘውን መመሪያ ተቀበል።

1ኛ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክትን አታምልክ።» ከእግዚአብሔር በላይ የምንወደው ነገር ሁሉ ጣዖታችን ነው። በልባችሁ እርሱን ብቻ ለመከተል ወሰኑ። ብዙ ነገሮች ለምሳሌ እንደ:- ጓደኛ፥ ትምህርት፥ መዝናናትና፥ ሥራፈትነት፥ የመሳሰሉት ሁሉ ልባችሁን ሊወስዱት ይፈልጋሉ። ኢየሱስ በማቴ. 6:33 እንዲህ ይላል። «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፅድቁንም እሹ ከዛ ይህ ሁሉ ይጨመርላችኋል»

2ኛ «ለራስህ ሌሎች አማልክትን አትሥራ» በአምልኮትህም ሆነ በሕይወትህ የእግዚአብሔርን ቦታ ለሌላ አትስጥ።

3ኛ መሐላና ዘለፋ ትሰሙ ይሆናል። በዚህ ወጥመድ ውስጥ እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ። ንግግርህን አታራክስ፤ ግለት ልብህን በንጽሕና ጠብቅ። «አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና» [ምሳ. 4:23]

4ኛ «የሰንበትን ቀን አክብር» ኢሳ. 58:13-14

5ኛ «እናትህንና አባትህን አክብር» ተስፋ ያለው ትእዛዝ ይህ ብቻ ነው። እርሱም:- «እግዚአብሔር አምላክ በሚሰጥህ አገር ዕድሜህ እንዲረዝም» ይላል። ወላጆቻችሁ ላይሆኑ እናንተ እንደተለወጣችሁ አትዘንጉ። ነገር ግን ይህንን ለውጥ እነርሱ ስለሚረዱት ከእነርሱ ዘወር ባትሉ ሊረዷችሁ ይችላሉ።

6ኛ «አትግደል» ኢየሱስ ይህንን በማቴ 5:21-22 ሰፋ ባለ መንገድ ገልፆታል። «ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል። የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። ወንድሙንም ደደብ የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለው ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል» ይህ በሕይወታችሁ ውስጥ አንዳንዴ በሰዎች ላይ የምትቆጡበት ጊዜ ነው። ቁጣ ትንሽ ነገር ስላልሆነ ወደ እግዚአብሔር ሄዳችሁ ቁጣችሁን እንዲያስወግድላችሁና በልባችሁም ፍቅር እንዲሞላ ጠይቁት፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቁጣን እንደመግደል ይቆጥረዋልና ነው።

7ኛ «አታመንዝር» ለተቃራኒ ፆታ የፍቅር ስሜት ሲኖራችሁ ይህን በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የመሞከር ፈተና አለ። እግዚአብሔር ግን አይሆንም ይላል። ይህ እናንተን የሚጎዳ ባይሆን

ኖሮ እንደማይከለክላችሁ አትጠራጠሩ። እግዚአብሔር ይህንን ሥጋዊ ግንኙነት በጋብቻ ውስጥ ብቻ እንዲፈጸም ደንግጓል። ነገር ግን ከጋብቻ ውጭ የሚሞክሩት ሁሉ ለራሳቸው በሕይወት ዘመናቸው ፀፀትን ያተርፋሉ። ስለዚህ ጉዳይ በምዕራፍ 12 በድጋሚ እንነጋገርበታለን።

8ኛ «አትስረቅ» ብዙ ጊዜ በወጣትነት ዕድሜ ያለ ችግር የመሰራረቅ ፈተና እንደሆነ አስተውላችኋል? ለዚህም ዋናው ምክንያት ወጣቶች ሌሎች ልጆች ያላቸውን ነገር እነርሱም እንዲኖራቸው ስለሚፈልጉ እነዚህን ነገሮች ለማገኘት ሲሉ ለመሰረቅ ያስባሉ። እግዚአብሔርም እንደገና ይህ አይሆንም ይላል።

9ኛ «በሐሰት አትመስክር» እውነትን ተናገር። ከችግር ለመዳን ስትል ውሸት በመናገር ትፈተን ይሆናል፤ ሆኖም ውሸት የመናገር ትርፉ ለበለጠ መከራ ወይም ችግር መጋለጥ ነው። ምን ጊዜም ቢሆን እውነት ተናገር። የሰራኸው ነገር ቅጣት የሚያስከትል ቢሆን እንኳ ሁልጊዜ እውነት መናገር ይሻላል። እግዚአብሔር እውነተኛነትህን ያከብርልሃል፤ አንተንም ይባርክሃል።

10ኛ «አትመኝ» ቅንአት በልብ ውስጥ እንደሚነድ ፍም ነው። ይኸውም የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን፤ መመኘት ደግሞ ሁለተኛው ነው። ስለዚህ አትመኝ ይላል። ምንአልባት ሌላ ሰው ያለውን ነገር እንዲኖርህ አጥብቀህ ትፈልግ ይሆናል። እግዚአብሔር ይህን ስሜት እንዲያስወግድህና ያ የተመኘኸው ነገር ሌላው ሰው ካለው ጋር መደሰት እንድትችል ጌታ እንዲሰጥህ ለምን። ሂሩት ኤልሳቤጥ ባላት አዲስ የሚያምር ሹራብ አብራ መደሰት ትችል ነበር። ምንአልባት ለእርሷ ይህ ሹራብ ለብርድ ያስፈልጋት ይሆናል። አብራት ከመደሰት ይልቅ ሂሩት ቀናችባት።

ከሌሎች ሰዎች ጋር በሰላም መኖር ስላለብን እግዚአብሔር እነዚህን ዋና ዋና ሕግጋትን ሰጥቶናል። ስለዚህ ተለማመዱ።ቸው። ከዛሬው ለመጀመር ምክሩና እንዴት እንደሚረዷችሁ ታያላችሁ።

ለአስተማሪዎች የሚጠቅም፡-

የሚጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡- ዘጸአት 20፡3-17፥ ማቴ. 6፡33፥ ኢሳ. 58፡13-14፥ ማቴ. 5፡21-22

ለተማሪዎቻችሁ ሕይወት ጥሩ መሠረት የሚሆነውን ጥቅስ ከመፅሐፍ ቅዱስ ማውጣት አስፈላጊ ነው። አሥርቱ ትዕዛዛት የክርስቲያኖች መለያ (ናቸው) ብለን መጥራት እንችላለን። የክፍላችሁ ልጆች እያንዳንዱን ትዕዛዝ እንዲወያዩባቸውና በቀን ሥራቸውም እንዲጠቀሙባቸው አበረታቷቸው።

ክፍል 4
ወጣቶች ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት

ምዕራፍ 7
ከወላጆቻችሁ ጋር በሰላም መኖር

ዓላማ፡- ወጣቶች የወላጆቻቸውን ዓላማ ምኞት፥ ጭንቀትና ደስታ እንዲያስተውሉና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዴት ማሻሻል እንደሚችሉ ለመርዳት።

የሚጠና ጥቅስ «ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ» (ሮሜ . 12፡18)

መግቢያ

ቤተሰብ ምንድን ነው? ቤተሰብ የሚመሠረተው በአባት በእናትና በልጆች ነው። አንተ የምትኖረው በመኖሪያ ቤትህ ነው። ይህም የምትኖርበት ቤት ድጋፍና ማበረታታት እንዲሁም በኑሮህ ለማደግ የምትችልበትን ሁኔታ ሊያመቻችልህ ይገባል።

ቤተሰብህ ምን ይመስላል? እንተስ በቤተሰብህ መካከል ላለው ግንኙነት ምን ያህል አስተዋፆ ታበረክታለህ? ምንአልባት ቤተሰብህ ይህንን ይመስል ይሆናል፡-

አባት፡- ወደ ቤተ ክርስቲያን የመሄጃው ጊዜ ደርሷል። ሁላችሁም ተዘጋጅታችኋል?

ዳዊት፡- አፋ (ለራሱ ብቻውን እንዲህ ይላል «ይህ ደግሞ ከጀርባዬ አይወርድም ሁሌ እኔ የማልወደውን ነገር ያመጣል»)

አባት፡- እባክህ ዳዊት መኪናውን ከጋራዥ አውጣልኝ፤ እና የግቢውን በር ከፍተህ እኛ ከወጣን በኋላ በሩን ትዘጋዋለህ።

ዳዊት፡- ከራሱ ጋር እየተነጋገረ (ወደ ደጅ እየወጣ፡- ሁሉን ነገር ለምን ይነግረኛል። እኔ አእምሮ እንዳለኝ አያውቅምን?)

ትምህርት

ወጣቶች ሲያድጉ ወላጆቻቸው ስህተት የሌለባቸው ወይም ፍጹም እንዳልሆኑ ወዲያውኑ ያውቃሉ። ትንሽ ልጅ ሳላችሁ አባትና እናታችሁ ሁሉን ነገር የሚያውቁ ሁሉንም ነገር በትክክል የሚሠሩና በዓለም ላይ ያሉትን ችግሮች ሁሉ የሚያሸንፉ መስለው ታይተዋችሁ እንደነበረ አያጠራጥርም። ለሕፃን ይመስለዋል። አሁን ግን ስላደጋችሁ ያ አስተሳሰብ በጭራሽ እውነት እንዳልሆነ ታስተውላላችሁ። ደግሞም ሁሉን ነገር ላያውቁ ይችላሉ። ይህ ግን ይረብሻችኋልን? የእናንተን ችግር የማይረዱና ለሚያስፈልጋችሁም ነገር ደንታ የሌላቸው መስለው ይታዩዋችሁ ይሆናል። እንዲህ በማድረጋቸው ኋላቀሮች ናቸው ትሉ ይሆናል?

እስቲ ወላጆች ስለ ቤተሰቦቻቸው ያላቸውን ዓላማና ግብ ላንድ አፍታ እናስብ። በሕፃንነትህ ለእነርሱ ታዛዥ እንድትሆን፥ ትልልቆችን እንድታከብር፥ በሥራህም ጥንቁቅ እንድትሆን

ለማስተማር ሞክረዋል። ያላቸውም ፍላጎት የእግዚአብሔር ፍቅርና ፍርሃት በውስጥህ እንዲሰርፅ ነው። ይህንንም ሁሉ ባላቸው አርአያነትና በሚሰጡህ መመሪያ ሁሉ አረጋግጠውታል። አንተ እያደክ መሆንህንና ከጥቂት ጊዜ በኋላም የራስህን ኑሮና ትዳር እንደምትመሠርት ያውቃሉ። ስለዚህም አንተን ለዚህ ቀን ለማዘጋጀት የሚጠቅም ምክርን፥ ሐላፊነትን፥ ልምምድን ለመስጠት ሞክረዋል።

ወላጆችህ ካንተ የበለጠ ዕድሜ እንደኖሩና እንዳንዴም ከነበራቸውም ልምድ ብዙ እንዳካፈሉህ ማስታወስ ይጠቅማል። አልፎ አልፎ አንዳንድ ነገሮችን እምቢ የሚሉህና የሚከለክሉህ ከሚያመጣው አደጋ ሊጠብቁህ ስለሚፈልጉ ነው።

ሕፃን ሳለህ አፍንጫህን የሚጠርጉልህ፥ ልብስህ ሲቆሽሽ የሚቀይሩልህ፥ ስትታመም የሚያስታምሙህ ለሐኪም ቤት የሚከፍሉልህ፥ ልብስ የሚገዙልህ፥ ለትምህርት ቤት የሚከፍሉልህ፥ በቀን ምግብህን በሌሊት መኝታህን የሚችሉህ ወላጆችህ እንደነበሩ ማስታወስ መልካም ነው። ይህን ሁሉ በፈቃደኝነትና በፍቅር ላለፉት 15 ወይም 16 ዓመታት ድረስ አድርገዋል። አሁን በሥራ እንድታግዛቸው ሲጠይቁህ አንተ እንቢ ስትላቸው በጣም ያዝናሉ። እነርሱ በቤት ውስጥ ያለውን ሐላፊነት መሸከም የምትችል ትልቅ ልጅ ነህ ብለው ስለሚያስቡ ነው። ከአንተ ለሚያንሱት ልጆች እንክብካቤ ማድረግ የሚገባህ መስሎ ስለሚሰማቸው የአንተ የሕፃንነት ጊዜ ስላለፈ ከወላጆችህ ጋር ልትተባበር የምትችለው አሁን ነው።

ይህን ተጨማሪ ኃላፊነት እንዴት ትወጣዋለህ? ልትወጣ የምትችልባቸው ብዙ ዓይነት መንገዶች አሉ። አንዳንድ ልጆች ሕፃናት ሳሉ ወላጆቻቸውን ቢረዱም እንኳ አሁን ግን ምንም ነገር ለመሥራት ፈቃደኞች አይደሉም። እንቢተኞች ናቸው። ወላጆቻቸው እነርሱን እንደባሪያ የሚጠቀሙባቸው ይመስላቸዋል። በአፋቸው ምንም ላይናገሩ ይችላሉ በውስጣቸው ግን እየተናደዱ ነው።

ሌሎች ወጣቶች ደግሞ በመርዳታቸው ይደሰታሉ ባደረጉትም ይረካሉ። ወላጆችህ ለምን እርዳታ እንደሚጠይቁህ ብትረዳ የቤተሰብህን ኑሮ የሚያስደስት ለማድረግ የሚቻልህን ያህል ትረዳ ነበር። ከእነርሱ ጋር ስትተባበርና እነርሱን ለመርዳት ስትሞክር እነርሱም በበለጠ እንደሚረዱህ ታያለህ። ሌላውን መርዳት ልክ እንደሞተር ዘይት ነው፥ ሞተሩን በደንብ እንዲሽከረከር ይረዳዋል።

በአሁኑ ጊዜ በብዙ መንገድ ከወላጆችህ ይልቅ ጓደኞችህን እንደምታቀርብ አስተውለሃልን? በትምህርት ቤት አንድ ዓይነት ትምህርት ስለምትማሩ እነርሱ የሚረዱህ ይመስላሉ። ፍላጎታቸው ከአንተ ጋር አንድ ዓይነት ነው። በዚህ ትልቅ ዓለም ውስጥ የሚፈፀሙትን ነገሮች ስለሚያውቁ ከእነርሱ ጋር መነጋገር ትወዳለህ። ነገሮችን ሁሉ አሰላስለህ ስለ ሕይወት ወደ እራስህ ውሳኔ ብትመጣ የምትወድ ይሆናል። ይህ ለአንተ አስፈላጊና ጠቃሚ ነገር ነው። የድሮውን መንገድ መመርመርና ለአንዳንድ ለሚከነክናችሁ ጥያቄዎች መልስ መፈለግ ስሕተት አይደለም። ወላጆቻችሁ ያልተረዷችሁ ሆኖ ከተሰማችሁ እናንተ የተማራችኋቸውን አንዳንድ ትምህርቶች ለመማር እንደ እናንተ ዓይነት ዕድል ስላላጋጠማቸው ትክክል ልትሆኑ ትችላላችሁ፤ ሆኖም የሚፈልጉትንና ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር ያውቃሉ።

እናንተ በራሳችሁ ልታስቡ የሚገባችሁን ነገር ማሰብ አስፈላጊ ነው። ስለወቅታዊ ሁኔታዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ። የራሳችሁን አስተሳሰብ ወስኑ፥ አእምሮአችሁም ማሰብ ይጀምራል። አእምሮአችሁን ለማሰራት ምን እና ለምን የሚሉትን ጥያቄዎች ጠይቁ። ይህ ለአሳባችሁና

ለድርጊታችሁ መሠረት የምትጥሉበት ጊዜ እንደሆነ ታያላችሁ፤ ሆኖም ከሐሜትና ከሚጎዳ ንግግር እራሳችሁን ጠብቁ።

የእግዚአብሔርን ቃል አጥኑ። ለጥያቄዎቻችሁ መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታገኛላችሁ። የእግዚአብሔር ቃል በሚያነሳቸው ጉዳዮች ሁሉ ትደነቁ ይሆናል። በደንብ ብትመረምሩት ያላችሁን ችግር ሁሉ የሚነካ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ አለ። እንደዚህ ያለውን ምክር ለጓደኞቻችሁም አካፍሏቸው። ለራሳችሁም ጥያቄዎች መልስ ማግኘት እንደምትችሉ ተመልከቱ።

አንተም ለግልህ በምርመራህ ሁሉ ወላጆችህ በአጠገብህ እንደሚኖሩ አስታውስ። ጓደኞችህ ሁሉ ሲከዱህ እነርሱ እስከመጨረሻ ከአንተ ጋር ይቆማሉ። ከወላጆችህ ጋር በሰላም ለመኖር የሚያስችሉህ እንዳንድ ምክሮች እነሆ፡-

አነጋገራቸው! መልካም ግንኙነት ሊቀጥል የሚችለው በየጊዜው እየተገናኙ በመነጋገር ነው። የሚነግሩህን ነገር በጥንቃቄ አዳምጣቸው! እነርሱ በሚያደርጉት ተግባር ደስታህን ግለፅላቸው፤ አበረታታቸውም፥ በተጨማሪም የግል ጉዳይህን ሳይቀር ከእነርሱ ጋር ተወያይበት።

አዲስ ሃሳብ ማቅረብ ስትፈልግ እንዲያስቡበት ጊዜ ስጣቸው። የወላጆችህን እሽታ አሁኑኑ ከፈለግህ ለእነርሱ ተቃራኒ መልስ መስጠት ይቀላቸዋል። የዚህ ዋናው ምክንያት ለማሰብ ጊዜ ስለሚፈልጉ ነው። በመጀመሪያ ጊዜ ስጣቸው።

በቤተሰብ ጨዋታ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ሁን። አንዳንድ ጊዜ ታኮርፍ ወይም ተስፋ ትቆርጥ ይሆናል። ነገር ግን እራስህን ረስተህ ሌላውን ሰው ለማስደሰት ብትጥር እራስን መቆጣጠር ስለተባለው ነገር ብዙ ትማራለህ ማለት ነው። ጥሩ ነገር ሲሠሩ አመስግናቸው። እናትህንም ጥሩ ምግብ ስትሠራ አድንቅላት አባትህም በየጊዜው ትንሽ አድናቆትና አስተያየትህን ይፈልጋል።

የት እንዳለህ፤ መቼ ወደ ቤትህ እንደምትመጣ ለወላጆችህ የምታስታውቅ ቁምነገረኛ ልጅ ነህን? ይህ ትንሽ አስተዋይነትን ይጠይቃል። ለወላጆችህ ግን ትልቅ ቁም ነገር ነው። በከተማ የምትኖሩ ከሆነ ስልክ ደውልላቸውና በጊዜ እቤት መምጣት እንደማትችል ንገራቸው፥ ወይም ወደቤትህ አካባቢ በሚሄድ ጓደኛህ በኩል መልዕክት ላክላቸው።

ከሌሎቹ ወንድሞችህና እህቶችህስ ጋር ያለህ ግንኙነት እንዴት ነው? ትከራከራለህ ትጣላለህስ? በማያገባቸው ጉዳይ ውስጥ እንዳይገቡ የምትነግራቸው በስድብ ነውን? ልጆች እንዲህ ስትሆኑ ለወላጆች አስቸጋሪ ነው። ከምታዛቸው ይልቅ ለምን እንዲያደርጉ በትህትና አትጠይቃቸውም? ለሕይወት ዘመንህ ሁሉ የሚጠቅም የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ አለ። እንዲህ ይላል «ሰው የዘራውን ያንኑ መልሶ ያጭዳል» ስድብን፤ ራስ ወዳድነትን፤ ክፋትን ብትዘራ ያንኑ መልሰህ ታጭዳለህ። ደግነትንና አሳቢነትን ብትዘራም ያንኑ ደግሞ መልሰህ ታጭዳለህ።

አንተ ታላቅ ከሆንክ ታናናሾችህ እህቶችህና ወንድሞችህ አንተኑ ይከተላሉ። ስለዚህም የአንተ ምላሌነት ከፍተኛ ዋጋ አለው። አንተ ልብ ባትለውም እነርሱ አንተን እያዩ አንተንም ለመምሰል ይሞክራሉ። በኤፌ. 4፡31-32 ያለው ምክር ጠቃሚ ነው። «መራርነት፤ ንዴት፤ ቁጣም፤ ጩኸትም፤ መሳደብም ሁሉ ከክፋትም ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ። ይልቅስ እርስ በእርሳችሁም ደጎችና ሩኅሩሆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ»

ለአስተማሪዎች የሚረዳ

የሚጠና ጥቅስ፡- ኤፌ. 6፡1-4፡ 4፡31-32፡ ቆላ. 3፡20፡ 23-25፡ ቆላ. 3፡13-17

ወላጆች ከወንዶችና ከሴቶች ልጆቻቸው ጋር ወጣቶች በቤት ውስጥ ጥሩ ጊዜ እንዲኖራቸው እንዴት አስተዋፆ እንደሚያደርጉ ተወያዩ። ከዚህ ትምህርት ባገኛችኋቸው ዕውቀት በቤት ውስጥ የተሻሻለ መግባባት እንዲኖር ነጥቦችን በማንሳት ተወያዩ።

ምዕራፍ 8
ትምህርት ቤት እንዴት ነው?

ዓላማ፡- ጥሩ ተማሪና ጥሩ ጓደኛ ለመሆን መመሪያዎችን ለመስጠት። ወጣቶች የጓደኞቻቸውን ግፊት አደገኛነት እንዲያስተውሉት ለማድረግ።

የሚጠና ጥቅስ፡- «በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ በዋዘኞች ወንበር ያልተቀመጠ እርሱ ምስጉን ነው» መዝ. 1፡1

መግቢያ

«ሰለቸኝ! አጠናለሁ! አጠናለሁ ማርኬ ግን ዝቅተኛ ነው» ብሎ አበራ ተበሳጭቶ ተናገረ። ቀጠል አድርጎም «ለያሳሌ ሂሣብን በተመለከተ በክፍል ውስጥ የተቻለኝን ያህል ላዳምጥ ሞክራለሁ የቤት ሥራዬን ሠርቻለሁ። ፈተናው አንድ ቀን ሲቀረው ማታ ለ2 ሰዓት ተኩል ያህል አጥንቻለሁ። ታዲያ ያገኘሁት 42ፄ ነው። ታዲያ ይህ ያዋጣል እንዴ? አያዋጣም! አስተማሪው እያደላ ነው። የእኔን ግማሽ የሚያጠኑ ልጆች ከእኔ የበለጠ ውጤት ያመጣሉ። አሁንስ ሂሣብ የሚባለውን ትምህርት መተው ነው ያማረኝ።»

አዎ! አበራና መሰሎቹ ሁሉ ትምህርታችሁን በማጥናታችሁ ምክንያት ትክክለኛ ነገር አድርጋችኋል። በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ለከፍተኛ ትምህርት ሆነ ጥሩ ሥራ ለመያዝ መልካም ዕድል አላቸው። መልካም የአጠናን ልምድና ዘዴ በትምህርት ስኬታማ እንደሚያደርግ ሁሉ የወደፊት ኑሮንም ስኬታማ ያደርጋል።

ለጥናት የሚረዳችሁ ቀላል ዘዴ ልንነግራችሁ እንችላለን። ቀላል ዘዴ ትፈልጋላችሁ? ነበዝ ተማሪ ከደካማው ተማሪ የበለጠ ዐዋቂ ላይሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ልዩነቱ የአጠናን ልምድ ነው። ጥሩ የአጠናን ልምድ ብዙውን ነገር በጥቂት ጊዜ እንድታጠኑና ሌላ ነገር ለመሥራትም ጊዜ እንዲኖራችሁ ይረዳችኋል።

አንዳንድ ጠቃሚ ሐሳቦች አሉ።

የማጥኛ ቦታ ይኑራችሁ። ይህ ቦታ ሰው የማይረብሻችሁና የማያቋርጣችሁ መሆን አለበት። በተወሰነ ሰዓት ሁልጊዜ ለማጥናት ሞክሩ። ንፁሕ ጠረጴዛና በቂ ብርሃን ይኑራችሁ። ቀጥ ብላችሁ በትክክል ተቀመጡ በእግራችሁ ተረከዝ መሬቱን በደንብ እርገጡና አሁን ተግባራችሁን ቀጥሉ!

ፕሮግራም ይኑራችሁ። ያላችሁን የቤት ሥራ ሁሉ እንድታጠቃልሉ ጊዜያችሁን መጥኑ። ንቁ ስትሆኑ የቤት ሥራችሁን ሥሩ። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተወሰነ ጊዜ መድቡ። የሚከብዳችሁን ትምህርት ሳትደክሙ አጠናቅቁት። በአንድ ትምህርት ብዙ ሰዓት አታጥፉ። በየትምህርቱ መካከል ለ5ና ለ10 ደቂቃ ያህል ዕረፍት ወስዳችሁ ትንሽ ዞር ዞር ብላችሁ ተዝናኑ። የአጠናን ዘዴዎቻችሁን ለዋውጡ። ለምሳሌ ትንሽ አንብቡ፥ የሂሣብ ፕሮብሌሞችን ሥሩ፥ ከዛም በቃል የሚጠና ካለ አጥኑ፥ አንብቡ። እንዲህ የመሳሰሉትን የጥናት ዘዴ ተከተሉ፥ አንድ ሰው የጥናት ሕጎችን እንዲህ አድርጎ አውጥቷል። (ቅኝት)፡- የመጽሐፉን መግቢያ አንብቡ። መግቢያው ውስጥ ጸሐፊው መጽሐፉን ለምን እንደጻፈው ለማን እንደጻፈው ይነግራችኋል። ከዚያም ማውጫውን አንብቡ። አርዕስቶቹ ማጠቃለያ የመሳሰሉትን አንብቧቸው። እነዚህ ከመጽሐፉ ምን እንደምታገኙ ያስታውቋችኋል ሥዕሎችንና ቻርቶችን አጥኑ።

ጥያቄ፡- የመጽሐፉን ጠቅላላ ሐሳበ ስትቃኙ እራሳችሁን እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ጠይቁ። ዋናው ርዕሳችን ምንድን ነው? ይህንን መረጃስ እንዴት በከፍል ውስጥ ወይም ራፖር ላይ አቀርባለሁ?።

ንባብ፡- በመጀመሪያ ባለማንበባችሁ ገርሞአችኋልን? ብዙውን ጊዜ ንባብን እናስቀድማለን አናስቀድምም? ንባቡ ስለትምህርቱ ያለውን ጠቅላላ ሐሳብና ጥያቄን የሚከተል ነገር ነው። ንቁ ሆናችሁ አንብቡ። ላልተረዳችሁት ነገርና ለቤት ሥራ የተሰጣችሁን ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሞክሩ። የእናንተ ሥራ ያነበባችሁትን ማስታወስና መረዳት ነው።

አስፈላጊ የሆኑትን መግለጫዎችና ቃላትን በማስታወሻ ያዙ። በመዝገበ ቃላት አማካይነት የተባለውን ሁሉ እንደተረዳችሁ አረጋግጡ። የቻርቶችንና የሥዕሎቹን መገለጫ አጥኑ። እነዚህ ብዙውን ጊዜ በትንሽ ቦታ የሚጻፉ ቢሆኑም ብዙ መረጃዎችን ይሰጣሉ። ያነበባችሁትን ሁሉ አሜን ብላችሁ መቀበል የለባችሁም። ነገር ግን ጸሐፊው ሊል ያሰበውን ነገር በደንብ ተረድታችሁ ከራሳችሁ ሐሳብ ጋር አስተያዩት። በዚህ መንገድ ለራሳችሁ ማሰብና ማመዛዘን ትማራላችሁ።

በቃል ማስታወስ ወይም ማስታወሻ መያዝ፡- እያነበባችሁ ሳላችሁ የእያንዳንዱን ርዕስ ዋና ሐሳብ ለማስታወስ መጨረሻ ላይ ቆም ብላችሁ አስቡ። ይህ ለመረዳታችሁና ዋናውን ሐሳብ ለማስታወስ ይረዳል። ባነበባችሁትም ነገር ላይ እንድታተኩሩ ይረዳችኋል። ጥሩ ማስታወሻ መውሰድ ነገሩን በቀላሉ ለመከለስ ይረዳል። የምታነቡትን ምዕራፍ ሁሉ በአጭር በአጭሩ ብታስቀምጡት ከ20 እስከ 30 ያለውን ገጽ በ3ና በ4 ገጽ ልታሳጥሩት ትችላላችሁ። አሁን ፍሬውን ከገለባ ለይታችኋል ማለት ነው! የማያስፈልጉ ነገሮችን በማስታወሻ አትያዙ ዋና ዋና ቁምነገሮችን መርጣችሁ በየትምህርቱ በተከፋፈለ የማስታወሻ ደብተር ላይ ፃፉት። በብዕር እንደሚነበብ አድርጋችሁ ጻፉት። መጥፎ አድርጎ መጻፍ ጥሩ አድርጎ የመጻፍ ያህል ጊዜ ይወስዳል። በገጹ መጀመሪያ ላይ ቀኑንና አርዕስቱን ጻፉ።

ከአስተማሪ ማስታወሻ የምትወስዱ ከሆነ አንዳንድ ሊረዷችሁ የሚችሉ ነጥቦች እነሆ። መምህሩ ዋናውን ነጥብ በሠሌዳው ላይ ይጽፍ ይሆናል ወይም «ዋናው ሐሳብ ይህ ነው ወይም ይህንን አስታውሱ ወይም በማስታወሻ ያዙት» ይል ይሆናል። ሌላ መንገድ ደግሞ መምህሩ ዓረፍተ ነገሩን ሊደጋግም ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ አስተማሪው አስፈላጊ ነው ብሎ አምኖበታል ማለት ነው። ድምፁን ከፍ አድርጎ ለዐረፍተ ነገሩ ትኩረት ይሰጠው ይሆናል። እነዚህን ነጥቦች በማስታወሻችሁ ያዙ።

ክለሳ፡ - ክለሳ ከመቃኘት ወይም (ሰረቬይ) ጋር ይመሳሰላል። ሆኖም የሚለይበት ሁኔታ አለ። ይኸውም ከንባብ ከጥናትና ፍሬ ነገሮችን በማስታወሻ ከያዝን በኋላ በስተመጨረሻ የሚመጣ ነገር ነው። ወደ ዋናዎቹ አርዕስቶች ሄዳችሁ ምን እንደሚሉ እራሳችሁን ጠይቁ። ክለሳ ጠቃሚ የሚሆነው አስተማሪው በሚያስተምርበት ወይም በሚናገርበት ወይም መጽሐፍ በሚነበብበት ቀን የተደረገ እንደሆነ ብቻ ነው። ማስታወሻችሁን መከለስ እውነቶቹን በአእምሮአችሁ ያስቀምጣል።

ከፈተና በፊት የሚደረገው ክለሳ በቃል ማጥናት ላይ ያተኮረ ነው። አንዳንድ ጊዜ ጥያቄዎቻችሁን ከጓደኞቻችሁ ጋር ትጠያየቃላችሁ። የተማራችሁትን ሁሉ ከልሱ። ሁሉን ማጥናት እንድትችሉ ጊዜአችሁን ቆጥቡ። ከፈተናው በፊት ባለው ምሽት ትምህርቱን ለመሸምደድ አትሞክሩ። ከፈተና በፊት በመጀመሪያ ከልሱና ከዛ ተዝናንታችሁ ጥሩ እንቅልፍ ተኙ። ለማጥናት የሚረዱ ነገሮችን መውሰድ፥ ማጨስ ወይም ወፍራም ቡና ወይም መጠጥ ብዙ መጠጣት ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም። አእምሮአችሁን እንደሚገባው በትክክል እንዳይሠራ ያደርጉታል።

ዘዴው ጠቅላላ ሐሳቡን መቃኘት ጥያቄ መጠየቅ፥ ማንበብ፥ በቃል ማጥናትና መከለስ ነው። ቅኝት/ጥያቄ/ንባብ/ጥናት/ክለሳ ምክሩትና እንዴት እንደሚጠቅም ተመለከቱ።

በትምህርት ቤት ሌላ የሚያስቸግራችሁ ችግር አለ። ያም ሌላውን መምሰል ነው። «መምሰል የሚለው ቃል ሌሎቹ ልጆች የሆኑትን ለመሆን ያለ ፍላጎት ነው። ይህም ሌሎች የሚሠሩትን መሥራት፥ የሚሉትን ማለት፥ የሚያስቡትን ማሰብ፥ እነርሱ እንደሚለብሱት መልበስ ነው። ሌላውን የሚመስል ሰው፡ - እራሱን ከብዙሃኑ ለመለየት የሚፈራ ሰው ነው። ሌላውን ለመምሰል ከፍተኛ ፍላጎት አለው። መምሰል ማለት በሀሳብ፥ በአለባበስ፥ በአካሄድና በአንጋገር በጊዜው የታወቁትን የሚደነቁትን መቀበል ማለት ነው። በሁላችንም ላይ ቡድኑን ለመምሰል አስደናቂ የሆነ ግፊት አለብን።

አሥር በሚያህሉ የከፍተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገውን ሙከራ ተመልከቱ። አንድ የዶክተሮች ቡድን ካርድ አዘጋጅተው በእያንዳንዱ ካርድ ላይ ሦስት ቀጥተኛ መስመር አድርገዋል። እነዚህም፡ - መስመሮች ሀ፥ ለ፥ ሐ ናቸው። ተማሪዎቹ ስለካርዱ ተነገራቸውና ሐኪሙ በካርዱ ላይ ያለውን ረጅሙን መስመር ሲነካ እጃቸውን እንዲያነሡ አዘዛቸው። እርሱም እንዲህ አላቸው። «ረጅሙን መስመር ስናመለክት እባካችሁን እጆቻችሁን አንሡ»

አንዱ ተማሪ የማያውቀው ነገር ቢኖር ለሌሎቹ ዘጠኙ ተማሪዎች በምስጢር ቀደም ሲል የተነገራቸው በሁለተኛ ደረጃ ያለውን ረጅም መስመር እንዲመርጡ ነው። በሌላ አባባል ለተሳሳተ መሥመር እጃቸውን እንዲያወጡ ተነግሯቸዋል።

ሐኪሙ የመጀመሪያውን ካርድ አነሣና ከመስመር ለ በግልጽ የሚያጥረውን ሀን አመለከተ፤ ሆኖም ዘጠኙ ተማሪዎች እጃቸውን አነሡ። አሥረኛው ተማሪም ዘጠኙ ልጆች እጆቻቸውን ማንሣታቸውን ተመለከተ። ነገር ግን መሥመሩ ከሁሉ ረጅም እንዳልሆነ አወቀ ሆኖም ከሌሎቹ ላለመለየት ሲል እጁን አወጣ። ምን አልባት መመሪያው አልገባኝም ይሆናል ብሎ አሰበ። ሐኪሞቹም እንደገና መመሪያውን እንዲህ በማለት ተናገሩ ልጆች ረጅሙን መስመር ስናመለክት እጆቻችሁን አውጡ። አሁንም አጭሩን መስመር ሲያመለክቱ ዘጠኙም እጆች ይነሣሉ። ከእነሱም ጋር የአሰረኛው ልጅ እጁ ይነሣል።

ምንም ግራ ቢገባውና ስህተት መሆኑንም ቢያውቅም ሐኪሞቹ ሁሉን ካርዶች ባነሱና ዘጠኙም ልጆች ለአጭሩ መሥመር እጆቻቸውን ባወጡ ቁጥር አሥረኛው ልጅም እጁን ያወጣ ነበር።

በሌላ ክፍል ደግሞ ስምንቱ ተማሪዎች ብቻ ለአጭሩ መስመር እጃቸውን እንዲያወጡ ሲነገራቸው ከአሥረኛው ልጅ ጋር ግን አንድ ልጅ ተጨምሮ ሁለት ሲሆኑ ሁለቱም ለረጅሙ መሥመር እጃቸውን አወጡ።

ይህ ምንን ያሳየናል? አንድ ጓደኛ ከእኛ ጋር ለእውነት የሚቆም ቢኖረን እንኳ ብርታት እንደምናገኝ ለማስተዋል ይረዳናል። ጓደኛ ለመምረጥ ምን ያህል ጥንቁቅ ናችሁ? ጓደኞቻችሁ በእናንተ ላይ ከባድ ተጽዕኖ ሊያሳድሩባችሁ ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አንድ ነገር ይናገራል። በ1ኛ ቆሮ. 15:33 እንዲህ ይላል «አትታለሉ! ክፉ ባልንጀራነት መልካሙን አመል ያጠፋል» አብራችሁ ስለምትሆኑት ጓደኞች ተጠንቀቁ። የማይጠቅሙ ነገሮችን በመሥራት ጊዜአችሁን ልታጠፉ ትችላላችሁ። ጳውሎስ በኤፌ. 5:15-16 እንዲህ ይላል «እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንደምትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ» እግዚአብሔር ብቻችሁን እንኳ ብትሆኑ ለእውነት መቆምን ብትማሩ ይወዳል። ኃይልንም ይሰጣችኋል።

ለአስተማሪ የሚጠቅም

የሚጠና ጥቅስ፡- መዝ. 1፥ 1ኛቆሮ. 15:33፥ 16:13-14፥ ኤፌ. 5:15-16፥ ዘፍ. 37:39-50፥ ማቴ. 28:20

ተማሪዎች ለእውነት መቆም ሲሳናቸው አስቸጋሪ ነገሮችን እንዲወያዩ ማድረግ። እንዲሁም ለችግሮቻቸው መፍትሄ ሊሰጡ የሚችሉ ምክሮችን ከእግዚአብሔር ቃል በማንበብ መፅናናትና ብርታትን እንዲያገኙ ማድረግ ነው። የዮሴፍ ሕይወት ለወጣቶች ጥሩ ትምህርት አለው። በክፍል ውስጥ ጊዜ ከሌለ ለሳምንት በቤታቸው ማንበብና ማጥናት ይችላሉ።

ምዕራፍ 9
ቤተክርስቲያን ምንድን ነው?

ዓላማ፡- የቤተክርስቲያን ሥራና ወጣቶችም በክርስቶስ አካል ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ለማስረዳት።

የሚጠና ጥቅስ «እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁ ብልቶቹ ናችሁ» 1ኛቆሮ 12:27

መግቢያ

እኛ የክርስቶስ አካል የሆንን ቤተክርስቲያኑ ነን። ማንኛውም ሰው እንደገና የተወለደና በክርስቶስ ኢየሱስም አዲስ ፍጥረት የሆነ ሰው ሁሉ የአካሉ ክፍል ነው። መዝገበ ቃላት አካልን በሰውነት ላይ ያለ በውጭ የሚታየውና በውስጥ የማይታየው ክፍሎች የሚያሳይ ነው። ይህ አባባል ለእኛ ለሰዎች ተነግሯል። ታዲያ የክርስቶስ አካል መሆን ምን ማለት ነው?

ትምህርት፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ ቤተክርስቲያንን እንደ አንድ አካል አድርጎ ይናገራል። ኤፌ. 5፡3 እንዲህ ይላል «እኛ የእርሱ የአካል ክፍል ነን» በተጨማሪም ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛቆር. 12፡14-26 እንዲህ ይላል፥ «አካል ብዙ ብልቶች አንጂ አንድ ብልት አይደለምና እግር እኔ እጅ አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ቢል ይህን በማለት የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? ጆሮም ዓይን አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ቢል ይህን በማለት የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? ... አሁን ግን እግዚአብሔር እንደወደደ ብልቶችን እያንዳንዳቸው በአካል አድርጎአል። ሁሉም አንድ ብልት ቢሆንስ አካል ወዴት በሆነ? ዳሩ ግን አሁን ብልቶች ብዙዎች ናቸው አካል ግን አንድ ነው። ... አንድም ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ አንድ ብልት ቢከብር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል። እንግዲህ እኛ የክርስቶስ አካል ነን፥ የአካሉ ክፍልም ነን»።

ሐዋርያው በሮሜ. 12፡3-8 ይህንኑ መልሶ ይናገርና እኛ የክርስቶስ አካል ክፍል ብቻ ሳንሆን ነገር ግን እያንዳንዳችን የምንሠራው ሥራ እንዳለንና ያንን እስካልሠራን ድረስ ደግሞ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ያላትን ተልዕኮ እንደማታሟላ ያስታውሰናል።

እጃችሁና እግራችሁን መጠቀም ካልቻላችሁ እንዴት ሊሆን ይችላል? እንዲህ ከሆነ በየቀኑ የምትሰሯቸውን ሥራዎች ለመስራት በጣም አስቸጋሪ ይሆንባችኋል። ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባሎች ሥራቸውን ባይሠሩ ቤተክርስቲያንም እንደሚገባት ልትሰራ አትችልም።

የክርስቶስ አካል እንደመሆናችሁ መጠን እንደክርስቲያን ጤነኛ ለመሆን የሚያስፈልጉዋችሁ የተወሰኑ ነገሮች አሉ። ልክ ሰውነታችሁ ምግብና ውሃ እንደሚያስፈልገው ቤተክርስቲያንም በስብከቷና በትምህርቷ የሚያስፈልጋችሁን መንፈሳዊ ምግብና መጠጥ በማሟላት ልትረዳችሁ ትችላለች። በደንብ እንድትመገቡ በቤተክርስቲያን ሁልጊዜ ትገኛላችሁን? አዎን በታማኝነት ብታዳምጡና በቤት በግላችሁ ከምታጠኑት ትምህርት ጋር ብታስተያዩት ብዙ መማር ትችላላችሁ። በየእሁዱ ሁልጊዜ በቤተክርስቲያን ተገኝታችሁ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ይዛችሁ ስብከቱን ተከታተሉ። አንዱን ጥቅስ ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር አመሳክራችሁ ተመልከቱና ስለምታጠኗቸው ጥቅሶች ተረዱ። ዋናውን የምንባብ ክፍል ሃሣብ ለመረዳት እንድትችሉ ለሌሎች ተመሳሳይ ጥቅሶችን በማወዳደር ፍቺውን ለማግኘት ሞክሩ። የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ምግባችሁ ስለሆነ መቀበልና ማሰላሰል የሚለውንም መታዘዝ ያስፈልጋችኋል።

ቃሉ የሚለውን መታዘዝ ሕይወታችሁን ያነፃል። ሰውነታችሁ ጤነኛ ለመሆን የማይጠቅሙ ቆሻሻ ነገሮችን ማስወገድ አለበት። የእግዚአብሔርም ቃል ሕይወታችሁን እንዲያጠራና ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርባችሁ ፍቀዱለት። ኢየሱስ እንዲህ አለ። «አሁን ስለ ነገርኳችሁ ቃል እናንተ ንፁሐን ናችሁ» (ዮሐ. 15፡3) ቃሉ ልባችሁን እንዲያነፃ ፍቀዱለት።

እረፍትም እንዲሁ ያስፈልጋችኋል። ወደ እግዚአብሔር ቤት በመምጣት የሰማችሁትንና ያጠናችሁትን የእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ለልባችሁ እረፍት ይሰጣል። ጌታ ሸክማችሁን ተሸክም የከበዳችሁንም ነገር ያቃልልላችኋል። «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም ዕረፍትን እሰጣችኋለሁ» (ማቴ. 11፡28) ሆኖም ግን እረፍታችንን የሚሠርቅብን ነገር አለ።

ብትሣሣቱና ኃጢአት ብትሠሩ ነፍሳችሁ ይጨነቃል። ወደ እግዚአብሔር መጥታችሁ ለእርሱ ንገሩት እርሱ እንዲህ ብሏልና «ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊል ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው። [1ኛዮሐ. 1፡9] በታማኝነት በንሥሐ በፊቱ ስትቀርቡ ጌታ ይቅር ሊላችሁና ሊያነፃችሁ ዝግጁ ስለሆነ ልባችሁ አርፎ መንፈሳችሁ ተፈቶ በደስታ ልትነሡ ትችላላችሁ።

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት ጎዳና ሁሉ ልትረዳችሁ ዝግጁ ነች። ልዩ እርዳታም ቢያስፈልጋችሁ ወደ ሰባኪው ወይም ወደ አንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሄዳችሁ ተናገሩ። እነርሱ እናንተን ለመርዳትም ሆነ ለማነጋገር ደስተኞች ናቸው።

እናንተም ጤነኛ የአካል ክፍል ለመሆን ብትፈልጉ ልምምድ ያስፈልጋችኋል። አንዳንድ የአካል ክፍሎቹ በሽተኛ ስለሆኑ ሥራ የማይሠራ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ? ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰውነቱ፤ ጠንካራ ይሆንና መንቀሳቀስ ይሳነዋል። ለጌታ ስትሉ ተንቀሳቀሱ በቤተክርስቲያን ውስጥ መደረግ ያለባቸው ብዙ ነገሮች አሉ።

እጅ ሁኑ፡- በማንኛውም በምትችሉት መንገድ ለመርዳት ፈቃደኞች፥ እግር ሁኑ፡- ተሳላኩ ውሃ እንጨት ጭራሮ ተሸከሙ።

ድምፅ ሁኑ፡- መዝሙር እንድትመሩ ስትጠየቁ መዝሙር ምሩ፥ ዘማሪዎች ሁኑ።

አፍ ሁኑ፡- የሰንበት ትምህርት አስተምሩ፤ ምስክርነታችሁን ስጡ።

አእምሮ ሁኑ፡- በኮሚቴዎች ተሳተፉ! ችግር ለግቃለል እርዳታን ስጡ።

ማንኛውም ዓይነት ሥራ በደንብ ለመሥራት እንዴት እንደሚሠራ ማወቅና ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋችኋል። ለወደፊት የቤተክርስቲያን መሪ ለመሆን ገና ወጣት ሳላችሁ፥ በቤተክርስቲያን ያሉትን ሥራዎች ሁሉ መሞከር አለባችሁ። ተመልካችና ነቃፊ አትሁኑ። ያ ቀላል የማያቅት ነገር ሲሆን እጅግ በጣም አፍራሽ ነው። በጣም ለመሥራት ፈቃደኛ ሁኑ።

የክርስቶስ አካል ከመሆናችሁም በላይ ስጦታ ያላችሁ አካል ናችሁ። ሮሜ ውስጥ እንዲህ ይላል «እኛ እያንዳንዳችን የሌላው አካል ነን» እያንዳንዱ የተለያየ ሥጦታ አለው (ሮሜ. 12፡5-8) እግዚአብሔር በጸጋው መጠን ለእያንዳንዳችን ልዩ ልዩ ችሎታን «ትንቢት መናገርን፥ ማገልገልን፥ ማስተማርን፥ ማፅናናትን ለችግረኞች መለገሥን መምራትን ምሕረት ማድረግን ሰጠን። እነዚህ እግዚአብሔር አካሉ እንደሚገባው እንዲሠራ ለክርስቶስ አካሎች ለልጆቹ የሰጠው አንዳንድ ስጦታዎች ናቸው። 1ኛቆሮ. 12፡7-11 ና ኤፌ. 4፡11፥ 12 አጥኑ። የኤፌሶን የምንባብ ክፍል እግዚአብሔር ይህ ለምን እንዳደረገ ይነግረናል። «ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላት ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍፁማን ይሆኑ ዘንድ» ቁጥር 14 እስከ 16 ያለውንም አንብቡ።

ሥጦታችሁ ምን እንደሆነ እንዴት ታውቃላችሁ? ከሁሉ የተሻለው መንገድ በቤተክርስቲያን ውስጥ መሳተፍ በምትችሉበት ሁሉ መሳተፍ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተወሰኑ ሥራዎችን ስትሠሩ እግዚአብሔር ሲጠቀምባችሁ ታያላችሁ እንዲሁም ሥራውን ስትሠሩ ልዩ የሆነ ደስታ ይሰማችኋል። የሰንበት ትምህርት ታስተምሩ ይሆናል በማስተማራችሁም ትደሰቱ ይሆናል ከዚያም በላይ የምታስተምሯቸው ልጆች በእግዚአብሔር ቃል አድገው በመንፈሳዊ

ሕይወታቸውም ታንፀው ታያላችሁ። እነዚህ ሁለቱ ምልክቶች እግዚአብሔር የሰጣችሁን የማስተማር ስጦታ እየተጠቀማችሁበት እንዳላችሁ ያረጋግጡላችኋል። ምናልባት ስጦታችሁ በአስተዳዳሪነት ይሆናል። ያንን ደግሞ የምታውቁት በቤተ ክርስቲያን ከሚገኙት ከሌሎች ወጣቶች ጋር ስትሠሩ ለሌሎችም በረከት የሚሆነውን ሥራ በቀላሉ ስታከፋፍሉ በዚህም እናንተ በምትሰጧቸው ትክክለኛ የአመራር ስልትና ወኔ ምክንያት በጌታ ዕውቀት ሲያድጉ ነው። ለጌታ ስትሉ በሥራችሁ ተሰማሩ። የምታገለግሉበትን ቦታ እርሱ ያሳያችኋል ከዚያም ለእርሱ ክብር ያንን ስጦታ ትኩረት ስጡት ለማሻሻልም ሞክሩ።

እግዚአብሔር ሊጠቀምባችሁ ይፈልጋል። ያዳናችሁና የራሱ ልጅ ያደረጋችሁ ለዚሁ ነው። የክብሩ መገልገያ መሣሪያ ትሆኑ ዘንድ ነው። ይህች የምንኖርባት በኃጢአት የተሞላች ዓለም በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የደስታና የሰላም መንገድ ለማሳየት በፍቅር ሌሎቹን የሚቀርቡ ሰዎችን በጣም ትፈልጋለች። እግዚአብሔር ለመጠቀም ንጹህ ዕቃ ይፈልጋል። ስለዚህም እንዲህ ይላችኋል። «እንግዲህ ለምኖቱ እንዳትታዘዙ በሚሞተው ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ ብልቶቻችሁን የዓመፅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ። ነገር ግን ከሙታን ተሰይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ። ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ» [ሮሜ. 6፡12-13]

እዚህ ላይ አካልን በሌላ መልኩ እናየዋለን። በዚህ ጊዜ ስለተለያየው የራሳችሁ የሰውነት ክፍል ይናገራል። እግዚአብሔር እያንዳንዱን የአካል ክፍላችሁን በጽድቅ እንድታገለግሉትና እንድትሰጡት ይፈልጋል። ስለዚህ ምርጫው የእናንተ ነው። እርሱ እንዲህ ይላል «ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ። (ሮሜ. 6፡16)

እግዚአብሔር ዛሬ እራሳችሁን በሙሉ እያንዳንዱን የአካል ክፍላችሁን ለእርሱ እንድታስረክቡ ይለምናችኋል። ከዚህ በኋላ አካላችሁ ሁሉ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚጠቅም ይሆናል። እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት መንገድ የእርሱን ዓላማ መፈፀም ይችላል። ይኸውም ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በመረዳት ከፍርድ እንዲድኑ ለማድረግ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት ሁሉ በምድር ላይ ፍሬ አፍርተው እና እንደተስፋ ቃሉ መሠረት በአርገጠኛነት ከእርሱ ጋር በመንግሥተ ሰማያት እንዲኖሩ ይፈልጋል።

ለአስተማሪዎች የሚጠቅም

የሚጠና ጥቅስ፡- ኤፌ. 5፡30፥ 1ኛቆሮ. 12፡12-21፥ ሮሜ. 12፡3-8፥ ኤፌ. 4፡11-16፥ ሮሜ. 6፡11-13፥ 12፡1፥2

ስለሚያስደንቀው የሰው አካል ዓይንና አእምሮ እንድንመረምርና የአነበብነውን እንድናስተውል እንዴት አካሎቻችሁ በአንድ ላይ ተባብረው እንደሚሠሩ ተወያዩ። በሚሆናቸው ወይም በደንብ ማገልገል በሚችሉበት ቦታ ገብተው ቤተክርስቲያንን የሚረዱበት መንገድ እንዳለ እንዲወያዩበት አድርጉ።

ክፍል 5
ለአዋቂነት መዘጋጀት

ምዕራፍ 10
እራስን መቆጣጠር

ዓላማ፡- ወጣቶች አሁን ያላቸውን ልምምድ እንዲመረምሩ ጤናማና መንፈሳዊ የሆነ ሕይወት እንዲመሠርቱ አንዳንድ ሐሳቦችን መስጠት።

የሚጠና ጥቅስ፡- «የሚታገልም ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው እኛ ግን የማይጠፋውን» 1ኛ ቆሮ. 9፡25

መግቢያ

ልጆቼ ሁሉ የተለያዩ ናቸው። አንደኛው በጠዋት መነሣት ይወዳል። ሌላው ደግሞ መተኛት ይወዳል» አለች እናት ለነረቤትዋ «እውነት! የኔ ልጆች ግን ሁሉም እኩል በጠዋት ይነሣሉ። ባለቤቴ መተኛታቸውን ስለማይፈልግ እርሱ ከተነሣ እነርሱ እንዲተኙ አይፈቅድላቸውም። እንደውም እርሱ ስንፍና የሚጀምረው አርፍዶ በመነሣት ነው ብሎ ያስባል» ብላ ጎረቤትዋ መለሰችላት።

ትምህርት

የሁሉም ሰው ቤት የተለያየ ነው። የእናንተም ቤት ልዩ እንደሆነ የማያጠራጥር ነው። አሁን የራሳችሁን ልምምድ ለማዳበር ዝግጁዎች ናችሁ። የግላችሁን ልምድ ሁልጊዜ ታደርጉታላችሁን? ሥራችሁን ሠርታችሁ በማግሥቱ ለትምህርትና ለቤት ሥራ ንቁ ለመሆን በቂ እንቅልፍ ማግኘት ትችላላችሁን? በተመሰነ ሰዓት መተኛትና መነሣት ካዘወተራችሁ ይህ የዕድገትና የብስለት ምልክት ነው።

የቀጠሮ ሰዓት መጠበቅስ? ከአንድ ሰው ጋር ቀጠሮ ካለህ በሰዓቱ ትደርሳለህን? የቤት ሥራህስ? የቤት ሥራህን በጊዜው ጨርሰህ ትሰጣለህን? ከፍልስ በሰዓቱ ትደርሳለህን? አንዳንድ ሰዎች በጊዜው ለመድረስ ቃል ይገባሉ። ቃላቸውን ግን አይጠብቁም። አንተ ራስህ ይህ እንዴት እንደሚያናድድ ታውቃለህን!

ሂሣብ የመክፈል ጉዳይም አለ። ለኮሌጅ ወይም ለዩኒቨርስቲ የምትከፍለው ገንዘብ ወይም ለስፖርት የሚከፈል ወይም መጽሐፍ የተከራየህበትና የቤት ኪራይ ሂሣብ ሊኖርህ ይችላል። ሂሣብህን በወቅቱ የመክፈል ልምድ አለህን? ይህ የገንዘብ አያያዝ ክፍል ሲሆን ጥሩ ልምድ ለማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው።

ለምትለብሰው ልብስስ ትጠነቀቃለህን? የራስህን ልብስ አጥበህ ትተኩሳለህን? የራስህ ንብረቶች በንፅህና በሥርዓት ስትፈልጋቸው ቶሎ የምታገኝበት ቦታ የተቀመጡ ናቸውን? ወደ ቤትህ ስትገባ ልብስህን አውልቀህ ትሰቅላለህን፥ ጫማንስ አውልቀህ በሥርዓት ታስቀምጣለህን?

ምግብ በተወሰነ ጊዜ በደንብ መብላት ጤነኛ ለመሆን ይረዳል። ጤንነት ሲሰማህ በሥራህ ሁሉ ንቁና ታታሪ ሠራተኛ ትሆናለህ። በትምህርት ቤት በተማርከው መሠረት ለጤና ሥጋ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ወተትና ጥራጥሬ እንደሚያስፈልግ ታውቃለህ። ገና ተማሪ ሆነህ የሚያስፈልግህን ተመጣጣኝ ምግብ ሁሉ ማግኘት መቼም የማይቻል ነገር ነው። ሆኖም የትመጣጠነ ምግብ ለመብላት መጣር አለብህ። ለግል ንፅሕናህም መጠንቀቅና በየጊዜውም መታጠብ በሽታዎችንና የቆዳ መበላሸትን ለመከላከል ይረዳል።

መልካም ጤንነት ከእግዚአብሔር የተገኘ አስደናቂ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር የሰጠህን ሰውነት ለመጠበቅ ተጣጣር። የግል ልማድህን በየጊዜው እንድትፈጽምና እራስህን የቻልክ እንድትሆን፣ ስትማር ለወደፊት ሕይወትህ መሠረት እየጣልክ ነው።

በስፖርትስ ትሳተፋለህን? በጥሩ የስፖርት ፕሮግራም ገብተህ ብትሳተፍ ብዙ ነገር ትማራለህ። ከሁሉ በፊት በየጊዜው መነቀሳቀስ ለሰውነትህ ጥሩ ነው። ሁለተኛ በስፖርት ውስጥ ያለው ውድድር ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመገናኘት ይረዳል። ይህ መማር የሚገባህ አስፈላጊ ትምህርት ነው። አሸናፊ ነህን? ሽንፈትህንስ በፀጋ ትቀበለዋለህን? ይህም ውስጣዊ ስሜትህን ለመግታትና ስለሌላው እንድታስብ ያደርግሃል። በትምህርት ቤት በሚገኙት የተማሪዎች አስተዳደር (ካውንስል) ውስጥ በመሳተፍ ጥሩ የዕድገት ትምህርቶች ይቀሰማል። ለምርጫ ስምህ በሚጠራበት ጊዜ ምን እንደምታደርግ ግራ ስለሚገባህ ፈርተህ ታውቃለህን? ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሥራት ብዙ ትማራለህ። አትርሳ እነርሱም በመማር ላይ ስላሉ ታዲያ ለምን አብረሃቸው አትማርም።

ጥሩ ጤናማ ልማድ ከኖረህና ከሰዎችም ጋር መተባበርን ከተማርክ በመንፈሳዊ ሕይወትህም ጥሩ ልማድን ለመመሥረት ትወዳለህ። በየዕለቱ መመገብ ለሥጋዊ ሕይወትህ እንደሚጠቅም ሁሉ በየዕለቱ ቃሉን ማንበብ ለመንፈሳዊ ሕይወትህ ይጠቅማል። ልክ ለሰውነትህ ኃይል ለማግኘት በየጊዜው መመገብ እንደሚያስፈልግህ ሁሉ፣ መንፈሳዊ ሕይወትህም በእግዚአብሔር ቃል በየጊዜው ልትመገብ ያስፈልግሃል።

እነሆ! መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደምታነብ የሚረዱህ አንዳንድ ምክሮች እዚህ አሉ።

1. በየቀኑ አንብብ፡- ብዙ ሰዎች ለንባብ የተሻለው ጊዜ ጥዋት ነው ብለው ያምናሉ። ዘወትር ከምትነሣበት ሰዓት 15 ወይም 30 ደቂቃ ቀደም ብለህ በመነሣት ጥሩ የጥሞና ጊዜ ሊኖርህ ይችላል።

2. በየጊዜው የምታነብበትን ጊዜ ወስን፡- መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል በእውነት ለማወቅ ከፈለግህ ጊዜ መስጠት ያስፈልግሃል። በየቀኑ ከ15 እስከ 30 ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር ትማራለህ።

3. የተወሰነ ቦታ ይኑርህ፡- በአንዳንድ ምክንያቶች ከብዙ ምኞት ነሽዎች ለመዳን ባዶና ንፁህ በሆነ ጠረጴዛ እንዲሁም ወንበር መቀመጥ ከሁሉ የተሻለ ይሆናል። ወይም ከውጭ ፀጥ ያለ ቦታ ፈልግ።

4. በምታነብበት ጊዜ እርሳስ ከእጅህ አይለይ፣ የቃላቶች ትርጉም ሳይገባህ ማንበብ ትችል ይሆናል። አእምሮህን ለመሰብሰብ እግዚአብሔር በግል የተናገረህን ነገሮች በወረቀት ላይ ማስፈር ከሁሉ የተሻለ መንገድ ነው።

5. *መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቅ አንብብ።* እግዚአብሔር ከምታነበው አንድ አዲስ ነገር እንዲያስተምርህ በጸሎት ጀምር። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ አንሥቶ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በልብህ እንደሚኖር ታውቃለህ! (2ኛ ጢሞ. 3፡16፥ 1ኛቆሮ. 6፡19-20) እርሱ የምታነበውን ነገር አንድትረዳ ስለሚፈልግ እንዲረዳህ ጠይቀው «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ» የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (2ኛጢሞ. 3፡17)

6. አንተ በቀን የተማርከውን መንፈሳዊ ነገር ጽፈህ አስቀምጥ። አንድ ሰው ጠቃሚ ሆኖ ያገኘው የአጻጻፍ ዓይነት በዚህ ምዕራፍ በስተመጨረሻ ላይ ይገኛል። የሚከተሉት በዕለት ማስታወሻህ ውስጥ መስፈር ያለባቸው አንዳንድ ነገሮች ናቸው።

   ሀ. ዛሬ ለአንተ ያለውን የእግዚአብሔር መልእክት፡- ያንኑ መልዕክት ከፈለከው ታገኘዋለህ። ይህም በዚያው ቀን ጠቃሚ ትምህርት እንዳስተላለፈልህ ይታወቃል። በተጨማሪም ችግርህን ወዲያውኑ ያቃልልልሃል።

   ለ. እግዚአብሔር ቃል የገባልህ ነገር፡- የምታነበው ምዕራፍ ሁሉ የተስፋ ቃል ላይኖረው ይችላል፥ ሆኖም ብዙ ጊዜ ለአንተ የሚሆን የተስፋ ቃል ታገኛለህ። ለራስህ የሚሆን የተስፋ ቃል ስታገኝ ሁለት ነገሮችን ማየት ይኖርብሃል። እግዚአብሔር በአጠቃላይ ለአንተ የገባው ቃልኪዳን እንደሆነና እንዲሁም ከቃል ኪዳኑ ጋር የተገፋትን ሁኔታዎች ተመልከት። ሁኔታዎቹን የምታሟላ ከሆንክ እግዚአብሔርም ለቃሉ እንደሚቆም እርግጠኛ መሆን ትችላለህ።

   ሐ. *መጠበቅ ያለበት ትእዛዝ*፡- በዚህ የሕይወት ዘመንህ አስፈላጊ ነው ብለህ የምታምንበትን ቃል በጸሎት ደብተርህ ላይ ጻፍ፤ ከዚያም ለመታዘዝ ሞክር።

   መ. ጊዜ የማይሽረው *መመሪያ*፡- *መጽሐፍ* ቅዱስ ለቀን ኑሮ የሚጠቅም ከሺህ የሚበልጥ *መመሪያዎችን* የያዘ በጣም ትልቅ መጽሐፍ ነው። እነዚህን *መመሪያዎች* በቃልህ ብታውቅ መልካም ውሳኔዎችን እንድትወስን ያስችሉሃል። ለምሳሌ በ1ኛቆሮ. 6፡14-18 «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ» ይላል።

   ሠ. በሕይወትህ የምትለማመደው፡- እግዚአብሔር የሰጠህን እውቀት አስበህ፤ እግዚአብሔር ከተናገረህ ውስጥ የቱን እንደምትጠቀምበት *መምረጥ*። ለመታዘዝ ቆርጠህ በመነሣትህ እንዲሁም አረማመድህን ለመለወጥና አንዳንድ ነገሮች ለማሻሻል እንደፈለግህ እርሱ ያውቃል። ከዚህም የተነሳ እርሱ አንተን ለመርዳት ኃይሉን ይልካል።

ምናልባት አንተና መሰሎችህ ልትጠቀሙበት የምትሹት የ3 ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራም አለ እንደሚከተለው ቀርቧል።

አንደኛ አመት

1ኛ ዮሐንስ፡- ለ7 ቀናት በየቀኑ *መጽሐፉን* በሙሉ አንብቡት። የዮሐንስ ወንጌል፡- *መጽሐፉን* ሁለት ጊዜ አንብባችሁ እስከምትጨርሱ በየቀኑ 4 ምዕራፍ አንብቡ።

የማርቆስ ወንጌል፡- ልክ የዮሐንስን ወንጌል እንዳነበባችሁት አንብቡ።

ከገላትያ እስከ ፊልሞንም በዚሁ *መንገድ* አንብቡት

ሉቃስ፡ የሐዋርያት ሥራና ሮሜንም እንደ ላይኛው አንብቡት

አዲስ ኪዳንን በሙሉ ሁለት ጊዜ አንብቡት።

ሁለተኛ ዓመት

ምሳሌ፡- ለአራት ወራት በየቀኑ አንድ አንድ ምዕራፍ አንብቡ። መጽሐፈ ኢዮብ፡ የዳዊት መዝሙር፡ መክብብ፡ መኃልየ መኃልይዘሰለሞን፡- በቀን ሁለት ምዕራፍ አንብቡ።

የሚከተሉትን ለአንድ ወር ያህል በመደጋገም አንብቢቸው።

1ኛ ዮሐንስ፡ ኤፌሶን፡ ፊልጵስዩስ፡ ቆላስይስ፡ 1ኛተሰሎንቄ፡ ያዕቆብ፡ ሮሜ. 5-8፡ ዮሐንስ 14-17።

ሦስተኛ ዓመት

በየቀኑ ከአዲስ ኪዳን አንድ ምዕራፍ

በየቀኑ ከብሉይ ኪዳን 2 ምዕራፍ

እሑድ እሑድ ከብሉይ ኪዳን 5 ምዕራፎችን ማንበብ

ይህ በሦስት ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉ እንድታነቡ ያደርጋል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሌላ በምንም ዓይነት መንገድ ልትማሩ የማትችሉትን ያህል እንድትተዋወቁ ያደርጋችኋል። እግዚአብሔር በፀጋው ይባርካችሁ።

ለአስተማሪዎች የሚጠቅም፡-

- የሚጠና (የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ) 2ኛጢሞ. 2፡15፣ 3፡16-17፣ 1ኛ ቆሮ. 6፡19-20፣ 1ኛ ቆሮ. 6፡14-18፣ የሐዋ. 17፡11

- ተማሪዎቻችሁን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ ፕሮግራም እንዲያወጡ እርዱአቸው። መቼ ማን ለማንና እንዴት መጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈ ግለፁላቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ አንዳንድ ሐሳቦችን ታገኛላችሁ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ደብተር

እሑድ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል _____ ቀን _____

እግዚአብሔር የተናገረኝ ቃል	ጌታ የገባልኝ የምታዘዘው ትዕዛዝ	ጊዜ የማይሽረው መመሪያ

ይህንን እንዴት በሕይወቴ መለማመድ እችላለሁ። _____

ሰኞ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል _____ ቀን _____

እግዚአብሔር የተናገረኝ ቃል	ጌታ የገባልኝ የምታዘዘው ትዕዛዝ	ጊዜ የማይሽረው መመሪያ

ይህንን እንዴት በሕይወቴ መለማመድ እችላለሁ። _____

ማክሰኞ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል _____ ቀን _____

እግዚአብሔር የተናገረኝ ቃል	ጌታ የገባልኝ የምታዘዘው ትዕዛዝ	ጊዜ የማይሽረው መመሪያ

ይህንን እንዴት በሕይወቴ መለማመድ እችላለሁ። _____

እሮብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል _____ ቀን _____

እግዚአብሔር የተናገረኝ ቃል	ጌታ ገባልኝ የምታዘዘው ትዕዛዝ	ጊዜ የማይሽረው መመሪያ

ይህንን እንዴት በሕይወቴ መለማመድ እችላለሁ። _____

ሐሙስ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል _____ ቀን _____

እግዚአብሔር የተናገረኝ ቃል	ጌታ የገባልኝ የምታዘዘው ትዕዛዝ	ጊዜ የማይሽረው መመሪያ
_____	_____	_____
_____	_____	_____
_____	_____	_____

ይህንን እንዴት በሕይወቴ መለማመድ እችላለሁ። _____

አርብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል _____ ቀን _____

እግዚአብሔር የተናገረኝ ቃል	ጌታ የገባልኝ የምታዘዘው ትዕዛዝ	ጊዜ የማይሽረው መመሪያ
_____	_____	_____
_____	_____	_____
_____	_____	_____

ይህንን እንዴት በሕይወቴ መለማመድ እችላለሁ። _____

ቅዳሜ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል _____ ቀን _____

እግዚአብሔር የተናገረኝ ቃል	ጌታ የገባልኝ የምታዘዘው ትዕዛዝ	ጊዜ የማይሽረው መመሪያ
_____	_____	_____
_____	_____	_____
_____	_____	_____

ይህንን እንዴት በሕይወቴ መለማመድ እችላለሁ። _____

ክፍል 5
ለአዋቂነት መዘጋጀት

ምዕራፍ 11
የሕይወትህ ሥራ

ዓላማ፡- ወጣቶች ችሎታቸውን በማመዛዘን እንደዝንባሌአቸውና እንደ ምርጫቸው የሆነውን የሥራ መስክ በጥበብ እንዲመርጡ ለማበረታታት ነው።

የሚጠና ጥቅስ፡- «ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ከፊት ይልቅ ልትበዙ፥ በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ ልትቀኑ፥ የራሳችሁንም ጉዳይ ልትጠነቀቁ፥ እንዳዘዝናችሁ በውጪ ባሉት ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ፥ አንዳችም እንዲያስፈልጋችሁ በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን» [1ኛተሰ. 4፡11-12]

መግቢያ

ሕፃን ሳለህ ሰዎች እንዲህ ብለው ጠይቀውህ ይሆናል። «ስታድግ ምን ለመሆን ትፈልጋለህ?»። አሁን አንተ አራስህን እንዲህ ዓይነት ጥያቄ መጠየቅ ጀመረሃል። ስለዚህ ዋና ጉዳይ እያሰብክ ብትሆንም ለሌላ ሰው ግን ስለነገሩ ማጫወት ከባድ ነው። ምናልባት አንድ ሰው አንተ ወደማትወደው የሥራ መስክ ይገፋፋኛል ብለህ ልታስብ ትችላለህ።

ስለሥራ መስክ ሲነሣ፤ ለመናገር ቢያስፈራም እንኳን፤ አሁኑኑ አንዳንድ ዕቅዶችን ማውጣት፤ በጣም አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ወጣቶች አጥጋቢ ውጤት በማምጣት ዓመት በዓመት እየተማሩ ዮኒቨርስቲ እስከመጨረስ ቢደርሱም እንኳን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ችሎታና ምርጫ ፈጽሞ ግምት ውስጥ አላስገቡትም። በሕይወትህ ውስጥ ልትሰራው ያቀድከውን አንተው ልትወስን ይገባል እንጂ በዘፈቀደ እንዲሁ የሚመጣ ነገር አይደለም።

ትምህርት፡-

በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የምትሠራውን ሥራ ለማግኘት በመጀመሪያ ማሰብ ያለብህ ነገር ቢኖር «የእግዚአብሔር ዕቅድ ለሕይወቴ ምንድን ነው?» ብሎ መጠየቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ። በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል» [ምሳ. 3፡5-6]

እግዚአብሔር አንተን ስለፈጠረህ ስለአንተ በደንብ ይረዳል። ለአንተ ያለውም ፍላጎት የተሟላና የደስታ ኑሮን እንድትኖር ነው። በዮሐ. 10፡10 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ይላል «እኔ ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁም መጣሁ» አንዳንድ ሰዎች ሕይወታቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ማስረከብ ይፈራሉ። ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቸጋሪ እና ከፈቀዳቸው ውጪ የሆነውን ነገር እንዲያደርጉ ይፈልግ ይሆናል ብለው ስለሚያስቡ ነው። እግዚአብሔር ጨካኝ አለቃ ሳይሆን ለአንተ ከሁሉ የሚሻለውን ነገር የሚወድ ሰማያዊ የፍቅር አባት ነው። ሕይወትህን ሁሉ ለእርሱ ስጥና መንገዱን እንዲያሳይህ ጠይቀው።

ሕይወትህን ለእርሱ አስረክበሃል ማለት እጅትህን አጣምረህ ቁጭ በማለት እርሱ የወደፊት ዕቅድህን ሁሉ ገልጦ ይስተሃል ማለት አይደለም። እርሱ ደረጃ በደረጃ ይመራሃል ችሎታህንና ተሰጥኦህን ለይቶ መመርመር ጥበበኛ መሆን ነው።

እውቀት፡ ለማመዛዘን፡ ለመረዳት፡ መረጃዎችንም ተቀብሎ ለማድረግ ያለህ የውርስ ችሎታ ነው። በጣም እዋቂ ያልሆኑ ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ዕውቀት በመጠቀም በሕይወታቸው ዘመን ትልቅ ሥራን የሰሩ ብዙ ንበዝ ሰዎች አሉ። ሌሎች የበለጠ ዓዋቂ ቢሆኑም በሕይወታቸው ምንም ዓላማና ግብ ስለሌላቸው ያላቸውን ተሰጥኦ ሆነ ሕይወታቸውን በከንቱ አባክነውታል። ቁምነገሩ ባለህ ምን ያህል መሥራትህ ነው።

ብታስብበት ያለህን የዕውቀት ደረጃ መገምገም ትችላለህ። ትምህርት ከባድ ነው ወይስ ቀላል? እራስህን እንዴት ትለካዋለህ፡ መካከለኛ ከመካከለኛ በታች ከመካከለኛ ሻል ያለ ወይስ ንበዝ ነህ? የስራ መስክ ስትመርጥ ችሎታህን በሐቅ መገምገም አስፈላጊ ነገር ነው። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የችሎታህን ደረጃ የሚወስን የጠቅላላ ዕውቀት ፈተና ይሰጣሉ። ብትችል እነዚህን ለመውሰድ ተጣጣር።

ጠቅላላ ችሎታ ማለት የተወሰነ ሥራን ለመማርና ለመሥራት ልምምድ ማድረግ ሊሆን ይችላል። ጠቅላላ ችሎታ ማለት በእንግሊዘኛ አፕቲትዩድ ማለት ነው። በእያንዳንዱ የእውቀት ደረጃ ጠቅላላ እውቀት ውስጥ ብዙ ልዩነት አለ። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ከአርእስቶቹ ሥር ችሎታ ላላቸው ሰዎች የሚጠቅም ብዙ ዓይነት ችሎታዎችና የሥራ መስኮች ታገኛለህ።

የተለያዩ ችሎታዎች ከሚስማማቸው የሥራ መስክ ጋር በቅደም ተከተል እንደተዘረዘሩ ተመልከት። አንድ ወይም ሁለት አንተ ይበልጥ ችሎታ አለኝ ብለህ የምታምንበትን ምረጥና ከእነዚህ ችሎታዎች ሥር በጣም ደስ የሚልህን 5 የሥራ መስኮች ጻፍ። ከዚያም በኋላ ስለነዚህ ነገሮች ያለህን እውቀት መርምር። ወደ እዚያ ጎዳና በሚመራህ ትምህርት ጠንክረህ እየሠራህ እዛ ደረጃ ለመድረስ ትችላለህ።

ሁለተኛ ደረጃን የፈፀመች አንዲት ልጃገረድ፤ ወደፊት ነርስ ለመሆን በጣም ትፈልጋለች። እውቀቷን የሚመዝን ፈተና ወስዳ «ከፍተኛ ውጤት» አገኘች። ከዚያም በኋላ ጠቅላላ ችሎታ የሚለካ ፈተና ወሰደች። በሳይንስና በጎብረት በጣም ከፍተኛ ውጤት አመጣች። እነዚህ ሁለቱ ለነርስነት የሚያስፈልጉ ትምህርቶች ናቸው። ይህ ማለት እርሷ በነርስነት ሙያ ሰዎችን ለመርዳት በተጨማሪም አብራቸው ለመሥራት እንደምትችል ያመለክታል። እርሷ ከበሽተኞችም ሆነ ከሥራ ባልደረቦቿ ጋር ስትሠራ ብዙ ችግር አይገጥማትም ማለት ነው። ሆኖም በሳንይስ በጣም ከፍተኛ ትምህርት አግኝታ በሕብረት ግን ዝቅተኛ ውጤት ቢኖራት ኖሮ ከበሽተኞችና ከሥራ ባልደረቦቿ ጋር ተግባብታ ለመስራት ከባድ ችግር እንደሚገጥማት ይጠቁማል። በሌላ በኩል በሳይንስ ዝቅተኛ ውጤት በሕብረት ደግሞ ከፍተኛ ውጤት ብታገኝ ኖሮ ከበሽተኞችና ከሥራ ባልደረቦችዋ ጋር እየተግባባች ትምህርቷን አልፋ ለመመረቅ ግን ከባድ ትግል ይገጥማት ነበር ማለት ነው።

ዝርዝሩን ካወጣህ በኋላ ለወደፊቱ ዕቅድ ስታወጣ እነዚህን ነገሮች አስብባቸው። በእነዚህም ሙያዎች የሚሠሩ ሰዎች ካሉ አነጋገራቸው። ምን ዓይነት ስልጠና እንደወሰዱ እወቅ። የት እንደተማሩም ምን ዓይነት ችግር እንዳጋጠማቸው ስለሥራው የሚወዱትና የሚጠሉት ነገር ካለ እወቅ። ምን አልባት ከዚሁ ሥራ ጋር የሚመሳሰል ሥራ በከረምት ታገኝ ይሆናል ያም ስለሥራው ምንነት በተጨባጭ ይነግርሃል።

በዝንባሌህ ባለው የሥራ መስክ ምን ዓይነት ሥልጠና እንደሚሰጥ ማወቅ መልካም ነው። ዩኒቨርስቲ ወይም ኮሌጅ ወይም ሌላ ቦታ መረጃዎችን፥ ቦታዎችን፥ በመጠቀም ከባለሙያዎች የሚያስፈልገውን ነገር ለማወቅ የበኩልህን ጥረት ማድረግ ይኖርብሃል። የፈለከውን ሥራ ላታገኝ ትችላለህ፤ ሆኖም በትምህርትህ ካልተመደብክ በስተቀር የምትፈልገውን ለመምረጥ መንገድ እንዳለህ አያጠራጥርም።

ትምህርትህን ጨርሰህ ሥራ እየፈለግህ ከሆነ፤ ጥቂት ማስታወስ የሚገባህ ነገሮች አሉ። በማመልከቻ ወረቀት ላይ ሁሉን ነገር በታማኝነት እስከምትችለው ድረስ መሙላትህን አረጋግጥ። የትምህርት መረጃዎችህን ፎቶ ኮፒ በማድረግ ተጨማሪ ፎቶግራፎችህን መያዝ አስፈላጊ ይሆናል። ለቃለ መጠይቅ ስትቀርብ በአነጋገርህ ጨዋ፥ አለባበስህም ንፁሕ ይሁን። በተጨማሪም ስለችሎታህ ወይም ስለ ጠቃሚነትህ ብዙ አታውራ። ሥራውን ካገኘህ በኋላ በደንብ ሥራ። መመሪያዎችን አዳምጥ፤ ያልገባህን ጠይቅ። ስሕተትህን ተቀበል። አለቆችህና የሥራ ባልደረቦችህ ታማኝ በመሆንህ ያከብሩሃል። የተጠየቅኸውን ከዚያም በላይ ለመሥራት ፈቃደኛ ሁን። የሥራ ጊዜህን አክብር።

አንተ ከዚህ ምዕራፍ የምታገኘው ዋና ሐሳብ ስለ ወደፊት ሕይወትህ ዕቅድና ሐሳብ እንድታወጣ ነው። እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያስባል አንተም እንድትደሰትበትና ለእርሱም ጠቃሚ እንድትሆን ይፈልጋል። በየጊዜው እግዚአብሔር እንዲመራህ መጸለይን አትርሳ። የምትሄድበትን መንገድ ለማሳየት እግዚአብሔር ይፈልጋል በእምነትም እርሱን ስትሻ በሩን ይከፍትልሃል ቢያስፈልግም ይዘጋዋል። ለሚቀጥሉት 30ና 40 ዓመታት ያህል፥ በሳምንት አምስት ቀናት፥ በቀን 8 ሰዓት ያህል ሥራ እንደምትሠራ ብታስተውል ምርጫህ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ትገነዘባለህ!

የቁጥርን ችሎታ፤ መረዳትና የሂሣብ ስሌትን መጠቀም

- መዝገብ ያዥ
- የሂሣብ መዝገብ ያዥ
- ልዩ ልዩ ዝርዝር መረጃ የሚይዝ ሠራተኛ
- የሂሣብ አስተማሪ
- የባንክ ገንዘብ ተቀባይ
- የኮምፕዩተር ሠራተኛ
- መሐንዲስ
- ለፋብሪካ የመለወጫ ዕቃ የሚሠራ (ማሽኒስት)
- የሬዲዮ ቴፕና ቲቪ ሥራ ባለሙያ
- የፊዚክስ ባለሙያ

የሳይንስ ችሎታ፤ ችግሮችን መፍታትና ሃሳቦችን መረዳት

- ሕይወት ስላላቸው ፍጡሮች የሚያጠና
- ጠበብት (ባዮሎጅስት)
- ቀግሚ ጥንተ- ንጥረ መድኃኒት (ኬሚስት)
- ሐኪም (ዶክተር)
- አስታማሚ (ነርስ)
- መሐንዲስ (ኤንጂኒየር)
- የሥነ አዕምሮ ሐኪም (ሳይካትሪስት)
- የመድኃኒት አዋቂ (ፋርማሲስት)
- የጥርስ ሐኪም (ዴንቲስት)
- የጥርስ ሐኪም ረዳት (ዴንታል አሲስታንት)
- የቤት ጥላን ኃላፊ (አርክቴክት)

የመገጣጠም ችሎታ፡ (ከማሽኖችና ከማሽን መገልገያ መሣሪያዎች ጋር መስራት)

- የአይሮፕላን ቴክኒሽያን ወይም ነጂ
- የጋራዥ ሠራተኛ
- አናጢ
- የከባድ መኪና ሹፌር
- የኮምፒዩተር ቴክኒሺያን
- በያጅ
- የመጽሐፍ ጠራዥ
- የኤሌክትሪክ ባለሙያ
- ለፋብሪካ የመለወጫ ዕቃ የሚሠራ (ማሽኒስት)
- ከቡልዶዘርና ከግሬደር ጋር የሚሠራ ጠጋኝ
- የተበላሹ እቃዎችን የሚያድስ
- አታሚ

አገናኝ መኮንን (የማህበራዊ ኑሮ ችሎታ ያለው ሰው)፡ ሃሳቦችን መረዳት ከሕዝብ ጋር ተግባብቶ መስራት

- አስተማሪ
- መጋቢ (ፓስተር)
- ወንጌላዊ
- የማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያ
- የሥነ አዕምሮ ምሁር
- የወጣቶች ጉዳይ አማካሪ
- የመዝናኛ ቦታ አስተባባሪ
- በኳስ ጨዋታና በስፖርት ውድድር አሠልጣኝ
- ቀጣሪና የሠራተኛ ጉዳይ አስፈፃሚ
- ጠበቃ (ጥብቅና)
- የሕዝብ ግንኙነት ሠራተኛ

የቃላት አገባብ ችሎታ፤ ለመረዳት፤ የተሳለውን ለመጠቀም ለማንበብና ሆሂያትን ወይም ፊደላትን በትክክል መፃፍ

- አስተማሪ
- ጋዜጠኛ
- አራሚ
- ደራሲ
- ተናጋሪ
- የሕዝብ ግንኙነት ሠራተኛ
- የሬዲዮ ተናጋሪ
- አማካሪ
- የሥነ አዕምሮ ምሁር
- አስተርጓሚ

የኪነ ጥበብ ችሎታ ሥዕል መሳል፤ በቀለም መቀባት፤ አዲስን ነገር ፈጥሮ የሚሰራ ተመራማሪ

- ሰዓሊ
- ቀያሽ (ዲዛይነር)
- የቤት ፕላን ነዳፊ (አርኪቴክት)
- መሐንዲስ (ኤንጂነየር)
- ምልክቶችና ማስታወቂያዎችን በትልልቅ ፊደላት ጽፎ የሚቀባ (ሳይን ፔንተር)
- በመሐንዲስ ክፍል ንድፍ ነዳፊ (ድራፍትስመን)
- ፎቶግራፍ አንሺ (ፎቶግራፈር)
- የንግድ ሽቀጣ ሽቀጥ ማስተዋወቂያ አውጪ (አድቨርታይዘር)

የሙዚቃመሣሪያ የአጨዋወትና፥ የመዘመር ችሎታ

ዝማሬ
የሙዚቃው መሪ
የመዘምራን መሪ
ሙዚቀኛ
የሙዚቃ አስተማሪ

የእርሻ ችሎታ፤ የአፈር እንክብካቤና ከእንስሳት ጋር የሚሰራ ስራ

አትክልተኛ
አራሽ
ከብት አርቢ
የዓሣ አርቢ
ዛፍ ተከላ
የዘር መሻሻያና ምርምር ሥራ
የእርሻ መሣሪያ መጠገን (ሜካኒክ)
የከብት ጤንነትን እንክብካቤ ማድረግ
የዶሮ እርባታ (ፖልተሪ)

የቢሮ አስተዳደር ችሎታ፤ የቢሮን ሥራ በጥራት መስራትና በተፈለገው ጊዜመጨረስ

ፀሐፊ
የቢሮ አስተዳዳሪ
የሂሣብ መዝገብ ያዥ
የባንክ ገንዘብ ተቀባይ
መዝገብ ቤት ሠራተኛ
ልዩ ልዩ ዝርዝር መረጃ የሚይዝ ሠራተኛ
መሬት ቀያሽ (ሰርቬየር)

ለሌሎች ማድረስ የሽያጭ ችሎታ፤ መሸጥ ወይም ሃሳብን

የንግድ ድርጅት ኃላፊ (ቢዝነስ ማኔጀር)
አሻሻጭ
የንግድ ሽቀጣሽቀጥ ማስተዋወቂያ አውጪ
የባንክ ሥራ አስኪያጅ
የቤት ውስጥ ቀያሽ (ኢንቴርየር ዲዛይነር)
ቤትና መሬት የሚሸጥ ነጋዴ

ለአስተማሪ የሚጠቅም

የሚጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡- 1ኛ ተሰ. 4፡11-12 ኤፌ. 4፡28፥ ምሳ. 3፡5-6

በአካባቢህ ስላሉት የሥራ መስኮች ተወያዩ። የተለያዩ ባለሙያዎች ወደ ክፍሉ ጋብዘህ ስለሥራቸው ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ አድርግ። ለምሳሌ ሐኪም፥ ገበሬ፥ አስተማሪ፥ ፋርማሲ ውስጥ የሚሰሩ (የፋርማሲ ባለሙያዎችንና) እነርሱንና የመሣሰሉትን ...

ምዕራፍ 12

መተጫጨትና ጋብቻ (የእጮኝነት ጊዜ)

ዓላማ፡- ለወጣቶች መተጫጨትና ጋብቻን በሚመለከት ዋና መመሪያዎች ለመስጠት በዚህ ንዳና በፀሎትና በጥበብ እንዲበስሉ ለማበረታታት፡-

የሚጠና ጥቅስ «ከክፉ የኀልማስነት ምኞት ግን ሽሽ በንጹህ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል» 2ኛ ጢሞ. 2፡22

መግቢያ

«ወንዶች ልጆችን ከልብ እወዳለሁ ብዙ የማስበውም ስለእነርሱ ነው። ሆኖም ከእነርሱ ጋር ጓደኛ ለመሆን ከተፈለገ ከበሰሉ ሰዎች የሚሰነዘረው የነቀፌታ አስተያየት በጣም ከባድ መሆኑ ይሰማኛል በማለት አስቴር ለጓደኛዋ አጫወተቻት።

ራሄልም እንዲህ ስትል መለሰችላት «እንደዚህ ይሰማሻልን?» ንግግሯንም በመቀጠል «እኔም ከወንዶች ጋር መነጋገር እወዳለሁ። ነገር ግን በጣም አፍራለሁ። ምን እንደምል ምን እንደማወራ እንዴት እራሴን እንደምገልፅ አላውቀም» አለች።

«ወንዶች ልጆችም ደግሞ እንዲህ ይሰማችሁ ይሆናል። ሴቶች ልጆችን በደንብ ለመተዋወቅ ትፈልጉ ይሆናል፥ ነገር ግን ክርስቲያን እንደመሆናችሁ መጠን ሴቶችን እንዴት እንደምትቀርቡ አታውቁም።

ሌሎቻችሁ ደግሞ ከተቃራኒ ፆታ ጋር ባላችሁ ግንኙነት ደስ የማይል ሁኔታ አጋጥሟችሁ ይሆናል። ከዚህ የተነሳ ስህተቱ የት ጋ እንዳለ ያስጨነቃችሁ ይሆናል።

ትምህርት

ከሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔር «ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ፥ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው» [ዘፍ. 1፡27] አዳም ብቸኛ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር እንዲህ አለ። «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፥ ስለዚህ ለእርሱ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» [ዘፍ. 2፡18]

15 ወይም 16 ዓመት ሲሆንህ ለአቅመ አዳም ደርሰሃል ማለት ነው። በስሜትህ ግን አሁንም ማደግ ስለሚኖርብህ በዚህ ምዕራፍ ስለእርሱ እንነጋገራለን።

ሴቶችና ወንዶች የሚተዋወቁበት መንገድ አለ። የቤተክርስቲያን ሥራ በምትሠሩበት ጊዜ በቡድን በአንድ ላይ ስለምትሆኑ ለመተዋወቅ ጥሩ ዕድል ይሰጣችኋል። ሴቶችንም ወንዶችንም በሚያካትት ኮሚቴ ውስጥ ገብታችሁ ሥሩ። ሁለቱም ፆታ የሚሳተፉበት ፕሮግራም አዘጋጁ። ምስክረነታቸውን እንዲሰጡ ወንዶችንና ሴቶችን ጋብዙ። አብራችሁ ዘምሩ፥ ጸልዩ አንድ ላይም ሥሩ። የስፖርት ክፍለ ጊዜ አንድ ላይ አዘጋጁ። ከሌሎች ቤተክርስቲያን ወጣቶች ጋር ለመገናኘት እነርሱም የሚጋብዙበት ኮንፍራንስ ወይም የጨዋታ ጊዜ አዘጋጁ። ይህ በማያሳፍርና በማያስፈራ ሁኔታ ተቃራኒ ፆታን ለመተዋወቅ እንድትችሉ ዕድል ይሰጣችኋል። ብዙ ወጣቶችን እወቁ። ብዙ ጓደኞች ይኑራችሁ። ለወጣት ቡድናችሁ ከቤተክርስቲያን አንድ አዋቂ ወይም

ባልና ሚስት ፕሮግራሙን የሚመሩና እንደዋና ተቆጣጣሪ ሆነው የሚያገለግሉ ቢኖሩ መልካም ነው።

ከዚህ በኋላ ከቡድኑ ውስጥ የተለያዩ ልጆች በተለየ መንገድ መቀራረብ ይጀምራሉ። ደብዳቤ መጻጻፍ ከዚያም ከተወሰነ ሰው ጋርም ከፕሮግራሙ ውጪ ብቻ ለብቻ ተገናኝተው ማውራትን አብሮ ጊዜ ማሳለፍን ይፈልጋሉ። አንዳንዶቹም ፍቅር እንደያዛቸው እርግጠኞች ይሆናሉ።

እስኪ ይህን ሁኔታ እንመልከት። በመጀመሪያ ይህ ሁኔታ ስሕተት ነውን? ሁለተኛም እውነት ፍቅር ይዞአቸዋልን? ለሁለቱም ጥያቄ መልሱ «አይደለም» ነው! በተቃራኒ ፆታ መሳብ ስሕተት እንዳልሆነ ትገነዘባላችሁ። ይህ የተፈጥሮ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር ሲፈጥራችሁ በሌሎች መወደድንና እናንተም መውደድን እንድትሹ አድርጎ ነው። ይህ ስሕተት አይደለም፥ ሆኖም ቁጥጥርና ልምምድ ያስፈልገዋል።

ስለተቃራኒ ፆታ ደስ የሚል ስሜት ሁሉ ፍቅር ነው ማለት እንችላለን እንዴ? ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ይህ ብዙውን ጊዜ በተቃራኒ ፆታ ያለ የመሳሳብ ሂደት ነው። ፍቅር ጠለቅ ያለ አክብሮት ያለውና በረጅም ጊዜ ውስጥ እንዲዳብር የሚደረግ ነገር ነው። የዕድሜ ልክ ፍቅር ሊኖርህ የሚችለው አንድ ሰው ስለሳቀልህና በጨዋ ደንብ ስላነጋገረህ አይደለም። ከሁለቱም ፆታዎች ጋር ተቀላቀል፤ ዳሩ ግን ፍትወተ ሥጋህን ለመቆጣጠር ሞክር። ያንን ስሜት በጠቃሚ ሥራዎች ለውጠው። በቤትና በቤተክርስቲያን የጉልበት ሥራዎችን ሥራ። የስፖርትም እንቅስቃሴ አድርግ።

ጋብቻን የሚደነግጉት ወላጆች በሆኑበት ጎብረተሰብ የምትኖር ነህ ወይስ እራስህም መምረጥ ትችላለህ? ወይስ ሁለቱም ይሠራል? አንተ የምትመርጥ ከሆንክ በጥበብና በጥንቃቄ ከተደረገ የእጮኝነት ወቅት ትርጉም ያለው ጊዜ ሊሆን ይችላል። በእጮኝነት ጊዜ መማር የሚገባ አስፈላጊ ነገር ቢኖር መነጋገርና መግባባት መቻል ነው። ሰፋ ስላሉ ነገሮች ስለ ስፖርት ስለ ትምህርት ቤት ስለ ቤተክርስቲያን ሥራ ስለ ተግራችሁት አዲስ ነገር ተነጋገሩ። እንዲህ ዓይነቱ ጨዋታ ሐሳብ መለዋወጥ እርስ በርሳችሁ እንድትተዋወቁ ይረዳል። አንዱ የሌላውን ቤተሰቦችና ዘመዶች የሚወዱትንና የሚጠሉትን ነገሮች ይወቅ።

አንድ ላይ ብዙ ቦታ ሂዱ፥ ነገር ግን ከጓደኞቻችሁ ጋር እንጂ ብቻችሁን አትሂዱ ሁለታችሁም ተቀምጣችሁ ከምትመለከቱበት የጨዋታ ቦታ ይልቅ ሁለታችሁም መሳተፍ የምትችሉበት የጨዋታ ቦታ ሂዱ። ቴኒስ፥ የመረብ ኳስ፥ ቅርጫት ኳስ፥ የመሳሰሉትን የምትጫወቱበት ቦታ ሂዱ። ሁለታችሁም ከሰዎች መሐል ገብታችሁ በምታሳዩት ሁኔታ የእያንዳንዳችሁን ማንነት ልታውቁ ትችላላችሁ።

የሌላውን ክብር ለመጠበቅ ሲባል አንዳንድ ጥንቃቄዎች መውሰድ ያስፈልጋል። 1ኛ ብቻችሁን ወደ ሰዋራ ቦታዎች አትሂዱ። ከዓለማውያን ቪድዮዎች፥ ሲኒማዎችና ዘፈኖች ተጠንቀቁ! ከአሜሪካና ከአውሮጳ የሚመጡት መዝናኛዎች አብዛኛው ዓለማዊና በኃጢአት የተሞሉ መሆናቸውን ልብ በሉ።

2ኛ ብዙ ሥጋዊ መቀራረብ ወይም መነካካት እንዲኖር ከፈቀዳችሁ ችግር ሊያስከትል ይችላል። ልጃገረዶች ተጠንቀቁ! የወንዶች ፍትወተ ሥጋ የሚነሳሳው በማየት ነው። ስለዚህም እናንተ ክርስቲያን እንደመሆናችሁ መጠን በአለባበሳችሁ በአነጋገራችሁና በአካሄዳችሁ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ጨዋዎች ሁኑ። እናንተ ወንዶች፡- ደግሞ ለልጃገረዶች ተጠንቀቁ! የልጃገረዶች የፍትወተ ሥጋ ስሜት የሚነሳሳው በመዳሰስ ስለሆነ በመሳሳም፥ መነካካት፥

መተሻሸት ከሚገባችሁ በላይ እንድትሄዱ ስለሚያደርግ ከዚህ ድርጊት መቆጠብ መልካም ነው። ከጋብቻ በፊት በነበራቸው የሥጋ ግንኙነት እርስ በርሳቸው ንፅሕናቸውን የተሰራረቁ ሰዎች ለእናንተ እንግዳ ነገር አይደለም፤ እነርሱም በመንፈሳዊ ነገር ይደክማሉ የሕሊና ወቀሳን ይሸከማሉ፤ እንዲሁም እርስ በርስ መናናቅ ይጀምራሉ። ይሄ ሁሉ የደረሰባቸው ጥንቃቄ ካለ ማድረጋቸው የተነሳ ነው። እንዲህ ዓይነት አባባልም አለ፡- «ግብረ ሥጋ ግንኙነት ብናደርግ የበለጠ እንዋደዳለን» ወይም «ሁሉም ሰው የሚያደርገው ነው»፤ ወይም «ብትወጂኝ ኖሮ በነገሩ ትተባበሪኝ ነበር» የሚለው አነጋገር የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት መኖሩ ስሕተት አይደለም፤ ነገር ግን ስሕተቱ ይህን ወደ መጥፎ ድርጊት የሚመራውን ስሜት መቆጣጠር አለመቻል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ስለዚህ የግል ንፅሕና በግልፅ ይናገራል። 1ኛቆሮ. 6፡18-20 ያለውን አንብቡና አጥኑ።

በምትመርጡት የትዳር ጓደኛችሁ ላይ ማየት የሚገባችሁ አንዳንድ ጠባዮች እነሆ፡-

1. እርሱ/እርሷ እንደገና የተወለዱ /የተወለደች አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያከብር/የምታከብር መጽሐፍ ቅዱስ ዋና ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያምን/የምታምን መሆን አለበት/አለባት። ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ጥበብ በቃሉና በጸሎት ያደገ መሆን አለበት።

2. እራሱን የሚገዛና የሚቆጣጠር የሥጋ ምኞቱን፥ ንዴቱንና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚቆጣጠር መሆን አለበት። እርሷም እንደዚሁ።

3. ስለ ሕይወቱ ግብና ዓላማ ያለው መሆን አለበት። ኃላፊነት ባለበት ቦታ የሠራ፥ ሃሣብ አፍላቂ መሆን መልካም ነገር ለማድረግ የሚቀድም፥ ጥንቁቅ መሆን፥ ሰዓትን አክባሪና ዝርዝር ሁኔታዎችን ለማወቅ የሚፈልግ ሰው መሆን አለበት። እርሷም እንደዚሁ።

4. ስሕተቱን የሚያምን ለስሕተቶች ኃላፊነት የሚቀበል ከእነርሱም የሚማር መሆን አለበት። እርሷም እንዲሁ።

5. ስለገንዘብ አያያዝ ጠለቅ ያለ እውቀት ያለውና ለጋብቻና ለቤት መሥረታም የሚሆን ጥቂት ገንዘብ ያጠራቀመ መሆን አለበት። እርሷም እንዲሁ።

6. ለቤተሰቡ፥ ለወላጆቹ፥ ለእህቶቹና ለወንድሞቹ ፍቅር፥ አክብሮትና አድናቆት ያለው መሆን አለበት። እርሷም እንደዚሁ።

7. ጨዋታና ቀልድ የሚያውቅ፥ በራሱ እንኳ የመሳቅ ችሎታ ያለው፥ ባለው መርካትና መደሰት የሚችል መሆን አለበት። እርሷም እንዲሁ።

8. በአቋሙ (ቁመና) የሚያኮራችሁ በአለባበሱም ንፁሕና ሥርዓት ያለው መሆን አለበት። እርሷም እንዲሁ።

9. በራሱ አስተዋይ ውሳኔን ማድረግ የሚችል መሆን አለበት። እርሷም እንዲሁ።

10. ስለ ግብረሥጋ ግንኙነት ስለ ቤተሰብ ሕይወት ስለልጆቹ የተስተካከለ አስተሳሰብ ያለው መሆን አለበት። እርሷም እንዲሁ። 1ኛ ቆሮ. 7 እና ኤፌ. 5፡22-33 ያለውን አንብብ።

ጓደኛችሁ የእግዚአብሔር ምርጫ መሆኑን ካ ረጋገጣችሁና ለጋብቻም ካቀዳችሁ አንዳንድ ሊረዳችሁ የሚችል ሐሳብ አለ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ጋብቻ አራት ጊዜ የተደጋገመ

አንድ ተመሳሳይ የሆነ ሃሣብ አለ። እርሱም በዘፍ. 2:24፥ ማቴ. 19:5፥ ማር. 10:7 እና ኤፌ. 5:31 ላይ ታገኙታላችሁ። አንድ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲደጋገም ጉዳዩ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። ይህንን ጥቅስ ነጥብ በነጥብ እንመልከት። «ስለዚህም ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ»

የመጀመሪያው ነጥብ «መተው» ነው። ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል እዚህ ላይ ግልፅና ቁርጥ የሆነ መለያየት መሆን አለበት። ልክ ሕፃን ልጅ እትብቱ ካልተቆረጠለት መኖር እንደማይችል ሁሉ ጋብቻም ከቤተሰብ መለያየት ከሌለ ሊያድግና ሊጠነክር አይችልም። ልጆች ወላጆቻቸውን መተው አለባቸው፤ እንዲሁም ወላጆችም ደግሞ ልጆቼን መልቀቅ አለባቸው። ይህ በደስታ የተመሠረተ ጋብቻ የሚያስከፍለው ዋጋ ነው። ይህ መኖሩ በሕዝብ ዘንድ የታወቀና ሕጋዊ ሊሆን ይገባል። ብዙ ጊዜ የሁለቱም ቤተሰቦች ሲስማሙ በሠርግ ይከበራል። እራሳቸውን የቻሉ፥ ከዕዳ ነፃ የሆኑ፥ አዲስ ባልና ሚስት ወደፊት ቤተሰባቸውን ሊረዱና ሊወዱ ይችላሉ። ቤተሰቦቻቸውን መተው እንጂ ከነጭራሹ መካድ የለባቸውም።

ብዙ ጊዜ በጋብቻ ውስጥ አለመስማማት ሲኖር ሚስትዮዋ ወደ እናትዋ ቤት ትሮጣለች። ይህ ለምን ይሆናል? የዚህ ምክንያት እርሷ ቤተሰቦችዋን ስትተው እርሱ ግን ፈጽሞ ቤተሰቡን ስላልተወ ይሆን? «መተው» የሚለው ቃል ለሁለቱም ነው መሆን ያለበት። እንዲሁም ውጫዊ መተው ብቻ ሳይሆን ውስጣዊም መሆን አለበት። ሁለቱም አዲስ ቤት ለመሥራት ቤተሰቦቻቸውን መተው ያስፈልጋቸዋል።

እውነተኛ «መተው» ካለ እውነተኛ መተባበር ሊኖር ይችላል። መተባበር ማለት አንድ ላይ ማጣበቅ ወይም መጠረዝ ማለት ነው። አንድ ላይ የተጣበቁ ሁለት ወረቀቶችን ለማላቀቅ ብትሞክሩ ሁለቱንም ትቀዷቸዋላችሁ። ባልና ሚስትንም ለማለያየት ብትሞክሩ ሁለቱንም ትጎዳላችሁ፥ ልጆች ካላቸው እነርሱም ይጎዳሉ። መፋታት ይህንኑ ነው የሚያደርገው። መጣበቅ ለሁልጊዜ የሚኖር ለአንድ ሰው የሆነ ልዩ ዓይነት ፍቅር ነው። እስከ ሕይወት መጨረሻ ድረስ። ለአንድ ሰው ለማካፈልና ታማኝ ሆኖ ለመቀመጥ የሚቻለው የበሰለ ፍቅር ሲኖር ነው።

አንድ ስጋ መሆን የጋብቻን አካላዊ ክፍል ይገልፃል። የዚህ ዓይነቱንም ጋብቻ እግዚአብሔር ደንግጓል። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ይህንን ጥልቅ የሆነ የፍቅር አገላለፅ እየገለፁ እንዲድሉ አቅዷል። አንድ ሥጋም መሆን ከግብረ ሥጋ ግንኙነት የበለጠ ነገር ነው። ይህ ማለት እነዚህ ሁለት ሰዎች ያላቸውን ነገር ሁሉ ያካፍላሉ። አካላቸውንና ሀብታቸውን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሀሳባቸውን፥ ስሜታቸውን፥ ደስታቸውን፥ ሥቃያቸውን፥ ተስፋቸውን፥ ፍርሃታቸውን፥ ብርታታቸውንና ውድቀታቸውን ማካፈል ያስፈልጋል። ይህ የጋብቻ ዋናው ትርጉም ነው። እግዚአብሔርም ከእናንተ የሚፈልገው ይህንኑ ነው።

ጋብቻ ልታስቡበትና ልትጸልዩበት የሚገባ ምን ያህል አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ማየት ትችላላችሁ። እግዚአብሔር እንዲመራችሁና በቃሉም ድምፁን እንዲያሰማችሁ ፍቀዱለት። እግዚአብሔር ለእናንተ የሚሆን የተለየ ሰው አለው። ለዚያ ሰው አእምሮአችሁንና ሰውነታችሁን ንፁሕ አድርጉ። ጊዜው ሲደርስ ትክክለኛ ወደ ሆነው ሰው ይመራችኋል።

እናንተም ደግሞ በተጨማሪ ለጋብቻ መዘጋጀት የሚለውን መጽሐፍ ተከታታይ እትም ልታነቡ ትችላላችሁ። በዚህ ባጭር ምዕራፍ ከሚጠቃለለው የበለጠ ሃሳብ ይሰጣችኋል።

ለአስተማሪ የሚጠቅም

የሚነበብ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡- ዘፍ. 24፥ 1ኛቆሮ. 6፡18-20፥ ኤፌ. 5፡21-33

ከተማሪዎቹ ጋር ግልፅ ሆናችሁ ማውራት እንድትችሉ የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠይቁ። ከዚያም በልጃገረዶችና በወንዶች መካከል ስላለው ግንኙነት የመተጫጨት ጊዜና ስለጋብቻ ተወያዩ። በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ነርስ ወይም ድሬሰር ካሉ እነርሱ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመመለስ ሊረዷችሁ ይችላሉ። ወጣቶች በዚህ መንገድ እርዳታን ቢያገኙ በጣም ደስ ይላቸዋል። በዚህ በወጣትነታቸው ዕድሜ ጤነኛና ታማኝ ትክክለኛና የተሟላ የክርስትና ኑሮ ለመኖርና ለመምራት ኃላፊነት ያለባችሁ እናንተ ናችሁ።

ምዕራፍ 13

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕይወታችሁ ማወቅ።

ዓላማ፡- ወጣቶች ለሕይወታቸው ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈልጉ ለማበረታታትና በየዕለቱም የሚያስተምሯቸውን ቃል እንዲታዘዙት ለማድረግ።

የሚጠና ጥቅስ፡- «ይህን ስለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ»
[2ኛ ቆሮ. 5፡14-15]

መግቢያ

በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አንድ የተደበቀ ምስጢር ቢኖር የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማወቁ ጉዳይ ነው። የዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፈቃድ ለማወቅ ስለማንተጋ ነው። ወይስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ማወቅ ስለማንሻ ነው ብሎ መናገር ከባድ ነው። ሆኖም በዚህ ትምህርት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚረዱን አንዳንድ መመሪያዎችን እንመልከት።

ትምህርት

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለማወቅ ስንናገር ሦስት ነገሮችን እናስባለን። እነርሱም በሚፈልግብን ቦታ እንድንሆን እየጠየቅነው ነው። በመጀመሪያ የት መኖር ይገባናል? በየት አገር መኖር እንደሚገባንም ልናውቅ እንፈልጋለን። ሁለተኛ በዚያ ቦታ ከእነማን ጋር መሆን እንደሚገባን ማወቅ እንፈልጋለን። ማንን ላግባ? ከአበራ ጋር በንግድ ሥራ ልሰማራ ወይስ ከማርታ ጋር ላስተምር? ሦስተኛው ከዚያም ስለ ሙያችን ማሰብ እንጀምራለን። ስለሕክምና አጥንቼ ነርስ ወይም ዶክተር መሆን ይሻላል ወይስ ስለንግድ ትምህርት አጥንቼ የሂሳብ ሹም ልሁን ወይም የሂሣብ መዝገብ ያዥ? ስለዚህ ስለቦታ፥ ስለ ሰዎች ስለ ሥራ እናስባለን በማለት ግጠቃለል እንችላለን። ምናልባት ቁጭ ብለን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቃችን በፊት ከሕይወታችን ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ልናስባችው የሚገባን ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉ መረዳት

በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ አስፈላጊ ነውና ነገር ግን ለእነዚህ የሕይወታችን ክፍሎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው አይደለም ከግለታችን በፊት ማሰብ የሚገባን ሌሎች ነገሮች አሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት ሁለት መንገዶች አሉ።

1ኛ በአጠቃላይ መንገድ፡- የእግዚአብሔር ፈቃድ ለአማኞች በሙሉ በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ

2ኛ በተለየ መንገድ፡- አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ ቦታ ለሚኖሩ አንዳንድ የእግዚአብሔር ልጆች የሚሆን።

በአጠቃላይ (በዓለም ሁሉ) ላለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ስር የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች መዘርዘር እንችላለን። የእግዚአብሔርን ቃል ስታጠኑ ከዚህ የምትጨምሩት ብዙ ነገሮች ታገኙ ይሆናል።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሁሉ ሰው

ሀ. ንሥሐ ገብተው እንዲድኑ፡- 1ኛጢሞ. 2፡4፥ 2ኛጴጥ. 3፡9፥ ማቴ. 18፡14፥ ዮሐ. 6፡40

ለ. በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ፡- ኤፌ. 5፡17-21

ሐ. አዕምሮአችን በእግዚአብሔር ቃል እንዲሞላ፡- [ቆላ. 1፡9፥ ቆላ. 4፡12]

መ. ፈቃዳችንንና ሰውነታችንን ለእርሱ እንድናስገዛ፡- ሮሜ 12፡1-2

ሠ. በሙሉ ልባችን ክርስቶስን እንድናገለግለው፡- ኤፌ. 6፡6-7

ረ. የተቀደሰ ንፁሕ የሆነ ሕይወት እንድንኖር፡- 1ኛተሰ. 4፡3፥ 1ኛጴጥ. 4፡2

ሸ. በሁሉ ለማመስገን 1ኛተሰ. 5፡18

እግዚአብሔር በእኛ ሊገነባ የፈለገው ባሕሪይ አለ። ከእርሱም መማር የምንችለው እራሳችንን በሙሉ ለእርሱ ስንሰጥ ነው። የእርሱ ዋናው ፍላጎት እኛ «በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራሱ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ» [ኤፌ. 4፡15] ፍላጎቱም «ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደ ሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመስራትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍፁማን ይሆኑ ዘንድ» (ኤፌ. 4፡13)።

የእግዚአብሔር ፍላጎት ጌታ ኢየሱስን ለመምሰል እናድግ ዘንድ ነው። በሕይወታችን እንዲፈፀሙ በሚፈቅዳቸው ሁኔታዎች እንድናድግ ያስተምረናል። ለእነዚህ ሁኔታዎች እንዴት እንደምንመልስ በትዕግሥት በምሥጋና ወይስ በአመፅና በማጉረምረም እንደሆነ ያመለክታል። ዕድገት ወደ ሕይወትህ እየመጣ ነውን?

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሚፈጽሙ ሁሉ ጌታ ቃል ገብቶላቸዋል በ1ኛዮሐ. 2፡17 እንዲህ ይላል «... የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል»

የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተለየ መንገድ ለሕይወታችሁ ስለቦታ፥ ስለሰዎችና ስለስራ፥ በሚመለከት እንዳንድ መመሪያዎች እነሆ፥

1. ለጌታ ራስን ማስገዛት ዕብ. 10:5፣ 7-9፣ ዮሐ. 4:32-34፣ 5:30፣ 6:38:- እራሳችንን እንዲህ ብለን መጠየቅ ይገባናል «የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝን?» ስንት ጊዜ እኛ የምንፈልገውን ነገር እንድናደርግ አዕምሮአችንን ለውሳኔ እናዘጋጃለን። ይሽንንም ካደረግን በኋላ ውሳኔአችንን እግዚአብሔር እንዲያፀድቅልን እንፈልጋለን።

2. መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት መዝ. 119:97-105:- በሕይወታችን ለሚደርስብን ለእያንዳንዱ ችግርና ፈተና ሁሉ አይመራንም የእግዚአብሔር ቃል መመሪያና የተስፋ ቃል አለው። የእግዚአብሔርን ቃል እንድናውቅ የሚፈለግበት አንዱ ምክንያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድናውቅ ነው።

3. መጸለይ ያዕ. 1:5:- በተለይ መወሰን ስላለባችሁ ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ንገሩት [2ኛሳሙ.5:17-23] የእግዚአብሔር አመራር በሁሉ ቦታ አንድ አይደለም። ለምሳሌ እግዚአብሔር በአንድ ወቅት በቃሉ በኩል ቢመራን በሌላ ጊዜ ደግሞ ሁልጊዜ በዚሁ ዓይነት መንገድ ይመራናል ብለን እንድናስብ አይገባንም።

4. ሁኔታዎች የሐዋ.16:6-7:- ብዙ ሰዎች ሁኔታዎችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አድርገው ይወስዷቸዋል። እግዚአብሔር በሚደርሱብን የተለያዩ ነገሮች ውስጥ ሊመራን ይችላል። ነገር ግን ውሳኔአችንን በሁኔታዎች ላይ ብቻ የተመረኮዘ መሆን የለበትም። ስለ ወደብ አንድ ታሪክ አለ። ለምሳሌ አንድ መርከብ በሌሊት ወደ ወደብ ይሄዳል እንበል። መርከቡ በውሃ ውስጥ ካለው ድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ ሦስት የሚያበሩ ምልክቶች ተደርገዋል። መርከቡ የሦስቱ የሚያበሩ ምልክቶችን መንገድ በመከተል በሰላም ወደ ወደቡ ይደርሳል ይህ ማለት የሦስቱ መብራት ምልክቶች ሲከተል እንደ አንድ ብርሃን ተመስሎ በቀጥታ ወደፈለገበት ቦታ ይደርሳል። ከእግዚአብሔር ቃል የምናገኘው መመሪያ፣ በጸሎት ያረፈ ልብና ሁኔታዎች ናቸው። እነዚህ ሦስቱ ካሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመከተል እርግጠኞች እንሆናለን።

5. ትዕግሥት መዝ. 37:3-7:- እግዚአብሔርን በተስፋ መጠባበቅ። እግዚአብሔር አንድ ነገር እንድንሰራ ከፈለገ በአንድ ጉዳይ ላይ ሸክምን እያበዛ ይሄዳል። እግዚአብሔር የሚፈልግብንን እስከምናውቅ ድረስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ትዕግሥት በማጣትና ለመጠበቅ ፈቃደኛ ባለመሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳያመልጠን እንጠንቀቅ።

6. ሰላም ፊል. 4:7:- እግዚአብሔር ሰላም ሲሰጣችሁ በትክክለኛ መንገድ ላይ እንዳላችሁ እርግጠኞች መሆን ትችላላችሁ። ሰላም ከሌላችሁ እንደገና ከቁጥር አንድ ጀምሩ።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማግኘትና እርሱንም መከተል አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ፈቃዱን እንድታደርጉ የሚፈልግባችሁ ነገር እስከፍፃሜው ማድረስ በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲህ ልንል እንችላለን:-

የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእንተ ትክክል ነው።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእንተ ከሁሉ የተሻለ ነው።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእንተ የማያስፈራ ነው።

በእግዚአብሔር ፈቃድ ስትሄዱ ከእግዚአብሔር ቃል መልስ ልታገኙለት የምትችሉትን አንዳንድ ጥያቄዎች እራሳችሁን መጠየቅ ትችላላችሁ። ይህ በቀን ሕይወታችሁ የምታሳዩት ፀባይና ለእናንተም ትክክለኛ የማይመስላችሁን ነገር ለማወቅ የሚረዳችሁ ነው። ለእናንተ እርግጠኛ ያልሆናችሁትን ነገር እርግጠኞች እንድትሆኑ የሚረዳችሁ ነው።

1. ወደ ንፅህና ይመራኛልን? 1ኛ ጢሞ. 5:22
2. ሰውነቴን ያንቋሸሻልን? 2ኛ ቆሮ. 6:16፥ 1ኛ ቆሮ. 3:17
3. ሱስ ሊሆንብኝ ይችላልን? 1ኛ ቆሮ. 6:12
4. ማሸነፍ ነው ወይስ መረታት? 1ኛቆሮ. 15:57
5. ነፍስን ይዋጋልን? 1ኛጴጥ. 2:11
6. የሚያጠራጥር ነውን? ሮሜ. 14:23
7. ጊዜን በብልሃት የምጠቀምበት ጉዳይ ነውን? ኤፌ. 5:16
8. ገንዘቤን በትክክል የምጠቀምበት ዘዴ ነውን? 1ኛቆሮ. 4:2
9. ጥሩ አርአያ እንድሆን ያደርገኛልን? 1ኛጢሞ. 4:12
10. በሌሎች ሰዎች ዐይን ስሕተት ነውን? 1ኛተሰ. 5:22
11. ጎረቤቴን ይረዳልን? ሮሜ 15:2
12. ሰውን ያስቀይማልን? 1ኛቆሮ. 10:32
13. ሰውን ያሰናክላልን? ሮሜ 14:21
14. በጌታ ስም ሊደረግ የሚችል ነገር ነውን? ቆላ. 3:17
15. ለጌታ ክብር ሊደረግ የሚችል ነገር ነውን? 1ኛቆሮ. 6:20
16. ለእግዚአብሔርና ለመንግሥቱ የሚበቃ ነገር ነውን? ቆላ. 1:10፥ 2ኛተሰ. 1:5

«ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ» [ኤፌ. 5:17] ለሕይወታችሁ ፈቃዱን ለማወቅ ብትሹ እርሱ ያሳያችኋል እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ለሰማይ አባታችሁ ደስታና ለሌሎችም ለሚከተሉት ምሳሌ ወደሚሆን የበሰለና የተሟላ የክርስትና ኑሮም ይምራችሁ።

ለአስተማሪ የሚጠቅም

የሚጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡- 2ኛቆሮ. 5:14-15፥ ኤፌ. 5:17

በትምህርቱ የተዘረዘሩትን ሁሉ፥

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ፍጹም የሆነ ፈቃድ እንዳለው ማወቁ ያስደስታል። የእግዚአብሔር ፈቃድ በእነርሱ በኩል እየተፈፀመ እርግጠኛ የሆኑበት ወቅት ካለ እንዲወያዩበት ወጣቶቹን አበረታቷቸው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመሥራት የሚያግዱን ማን አለብኝነትና የራስ ፈቃድ የመሳሰሉት ካሉ ተነጋገሩባቸው።

BIBLIOGRAPHY

Blockman, Larence G. *Understanding Your Body,* New York: Crowell-Colier Press, 1968.

Briscoe, Stuart. *Where was the Church When the Youth Exploded.* London: Lakeland Blundell House, 1972.

Caprio, Grank S. and Frank B. Caprio. *Parents and Teenagers.* New York: The Citadel Press, 1968.

Cook Robert A. *It's Tough to be a Teenager.* Wheaton, Illinois: Mairacles Unlimited, 1955.

DeJong, Arthur J. *Making it to Adulthood.* Philadelphia: The Westminister Press, 1972.

Dobson, James. *Preparing for Adolescence.* Toronto, New York, London: Bantam Book, 1978.

Gersh, Dr. Marvin J. and Dr. Iris R. Litt. *The Handbook of Adolescence.* New York: Dill Publishing Co. Inc., 1971.

Hashen, Dorothy, *Just for Girls.* Grand Rapids. Mich.: Baker Publishing House, 1958.

Hendricks, Howard. *How to Prepare Your Young People for Marriage.* Wheaton, Ill.: Victor Books, 1973.

Hendriks, Howard. *Heaven Help the Home,* Wheaton, Ill.: Victor Books, 1973.

Inglis, J.K. *The Textbook of Human Biology,* Second Edition. Oxford: Pergamon Press, 1974.

Josselyn, Iren. *The Adolescent and His World.* New York: Family Service Association of America, 1964.

Knight, John. F. *What a Young man Should Know About Sex.* Omaha, Nebraska, Mountain View, California, Oshawa, Ontario: Pacific Press Publishing Association, 1977.

LaHaye, Tim F. *How to Study the Bible for Yourself.* 17895 Sky Park Circle, Irvine, California, 92714: Harvest House Publishers,

McCoy, Kathy and Charles Wibbelsman. *The Teenage Body Book.* New York: Pocket Books, Gulf & Western Corporation, 1978.

Menninger, Wm. C. *How You Grow Up.* New York: Sterling Publishing Corporation, Inc., 1957.

Miles, Herbert J. *The Dating Game*, Grand Rapids, Michigan, 49506: Zondervan Publishing House, 1975.

Moser, Clarence G. *Understanding Boys.* New York: Associated Press, 1953.

Muuss, Rolf E. *Theories of Adolescence.* New York: Random House, 1975.

Narramore, Clyde M. *Dating.* Grand Rapids, Mich.: Zondervan Publishing House, 1961.

Narramore, Clyde M. *How to Study and be Successful in School.* Grand Rapids, Mich.: Zondervan Publishing House, 1961.

Narramore, Clyde M. *Improving Your Self-Confidence.* Grand Rapids, Mich.: Zondervan Publishing House, 1961.

Narramore, Clyde M. *How to Choose Your Life's Work.* Grand Rapids. Michigan: Zondervan Publishing House, 1971.

Narramore, Clyde M. *Young Only Once.* Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House, 1957.

Pedrick, Bob. *The Cofident Parent.* Elgin, Ill.: David C. Cook Publishing Co., 1979.

Poure, Ken. *Parents, Give Your Kid a Chance.* Irvin, CA: Harvest House.

Price, Eugenia. *Never a Dull Moment.* Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House, 1955.

Renich, Jill. *So You're a Teenage Girl.* Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House,

Riddell, Jim and Melvin Whitehurst. *Career Decision Making.* Nashville, Tennessee: Broadman Press, 1979.

Rice, John R. *The Home.* Wheaton, Ill.: Sword of the Lord, 1945.

Sigsworth, John W. *Careers for Christian Youth.* Chicago: Moody Press, 1956.

Small, Dwight Harvey. *Design for Christian Marriage.* Westwood: Fleming Publishing House, 1959.

Stattford, *The Trouble with Parents is.* Grand Rapids, MI 3/4: Zondervan Publishing House, 1978.

Sutera, Ralph. *On Making My Christian Commitment Stick.* Regina, Sask.: Canadian Revival Fellowship, 1972.

Shryock, Harold. *On Becomming a Man,* R. & H. (SDA).

Trobisch, Walter. *I Married You.* New York: Harper and Row Publishers, 1971.

Trobisch, Walter, *My Parents are Impossible.* New York: Harper and Row Publishers, 1970.

Trobisch, Walter. *Love Yourself.* Downers Grove, Ill. 60515: Inter-Varsity Press, 1976.

Wright, Norman. *An Answer to Parent-Teen Relationships.* Irvine, Calif. 92714: Harvest House Publishers, 1977.

Wright, Norman. *Improving Your Self-Image.* Irvine, Calif. 92714: Harvest House Publishers, 1977.

Zuck, Roy B. and Roy G. Irving. *Youth and the Church.* Chicago: Moody Press, 1968.

ኤይድስ እና ክርስቲያን

ኤይድስ ምንድን ነው?

ለብዙዎቻችን አዲስ መስሉ የሚታየን የኤይድስ በሽታ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1981 ዓ.ም. በሕክምና ሰዎች ተረጋገጠ።

ኤይድስ በኤች አይ ቪ ቫይረስ የተነሣ ይከሰታል። በሽታን የሚፈጥሩ የተለያዩ ዓይነት ቫይረሶች አሉ። የጉንፋን ቫይረሶች ጉንፋን ተብሉ የሚጠራውን በሽታ ያመጡብናል። የፖሊዮ (ልምሻ) ቫይረስ ፖሊዮ (ልምሻ) ብለን የምንጠራውን በሽታ ያመጣል። አሜባን የሚያመጣው ቫይረስ አይደለም፥ ፕሮቶዞአን የሚባሉ የተለዩ ጀርሞች ናቸው። የኤች አይ ቪ ቫይረስ ኤይድስ ብለን የምንጠራውን በሽታ ያመጣል።

አንድ ሰው በሦስት መንገዶች በኤች አይ ቪ ቫይረስ ሊያዝ ወይንም ሊለከፍ ይችላል።

1. የኤች አይ ቪ ቫይረስ ካለው ሰው ጋራ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚያደርግበት ጊዜ፤
2. ሕፃናት ከመወለዳቸው በፊት እናታቸው በኤች አይ ቪ ቫይረስ የተለከፈች ከሆነች በማህፀን ውስጥ ሆነው በዚሁ በሽታ ሊያዙ ይችላሉ።
3. በኤች አይ ቪ ቫይረስ የተለከፈ ሰው ደም ወደ ሰውነትህ ከገባ አንተም በዚሁ በሽታ ልትለከፍ ትችላለህ። ይህም፡- በበሽታው በተለከፈ መርፌ በመወጋት በበሽታው የተበከለ ደም ያለበት ምላጭ ወይንም ሌላ ስለት ነገር ሰውነትህን ቢቆርጥ ወይም በበሽታው የተለከፈ ሰው ደም ወደ ደምህ ቢጨመር(ትራንስፊዩዥን) በሚሆንበት ጊዜ ልትለከፍ ትችላለህ።

አንድን ሰው በመንካት ወይንም በመጨበጥ በኤች አይ ቪ ቫይረስ አትለከፍም። የወባ ትንኝ፥ ቁንጫ፥ ትኋንና ሌሎችም ተባዮች ይህንን በሽታ ሊያመጡብን አይችሉም። ኤይድስ ካለበት ሰው ጋር በመኖር ወይንም አብሮ በመብላት በበሽታው አንለከፍም። ከምላጭና ከሌሎች ስል ነገሮች እንዲሁም ከመርፌ ከተጠነቀቅን ኤይድስ ሊይዘን የሚችልበት መንገድ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብቻ ነው። በአፍሪካ አብዛኛዎች ሰዎች በኤይድስ የሚያዙት የኤች አይ ቪ ቫይረስ ካለባቸው ሰዎች ጋራ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲያደርጉ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎች በኤች አይ ቪ ቫይረስ በሚለከፉበት ጊዜ በጤንነታቸው ላይ ምንም ለውጥ አያስከትልም። ለጥቂት ዓመታት ምንም ለውጥ ሳያዩ መቆየት ይችላሉ። በእነዚህ ዓመታት ይህንን ኤች አይ ቪ ቫይረስ ለብዙ ሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሰዎቹ በበሽታው ምልክቶችንና ሕመምን ማየት ይጀምራሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሕመሙ ልክ እንደ ሌሎች ሕመሞች ሊመስል ይችላል። ደሙ በልዩ የሕክምና ምርምር ጣቢያ (ላቦራቶሪ) ከተመረመረ ብቻ ለኤይድስ መኖር እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ከዚያ በኋላ ሕመሙ በጣም ከባድና ሕክምና ለመስጠትም በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። በኤች አይ ቪ ቫይረስ ከተለከፉ በኋላ ብዙ ሰዎች በ5 ዓመት ውስጥ ኤይድስ ይይዛቸዋል። በብዙ ቦታዎች እንደታየው ኤይድስ ያለባቸው ሰዎች በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ይሞታሉ።

ኤይድስ ማንንም ሊያጠቃ ይችላል። ነገር ግን የግብረ ሥጋ ግንኙነትን አብዝተው በሚያደርጉ ጤነኛ በሚመስሉ የደረሱ ወጣቶች አካባቢ በብዛት ይገኛል። እነኚህ ዓይነት ሰዎች ሠራተኞች

ተግሪዎች እናቶችና አባቶች ናቸው። በኤይድስ በሽታ ከሚሞቱት የኤች አይ ቪ ቫይረስ ካለባቸው እናቶች ከሚወለዱ ሕፃናት መሃከል በግምት ከሦስት አንዱ በኤይድስ በሽታ ተለክፈው ይሞታሉ።

ዛሬ ኤይድስ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ይገኛል። በአፍሪካ ግን ሁኔታው እጅግ የከፋ ነው። በኡጋንዳ ዋና ከተማ በካምፖላ ከአራት ሰዎች መካከል አንዱ በኤይድስ በሽታ የተለከፈ ነው። በአሁኑ ጊዜ ትላልቅ ወጣቶችን፣ ሕፃናትንና ትምህርት ቤትን ያረጁ ሰዎችን ትተው የሞቱባቸው «የተተዉ መንደሮች» ብዙ ናቸው። በኡጋንዳ የሚገኙ ሆስፒታሎች በኤይድስ በተያዙ ሰዎች ተሞልተዋል። ኢትዮጵያ ከኡጋንዳ በአምስት ዓመት ብቻ ወደ ኋላ ነች። በጤና ጥበቃ የታወቁ በኤይድስ የተያዙ ሰዎች 5000 ብቻ ናቸው። ነገር ግን 530 000 ሰዎች በኤች አይ ቪ ቫይረስ እንደ ተለከፉ ይገመታል። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከእነኚህ ሰዎች ብዙዎቹ በኤይድስ በሽታ ይለከፋሉ ተብሎ ይጠበቃል። (መረጃ ነሐሴ 1985)

በአዲስ አበባ የተደረገው ጥናታዊ ዘገባ እንደሚያሳየው አንድ ባል ብቻ ካላቸው ሴቶች ግማሽ የሚሆኑት ጭብጥ በሚባለው በሽታ ተለክፈዋል። ጨብጥ ልክ እንደ ኤይድስ ከሰው ወደ ሰው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ይተላለፋል። ከዚህ ጥናት ልንል የምንችለው ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ጭምር እንኳን ለትዳር ጓደኞቻቸው ለባል ወይንም ለሚስት ታማኝ ሆነው አለመገኘታቸውን ነው። ሰውነታቸውን በመሸጥ የሚተዳደሩ ሴቶች (ሴተኛ አዳሪዎች) ቁጥር እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል። ይህም የሆነው ብዙ ወንዶች ለዚህ ዓይነቱ አጸያፊ ግንኙነት ገንዘባቸውን ለማውጣት በመፈለጋቸው የተነሣ ነው።

ሁለት ሰዎች (የትዳር ጓደኞሞች) ብቻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚፈጸሙበት ሁኔታ በኤች አይ ቪ ቫይረስ የመለከፍ ሥጋት ሊኖር አይችልም። ነገር ግን ከጋብቻ ውጭ በሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የኤች አይ ቪ ቫይረስ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው በቀላሉ ይተላለፋል።

ኤይድስ አዲስ እና የሚያስፈራ በሽታ በመሆኑ ብዙ ውሸት የሆኑ ነገሮች ስለ ኤይድስ ይነገራሉ። አንዳንድ ሰዎች የኢትዮጵያውያን ምግብ በርበሬ ኤይድስን ይከላከላል ይላሉ። ብዙ ጊዜ ኤይድስን የሚፈውሱ መድኃኒቶች እንደ ተገኙ ይነገራል። የሚያሳዝነው ነገር ግን እነኚህ ወሬዎች በሙሉ እውነት አይደሉም።

ኢትዮጵያ አገር አቀፍ የሆነ ወረርሽኝ እየገጠማት ነው። ሰዎች የሚኖሩበትን መንገድ በተለይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አኗኗራቸውን ካልቀየሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይሞታሉ። አንዳንድ የሕክምና አዋቂዎች ሰዎች ራሳቸውን በመጠበቅ ካልኖሩ በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ከ3 ሰዎች 1 ሰው በኤይድስ እንደሚሞት ይናገራሉ።

በአብያተ ክርስቲያናት ለምን የግብረ ሥጋ ግንኙነትና ሴተኛ አዳሪነት (ዝሙት) ችግሮች እንደሆኑ ልንወያይ ይገባል። ክርስቲያኖች ስለ ኤይድስ ምን ማድረግ እንደሚኖርባቸው ልንወያይ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ በሚለው ጀምረን ይህንኑ ለሌሎች ማስተማር ይኖርብናል።

ልናስብባቸውና ልንወያይባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

1. ለምን የኤይድስ በሽታ በጣም እየተዛመተ መጣ?

2. ኤይድስ እንዴት እንደ ተዛመተ፥ እንዴትስ መከላከልና መረመስ እንደሚቻል ምን የሰማሃቸው ወሬዎች አሉ?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ምን ያስተምራል?

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው፤ እግዚአብሔር እንደ ጋብቻ ክፍል አድርጎ ግብረ ሥጋን ለወንድና ለሴት ሰጥቷል።

በመጽሐፍ ቅዱስ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በጋብቻ ብቻ የመወሰን አስፈላጊነት ተነግሮናል። «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» ዕብ. 13፡4።

ከጋብቻ ውጪ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይንም ዝሙት እንዲሁም ከሴተኛ አዳሪዎች ጋራ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብዙ ጊዜ ተወግዟል፤ ማስጠንቀቂያም ተሰጥቶበታል። ምሳሌ 2፡16-19፤ 6፡20-29።

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቅዱስ ስጦታ ነው። ቅዱስ የሆነ ሥጦታችንን የማንጠቀምባቸው ጊዜያት መቼ እንደሆኑ ልናውቅ ይገባል፤ (ዘሌ. 18)። መጽሐፍ ቅዱስ ከቅርብ ዘመዶቻችን ጋራ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊኖረን እንደማይገባ ይነግረናል። (6-19) በሴቶች የወር አበባ ጊዜ (ቁ. 19)፥ በአንድ ዓይነት ዖታዎች (ሆም ግብረ ሰዶም ቁ. 22)፥ ከእንስሳት ጋራ(ቁ. 23) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ አጥብቆ ተከልክሏል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ቀላል ኃጢአት አልታየም። ለእስራኤል ልጆች በሞት ቅጣት የሚቀጣ የከፋ ኃጢአት ነበረ፤ (ዘዳ. 22፡22-24)።

ከጋብቻ ውጪ የሆነ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው። ነገር ግን በዚህ ልምምድ ውስጥ ላለ ሰው ሌላም አስከፊ ውጤት አለው። «ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮ የጎደለው ነው፤ እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል» ምሳሌ 6፡32።

1ኛ ቆሮ. 6፡12-20 አጥና። ግብረ ሥጋ ቀላል ነገር አይደለም። ከሌላው ሰው ጋር በግብረ ሥጋ ስንተባበር ከዚያ ሰው ጋራ አንድ ሆንን ማለት ነው። ይህ የተቀደሰ ነገር ነው። በግል ፍላጎት ወደዚህ ልምምድ መግባት አይገባንም። ከጋብቻ ውጪ የሆነ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መንፈሳችንን ይጎዳል። ሰውነታችንን በኤይድስ ብቻ ሳይሆን በሌላ ብዙ በሽታዎችም ይጎዳል።

ነገር ግን ከጋብቻ ውጪ ግብረ ሥጋ አደገኛ ነገር ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ ግን የተዋበ ነገር መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል።

«ውዴ ሆይ እነሆ አንተ ውብ ነህ መልከ መልካምም ነህ። አልጋችንም ውብ ነው» መኃ. 1፡16

መኃልየ የፍቅርን ደስታ ያከብራል፤ ይህም ከትልቅ ፍላጎት ጋር ከሆነ ግብረ ሥጋ ፍቅርን ይጨምራል። ስለዚህ ነገር ማውራት አንዳንዶችን ሊያሳፍራቸው ወይንም ሊያስከፋቸው ይችላል። ነገር ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለዚህ ነገር መወያየት ይኖርብናል። መጽሐፍ

ቅዱስ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ጠቃሚ የሆኑት ምክሮች አሉት። ምሳሌ 5፡15-20 አጥና። በዚህ ቦታ በጋብቻ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን እንድንደሰትበት ተጽፎዋል። ከጋብቻ ውጪ ግን አይደለም። 1ቆሮ.7፡2-5 ስናጠና ደግሞ በጋብቻ ውስጥ የእንዳችንን ሰውነት ለሌላው እንድንሰጥ ተመክረናል። ባለ ትዳር ሰው ወይንም ያገባ ሰው ባል ወይንም ሚስት ለኑሮ ጓደኛቸው የግብረ ሥጋን ደስታ እንዴት መስጠት እንዳለባቸው ማሰብ ይገባቸዋል። እግዚአብሔር ወንድም ሴትም በግብረ ሥጋ እንዲደሰቱ እንደሚፈለግ ልናስተውል ይገባል።

አንድ ሊስተዋል የሚገባ ነገር አለ። ብዙ ሰዎች ከጋብቻ ውጪ የሆነ ግብረ ሥጋ ስህተት እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን ብዙዎች ይህንን ያደርጋሉ። በቤተ ክርስቲያን እንኳን በጣም እየተለመደ መጥቷል። ለምን? በአንድ መንገድ እንደምንኖር እየተናገርን ነገር ግን በምስጢር በሌላ መንገድ የምንኖር ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ግብዞች ብሎ ይጠራናል። ግብዝነት የቆየና የተለመደ ኃጢአት ነው። ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እንኳን በግብረ ሥጋ ግብዝነት ኃጢአት ወድቀዋል የይሁዳን ታሪክና (ዘፍ.38) የዳዊትን ታሪክ (2ኛ ሳሙ.11፡1-12፡13) አጥና። በእነዚህም በሁለቱም ክፍሎች ሰዎቹ ራሳቸው ባደረጉት ኃጢአት ሌሎችን ለመኮንን ተዘጋጅተው እንደነበረ አስተውል። ሉቃ.12፡1-3 አጥና። ኃጢአት በልባቸው እያለ ንጹሕ ለመምሰል በመሞከራቸው ባሳዩት ግብዝነት ኢየሱስ ክርስቶስን እጅግ አድርጎ አሰቆጥቶታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ልንደብቃቸው የምንሞክራቸው ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ግልጽነት እንደሚመጡ ተናግሯል።

«አንቺ ግን ንጹሕ ነኝ በእውነት ቁጣው ከእኔ ተመልሶአል አልሽ እነሆ ኃጢአት አልሰራሁም ብለሻልና በፍርድ እከሰሰሻለሁ።» ኤር.2፡35።

መጽሐፍ ቅዱስ ለኃጢአታችን ማድረግ የሚኖርብንን ብቸኛ ነገር በግልጽ መናዘዝ እንደሆነ ግልጽ ያደርግልናል። መዝ.32፡5፤ 1ኛ ዮሐ.1፡8-10። በተደበቀ ኃጢአት ለመኖር ብንሞክር የእግዚአብሔር ቁጣ በእኛ ላይ ይነዳል። መዝ.66፡18፤ ማር.4፡22፤ 1ኛጢሞ.5፡24 አንብብ።

ከጋብቻ ውጪ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት በአጠቃላይ ልናስታውሳቸው የሚገቡንንም ነገሮችን ይነግረናል። መጽሐፍ ቅዱስ ከጋብቻ ውጪ ስላለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያስተምረውን ለመርዳት ስለ ኃጢአት ያለውን አጠቃላይ ትምህርት መገንዘብ አለብን። ያዕ.1፡13-15፤ 1ዮሐ.3፡4-10 ተመልከት።

ልናስብባቸውና ልንወያይባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

1. ለምንድነው ስለ ግብረ ሥጋ ለመነጋገር አስቸጋሪ የሚሆንብን?
2. ቤተ ክርስቲያን ስለ ግብረ ሥጋ ምን ማስተማር ይኖርባታል? ለማን? እንዴት?
3. በጥሩም ሆነ በመጥፎ መልኩ፥ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትል የኢትዮጵያ ባህል የትኛው ይመስልሃል?

እንዴት እንኑር?

የግብረ ሥጋ ኃጢአት የሁሉ ፈተና ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግብረ ሥጋ ኃጢአት ብዙ ጊዜ ይናገራል። ምክንያቱም አስቸጋሪና የሁሉ ችግር ስለ ሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት

እንዳናደርግ ያዘናል። ነገር ግን ኃጢአትን ለማስወገድ እንዴት መኖር እንዳለብንና በእግዚአብሔር እርዳታም እንዴት ፈተናን መወጣት እንድምንችልም ይነግረናል። እግዚአብሔር ቅዱስ እንድንሆን ይፈልግብናል። ሰውነታችን አእምሮአችንና ልባችን እግዚአብሔርን ለማገልገል የተሰጡና የተዘጋጁ ሊሆኑ ይገባል።

«ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ» ሮሜ 12:1፤ (ዘሌ.20:7-8፤ ዘዳ.6:5፤ ማቴ.22:37) ተመልከት።

እንደዚህ ሆነን እግዚአብሔርን ለማገልገል ቃል ከገባን እግዚአብሔርም እንደሚረዳን ቃል ገብቶልናል። በፈተና ጊዜ እንደሚረዳን ቃል ገብቷል፤ (1ቆሮ.10:13)። እንደዚሁም መለወጥ እንድንችል እንደሚረዳን መንፈሳችንን እንደሚያጠነክር አእምሮአችንን ለውጦ ፈተናንና ችግርን መቋቋም እንድንችል እንደሚያደርገን ቃል ገብቶልናል፤ (ሮሜ 12:2)። ነገር ግን እኛ ፈተናን በመቋቋም የተጋን ልንሆን ይገባናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን እርምጃዎች ከወሰድን እግዚአብሔር ይረዳናል። (ማቴ.5:27-30፤ 1ቆሮ.6:18) አንብብ። ከፈተና ልንሸሽ የሚፈትኑንን ነገሮች ከሕይወታችን ልንቆርጥ ከክፉ አስተሳሰብ እንኳን ልናመልጥ ይገባናል። ነገር ግን የክርስቲያን ሕይወት ከፈተና መሸሽ ብቻ አይደለም። መዝ.119:9-11፤ ፊል.4:8፤ 1ኛጢሞ.6:11፤ 2ኛጢሞ.2:22። መጽሐፍ ቅዱስ ለመጥፎ ሀሳብ ቦታ ሳናስቀር ጥሩና ንጹሕ የሆነውን ነገር እንድናስብ ይመክረናል። በመልካምና ጥሩ ነገሮች ከተጋን ለመጥፎው ቦታ የለንም ማለት ነው። በተለይ የእግዚአብሔርን ቃል የማንበብ የመጸለይና ለመረዳዳት አብሮ የመሰባሰብን አስፈላጊነት ተነግሮናል። (ኤፌ.6:10-18)፤ አጥና። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ቅድስና የኃጢአት አለመኖር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ጽድቅን፥ እምነትን፥ ፍቅርን፥ ትዕግሥትን፥ እውነትንና ሰላምን ባለን ኃይል ሁሉ መከተል ማለት ነው። ብዙ የምናስወግዳቸው ነገሮች ቢኖሩም ክርስቲያኖች ብዙ ደግሞ ልናደርጋቸው የሚገቡን ነገሮች አሉ ማለት ነው።

በፈተና ልንወድቅ እንደምንችልም ልናስታውስ ይገባል። ይህ ችግር የሌሎች ብቻ እንደሆነ እያሰብን በአስተሳሰባችን ትዕቢተኞች ልንሆን አይገባም። (ምሳ.16:18፤ 1ኛቆሮ.10:12 አንብብ።) ኃጢአት ብንሠራ በምንም ዓይነት ልንደብቀው አይገባም።

«በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሁሉ ሊያነጻን (እግዚአብሔር) የታመነና ጻድቅ ነው» 1ዮሐ.1:9።

ኃጢአት በምናደርግ ጊዜ ስሕተታችንን ለእግዚአብሔርም ሆነ ለክርስቲያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንም ልንናዘዝ ይገባናል። ስሕተታችንን ከተናዘዝን በኋላ ይህንን ስሕተት ላለመድገም አዲስ መንገድን እንጀምራለን ማለት ነው።

«...ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ» ሉቃ.13:3።

ንስሐ መግባት ማለት ከእግዚአብሔር ይቅርታ መጠየቅና የአኗኗራችንንም መንገድ መቀየር ማለት ነው። ከዚህ በኋላ በእነዚህ ስሕተቶች መኖራችንን አንቀጥልም ማለት ነው። (ዘሌ.26:40-42፤ 2ዜና 7:13-14፤ መዝ.51፤ ኢዩ.2:12-17።) ንስሐ ትንሽ ነገር አይደለም። በእግዚአብሔር ፊት ልባችን መሰበር አለበት። ሁልጊዜ የጥሩ ንስሐ ምልክቱ የቅድስናን ሕይወት ለመኖር መመለስ ነው። ይህንን መንገድ ብንከተል እግዚአብሔር በደስታ ይቅር ሊለን፥ ሊቀበለንና እንዲሁም አንዳንዴ ሊፈውሰን ቃል ገብቷል።

ብዙ ሰዎች ኤይድስ ያስፈራቸዋል። ከፍርሃታቸው የተነሣ አንዳንድ ሰዎች አኗኗራቸውን እንኳን ይለውጣሉ። ለክርስቲያን ግን ይህ በቂ አይደለም። የቅድስናን ኑሮ መኖር ያለብን በእግዚአብሔር ፍቅርና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በተገለጸው ምሳሌነቱ የተነሣ ሊሆን ይገባል እንጂ በፍርሃት የተገፋ ብቻ መሆን የለበትም።

«ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል፣ ...ፍርሃት ቅጣት አለውና የሚፈራ ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም» 1ዮሐ.4፡18።

ክርስቲያን ኤይድስን ጨምሮ የኃጢአትን ውጤት ለሌሎች ማስጠንቀቅ ይኖርበታል። ነገር ግን የቅድስና ኑሮ የፍርሃት ውጤት አይደለም። ነገር ግን የኢየሱስን ምሳሌ የመከተልና ከእግዚአብሔር እርዳታ የመቀበል ውጤት ነው።

ልናስብባቸውና ልንወያይባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

1. የቅድስና ሕይወት ምን ይመስላል?
2. በቤተሰባችን ውስጥ ከጓደኞቻችን ጋራ በቤተ ክርስቲያን የቅድስና ሕይወት እንዲኖረን አንዳችን አንዳችንን እንዴት ልናበረታታ እንችላለን?

ቤተ ክርስቲያን ለኤይድስ ማድረግ ያለባት ነገር ምንድን ነው?

ብዙ ሰዎች ኤይድስ ከእግዚአብሔር የመጣ ፍርድ እንደሆነ ያስባሉ፤ ዘሌ.26፡14-26፤ ዕብ.10፡26-31። በኃጢአታቸው ለሚጸኑና ወደ እግዚአብሔር ለማይመለሱ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዴ እግዚአብሔር በበሽታ እንደሚፈርድባቸው ያስተምረናል። ይህም አንዳንዴ ኃጢአቱን ባላደረጉ ሰዎች እንደ ነቢያት ባሉ ከእስራኤል ልጆች ጋራ አብረው በተሰቃዩ ላይ እንደ ደረሰ እንመለከታለን። አንዳንድ ሰዎች ኤይድስ የእግዚአብሔር ፍርድ ከሆነ እኛችንን ወደዚያ ማስገባት የለብንም ይላሉ። ይህ አባባል ግን ስሕተት ነው። «ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበረና በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን። ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» 2ቆ.5፡18-20።

እኛ ሁላችን ኃጢአተኞች ነን። መጽሐፍ ቅዱስም የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦልናል፤ (ሮሜ 3፡23፤ 6፡23)። ነገር ግን እግዚአብሔር የምሕረት አምላክ ነውና እንድንኖር ፈለገ።

«ነገር ግን ሁሉ ወደ ንሰሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም... እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል» 2ኛጴጥ.3፡9።

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ፍርድ ዓላማ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ነው። ኢየሱስ ወደ ምድር ለመሞትና እኛን ከፍርድ ለማዳን መጣ። ይህንንም ያደረገልን እኛ የሚገባን ሆነን ሳይሆን

እግዚአብሔር ስለ ወደደን ነው። የእኛም አቀራረብ እንደዚሁ ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር እንደወደዳቸው ሌሎችን ብንወድ ምኞታችን እነርሱን ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማዳን ይሆናል ማለት ነው። እንዲሁም ሌሎችን እግዚአብሔር እንደ ወደዳቸው ከወደድናቸው የግብረ ሥጋን ኃጢአት ውጤት እንዲያመልጡ በመርዳት ከኤይድስም አስከፊ ውጤት እንታደጋቸዋለን ማለት ነው። ሕዝ.33፡1-20፤ ሮሜ.5፡12-21 አጥና።

«ኃጢአተኛውን ኃጢአተኛ ሆይ በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁ ጊዜ ኃጢአተኛውን ከመንገዱ ታስጠነቅቅ ዘንድ ባትናገር ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል፤ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ» ሕዝ.33፡8።

ከመጽሐፍ ቅዱስ አያሌ ትምህርቶች ሰዎች ሁሉ በተሳሳቱ ጊዜ እግዚአብሔር እንዲለወጡ ፈልጎአል። እግዚአብሔር ሕዝቡ ሌሎችን እንዲለወጡ እንዲረዱ እንጂ እንዲኮንኑዋቸው ወይም ፍርድና ሞት በላያቸው እስኪወድቅ እንዲጠብቁ አይፈልግም። ይህ የእኛ ኃላፊነት ነው። ዮሐ.8፡1-11 አጥና። የኢየሱስ ትምህርትና ምሳሌ ግልጽ ነው፤ እንደ ኢየሱስ በሌሎች ላይ መፍረድ (መኮነን) የለብንም። ስለ ኃጢአታቸውም እንዲሠቃዩ መመኘት የለብንም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ምሕረትና መንገድ በማስተማር ከኃጢአት እንዲጠበቁ ልናደርጋቸው ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስን ምሳሌ መከተል ከፈለገች የሚከተለውን ልታደርግ ይገባል

1. ለሰዎች ትክክለኛውን መንገድ ማስተማር ይገባል። በመጀመሪያ ደረጃ በቤተሰባችን ውስጥ የእግዚአብሔርን የቅድስና መንገድ ለማስተማር ጊዜ መውሰድ አለብን። ይህም ትክክለኛውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚጨምር ሊሆን ይገባል። ይህም ስለምናስተምረው ትምህርት ትክክለኛ የሆነ የኑሮ ምሳሌነትም ሊኖረን ይገባል ማለት ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥም መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት መኖር እንዳለብንና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ምን እንደሚል ማስተማር አለብን። ይህንን ችግር ሊያስወግዱ የሚችሉ ባሕላዊ ጉዳዮችን ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነትና ስለ ኤይድስ ማስተማርን መፍራት የለብንም። በመጨረሻም ለዘመዶቻችን ለጓደኞቻችንና ለጎረቤቶቻችን ትክክለኛውን የአኗኗር መንገድ ለማስተማር መፍራት የለብንም።

2. ሰዎች ትክክለኛውን መንገድ እንዲከተሉ መርዳት አለብን። ከብዙዎቹ ሴተኛ አዳሪዎችና ሌሎች ሰውነታቸውን ከሚሸጡ ሴቶች ይህንን የሚያደርጉት ሌላ የገንዘብ ግፊኛ ዘዴ ስለሌላቸው ነው። ለወጣት ሴቶች ሥልጠናን መስጠት ሥራን መፍጠር ከወላጆቻቸው ጋራ ማስታረቅ እንዴት እንደምንችል ማሰብ ያስፈልገናል።

በአንድነት ወይንም በቡድን ሆነን የቅድስናን ሕይወት ለመኖር እርስ በእርሳችን መረዳዳትና መበረታታት አለብን። ይህም እያንዳንዳችን ለሌላው ኃጢአታችንን መናዘዝንም ይጨምራል። በየራሳቸው ዓላማ ሥር አብያተ ክርስቲያናት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች አሉ። እንኅህን ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲያስቡና ምን ግድረግ እንዳለባቸው ልናስብ ይገባል።

3. ምሕረትና ርኅራኄን ግላዊት እንጂ መፍረድ ወይንም መኮነን የለብንም።

ክርስቲያናዊ ፍቅር ኤይድስ ለያዛቸው ሁሉ ልናሳያቸው ይገባል፤ አንዳንዶች የሚቆዩበት ቦታ ይፈልጋሉ፤ በተለይ ተቀባይነት እንዳላቸው ማየት በጣም ይፈልጋሉ።

ልናስብባቸውና ልንወያይባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

1. ቤተ ክርስቲያን ኤይድስ ለያዛቸው አባሎችዋ ምን ማድረግ ይኖርባታል። (ሰው ኤይድስ አለበት ማለት በግብረ ሥጋ ኃጢአት ላይ ወድቋል ማለት እንዳልሆነ አስታውስ። ምንም ኃጢአት የሌለባቸው ሰዎች በኤይድስ ሊለከፉ ይችላሉ።)

2. በአካባቢያችን፥ በቤተ ክርስቲያናችን፥ በት/ቤቶችና በቤተሰቦች ስለ ግብረ ሥጋ፥ ኤይድስና የተቀደሰ ኑሮ ማስተማር ለመጀመር መውሰድ ያለብን እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

3. ሰውነታቸውን የሚሸጡትን ብዙ ወጣት ሴቶች ለመርዳትና ለማገልገል መውሰድ ያለብን ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው።

4. ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በማንኛውም መንገድ ለሚያደርጉ ወይም ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ገንዘባቸውን በማውጣት ላይ ላሉ ወንዶች ቤተ ክርስቲያን እንዴት ልትደርስላቸው ትችላለች?

5. በኤይድስ ለተያዙ ሰዎች ክርስቲያናዊ ፍቅርና ርኅራኄን ለማሳየት መውሰድ ያለብን እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

ዕርማት

በዓለማችን ላይ የኤይድስ በሽታ በከፍተኛ ደረጃ ተሰራጭቶ ይገኛል። በተለይም በአፍሪካ አህጉር ሁኔታው በአስጊ ሁኔታ እየተሰራጨ ነው። ለምሳሌ ያህል በኡጋንዳ በአሁኑ ሰዓት በዋናው ከተማ በካምፖላ ውስጥ ከ 4 ሰዎች መሃል አንዱ ሰው የኤች፥ አይ፥ ቪ ቫይረስ ተሸካሚ ነው። በአንዳንድ አካባቢዎችም በሽታው ከመባዛቱ የተነሳ ወላጆች አልቀው ልጆችና አዛውንቶች ብቻ የቀሩበት መንደሮች ይገኛሉ። የኡጋንዳ ሆስፒታሎችም በኤድስ በሽተኞች ተጨናንቀዋል።

ኢትዮጵያም ከዚህ አስፈሪ ሁኔታ ብዙም አልራቀችም። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንደሚገልፀው ከሆነ በኢትዮጵያ የበሽታው ተጠቂዎች ብዛት በ አስር ሺዎች ውስጥ ይገመታል። በአሁኑም ጊዜ የኤች አይ ቪ ቫይረስ ተሸካሚዎች ቁጥር ብዛት በየአመቱ በአደገኛ ሁኔታ እየጨመረ እንደሆነ ይነገራል። ከእነዚህ ሰዎች አብዛኛዎቹም በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ውስጥ የኤይድስ በሽታ ተጠቂዎች ይሆናሉ።